# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ሐሙስ | 82ኛ ዓመት ቁጥር 166 የካቲት 16 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10:00 | ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!







# ጉባኤው የኢትዮጵያን ወቅታዊ የሰላምና የልማት ሁኔታ ለማስረዳት መልካም አጋጣሚ ፈጥሯል

## - ከአንድ ሺህ በላይ የአገር ውስጥና የውጭ ጋዜጠኞች ሽፋን ሰጥተውታል

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- የአፍሪካ ኅብረት የመሪዎች ጉባኤ ኢትዮጵያ ያለችበትን ወቅታዊ የሰላምና የልማት ሁኔታ ለማስረዳት መልካም አጋጣሚን ፈጥሮ ያለፈ መሆኑን የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አስታወቀ። ጉባኤውን ከአንድ ሺህ በላይ የአገር ውስጥና የውጭ ጋዜጠኞች ሽፋን እንደሰጡትም ተጠቁሟል።

36ኛውን የአፍሪካ ኅብረት የመሪዎች ጉባኤ አስመልክቶ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ቃል አቀባይ አምባሳደር መለስ አለም ለጋዜጠኞች እንደተናገሩት፤ የአፍሪካ ኅብረት ስብሰባ ስኬታማ በሆነ ሁኔታ ተጠናቋል። ኢትዮጵያ ደረጃውን የጠበቀ በቂ ዝግጅት አድርጋ እንግዶቿን በብቃትና በሰላም ተቀብላ በሰላምና በደስታ ሸኝታለች። ከተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ጠቅላላ ጉባኤ ጋር ተቀራራቢነት ባለው ደረጃ የተሳትፎና የመገናኛ ብዙኃን ሽፋን የነበረው ነው ብለዋል።

እንደ አምባሳደሩ ማብራሪያ፤ ጉባኤው ኢትዮጵያ ከጦርነት ዲፕሎማሲ ወደ ድህረ ሰላም ግንባታ ዲፕሎማሲ የገባችበት ነው። ከፈረንጆቹ አዲስ አመት ጀምሮ የሚሠሩ የዲፕሎማሲ ሥራዎች የማለዘብ፣ የማስገንዘብና የማብዛት ሥራ ላይ ያተኮሩ ናቸው፤ በዚህም ውጤት እየመጣ ነው።

በጉባኤው በርካታ የዲፕሎማሲ ሥራ በመሥራት ወዳጅ የማብዛትና ጠላት የመቀነስ ሥራ ተሠርቷል ያሉት አምባሳደሩ፤ የጎንዮሽ ውይይቶች ተደርገዋል፤ በዚህም ኢትዮጵያ ያለችበትን ወቅታዊ የሰላምና የልማት ሁኔታን ለማስረዳት መልካም አጋጣሚ ተፈጥሯል ብለዋል።

በጉባኤው 47 በሚሆኑ አጀንዳዎች ላይ ጥልቅ

ጉባኤው የኢትዮጵያን ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


ፎቶ - ፀሐይ ንጉሤ

አምባሳደር መለስ አለም









# ተወዳዳሪ ኢኮኖሚ ለመገንባት አምራች ኢንዱስትሪዎች በፋይናንስ መደገፍ አለባቸው


ፎቶ - ሃዲስ አብርሃ

አቶ መላኩ አለበል

**አዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ፡- ጤናማና ዘላቂነት ያለው ተወዳዳሪ ኢኮኖሚ ለመፍጠር አምራች ኢንዱስትሪዎች በፋይናንስ ተቋማት የብድር አቅርቦትና የተቀላጠፈ አሠራር መደገፍ እንዳለባቸው ተገለጸ።

የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር አምራች ኢንዱስትሪዎች እያጋጠማቸው ያሉ የፋይናንስ ችግሮችን ለመፍታት ከፋይናንስ ተቋማት ማለትም፣ ባንኮች፣ የብድር ተቋማት፣ የንግድና ማህበራት ዘርፍ፣ አገር አቀፍ የዘርፍ ማህበራትና ባለ ድርሻ አካላት ጋር ትናንት የውይይት መድረክ አካሂዷል።

በወቅቱም የኢንዱስትሪ ሚኒስትር አቶ መላኩ አለበል፤ የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ ለኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግር ትልቅ አስተዋጽኦ የሚያበረክቱ መሆናቸውን ጠቅሰው፤ ጤናማና ዘላቂነት ያለው ጠንካራና ተወዳዳሪ የሆነ አገራዊ ኢኮኖሚ ለመገንባት የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍን መደገፍና ማጠናከር ይገባል ብለዋል።

ባለፉት አራት ዓመታት የፋይናንስ ሴክተሮች በከፍተኛ ሁኔታ እየጨመሩና ተቀማጭ ገንዘባቸውም እያደገ፣ ተደራሽነታቸውም እየሰፋ ነው ያሉት ሚኒስትሩ፤ ተቋማቱ ለአምራች የኢንዱስትሪ ዘርፍ እያደረጉት ያለው ድጋፍ ውስንነት ያለበት መሆኑን ተናግረዋል።

አምራች ኢንዱስትሪው እያገኘ ያለው የፋይናንስ ድጋፍ 19 በመቶ ብቻ ሲሆን፤ ከዚህ ውስጥ ከፍተኛውን ድርሻ የሚወስደው ከልማት ባንክ የሚገኝ ድጋፍ እንደሆነ

ተወዳዳሪ ኢኮናሚ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



# የአፍሪካ ኅብረት

## ጉባኤ ለሆቴል ዘርፉ መነቃቃት ጉልህ አስተዋጽኦ እንደነበረው ተገለጸ

ገጽ 4






ገጽ 4

## ከአፍሪካ ነፃ ገበያ

ጀርባ ያሉ የነፃነት ተግዳሮቶች



# በተለያዩ አካባቢዎች ግጭት ሲከሰት ምልክት የሚሰጥ ቴክኖሎጂ ተግባራዊ ሊደረግ ነው

**አመለወርቅ ከበደ**

አዲስ አበባ፡- በተለያዩ የኢትዮጵያ አካባቢዎች ግጭት ሲከሰት ምልክት የሚሰጥ ቴክኖሎጂ ተግባራዊ ሊደረግ መሆኑን የሰላም ሚኒስቴር አስታወቀ። ቅድመ ግጭትን በመከላከል ረገድ ከክልሎች ጋር በቅንጅት እየተሠራ መሆኑ ተጠቁሟል።

በሰላም ሚኒስቴር የግጭት ማስጠንቀቂያና ምላሽ ዴስክ ኃላፊ አቶ ሺ‚ጋዝ ዳኒ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ከክልሎች የሚመጡ መረጃዎችን ሳይንሳዊ እንዲሆኑ በዘመናዊና በተደራጀ መልክ ለመቀበልና ለመሥራት እንዲያስችል በቴክኖሎጂ የታገዘ ‹‹ሲዋር ሲስተም›› የሚባል አሠራርን በሁሉም ክልል ለመዘርጋት ታቅዶ እየተሠራ ይገኛል።

በቴክኖሎጂው መሠረት የመረጃ ተቆጣጣሪዎች በፌዴራልም ሆነ፣ በክልል ደረጃ የሚያገኙትን መረጃ ወደ መረጃ ሥርዓቱ ያስገባሉ። በዚህም ቴክኖሎጂው የፀጥታ ችግር ሲኖር ቀይ ቀለም ያሳያል ብለዋል።

የተፈጠረው ችግር በተወሰነ መልኩ ሲፈታ ቢጫ ቀልም ያሳያል። ችግሩ ሙሉ በሙሉ ሲፈታ አረንጓዴ ቀለም ያሳያል፤ ይህ ካልሆነ ግን የአደጋ ምልክቱን እንዳሳየ የተለያዩ አማራጮች እንዲወሰዱ የሚያሳስብ መልዕክት ያሳያል ሲሉ አስረድተዋል።

አቶ ሺ‚ጋዝ እንደገለጹት፤ ሰላም ሚኒስቴር መረጃዎችን ሳይንሳዊ በሆነ መልኩ የሚያደራጅበትን አሠራር በመዘርጋት ከአገሪቱ ክፍሎች የሚመጡ ግጭትና የጸጥታ ችግሮችን የተመለከቱ መረጃዎች ተንትኖ ለሚመለከተው አካል ያሳውቃል።



**አቶ ሺጋዝ ዳኒ**

‹‹ሲዋር ሲስተም›› የተሰኘው ቴክኖሎጂ በ2010 ዓ.ም መረጃዎችን ሳይንሳዊ አድርጎ ለመሥራት ታስቦ በሦስት የተለያዩ ክልሎች፣ በአምስት ዞኖችና በ60 ወረዳዎች ላይ የተጀመረ ቢሆንም ባጋጠመው የበጀት እጥረት መቀጠል ባለመቻሉ ተቋርጦ መቆየቱን አስታውቀዋል።

አሁን ላይ አሠራሩ በሁሉም የኢትዮጵያ ክፍሎች ተግባራዊ እንዲደረግ ፕሮጀክት ተቀርጾ እየተሠራ መሆኑን የጠቆሙት አቶ ሺ‚ጋዝ፤ የበጀቱን ችግር በመፍታት በሁሉም ክልሎች ሥራው እንዲጀመር ጥረት እየተደረገ መሆኑን አስረድተዋል።

በቴክኖሎጂ የታገዘውን አሠራር በተለያዩ የዓለም አገራት ሲጠቀሙት መቆየታቸውን አስታውሰው፤ አሠራሩ የተሻለ ውጤት ያመጣላቸው አገራት ልምድ መታየቱን ገልጸዋል።

ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ቅድመ ግጭትን የመከላከል ሥራዎችን በተሻለ ቅንጅት ለማከናወን ከክልሎች ጋር የተለያዩ ሥራዎችን እያከናወነ ይገኛል ብለዋል።

መረጃን ለመከታተል የሚረዳ የመረጃ ዴስክ ክፍል አለ፤ ክፍሉ በእያንዳንዱ ቀናት ግጭት አመላካች ጉዳዮችን በሁኔታና በክስተት ለይቶ መረጃዎችን ያደራጃል። መረጃ ክፍሉ ጉዳዮቹን በመተንተን ለሚመለከተው የበላይ አካል እንደሚያቀርብ አቶ ሺ‚ጋዝ አስታውቀዋል።

የበላይ አካላት አስጊ ነገሮች ሲገኙ ችግሮቹ በፍጥነት እንዲፈቱ ለየክልሎቹ መልዕክት ያስተላልፋሉ። አልፎ አልፎ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በእራሱ አቅም ብቻ መፍታት የሚችላቸው ጉዳዮች ሲኖሩ የሚያስተካክልበት አሠራርም አለው ሲሉ ተናግረዋል።

በዚህ አሠራር ከጥምቀት በዓል አከባበር ጋር በተገናኘ ቅድመ ግጭት መከላከል ላይ መሠረት ያደረጉ መረጃዎችን ከኦሮሚያ ክልል ጋር በመለዋወጥ ችግሩ በአፋጣኝ እንዲፈታ የተደረገበትና በዓሉ በሰላም እንዲጠናቀቅ የተደረገበት አግባብ መኖሩን አንስተዋል።

አቶ ሺ‚ጋዝ እንዳስታወቁት፤ በቀጣይም ከክልሎች ጋር ያለውን ቅንጅታዊ አሠራር በማጠናከር ቅድመ ግጭት መረጃ ልውውጥና ትንተና ሥራዎች ላይ ትኩረት ያደረገ ሥራ ይከናወናል።

# ጉለሌ ክፍለከተማ የትምህርት ጥራትን ለማሻሻል የሚያስችሉ መርሐግብሮችን ቀርጾ እየሠራ ነው

**መክሊት ወንድወሰን**

አዲስ አበባ፡- በጉለሌ ክፍለ ከተማ ባሉ ትምህርት ቤቶች የተማሪዎችን ውጤት ለማሻሻል የጥናት መርሐ ግብሮችን በመቅረጽ እና የትምህርት ቤት አገልግሎት አሰጣጦችን በማሻሻል እየሠሩ መሆኑ ተገለጸ። የሕፃናት፤ የሴቶች እና የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች የሚያጋጥሟቸውን ተግዳሮቶችን ለማስወገድም ጥረት እየተደረገ ነው።

የጉለሌ ክፍለ ከተማ ትምህርት ጽሕፈት ቤት ኃላፊ አቶ ሚሊዮን ኮራ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፣ በክፍለ ከተማው የተለያዩ ትምህርት ቤቶች የጥናት መርሐ ግብሮች ተጀምረዋል ሲሉ ተናግረዋል።

የተማሪዎችን ውጤት እና ሥነ ምግባር ለማሻሻል ታልሞ የጥናት መርሐ ግብሮች በ23 አንደኛ ደረጃ እና በሰባት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እየተሰጡ መሆኑን ተናግረዋል። የትምህርት ጽሕፈት ቤቱም የተማሪዎች ውጤት መሻሻል ላይ በትኩረት እየሠራ መሆኑን አስታውቀዋል።

በጉለሌ ክፍለ ከተማ የወረዳ ሰባት ትምህርት ጽሕፈት ቤት ኃላፊ አቶ አድማሱ ደምሴ በበኩላቸው ወረዳው ውስጥ ከሚገኙ ግብረሰናይ ድርጅቶች ጋር በመተባበርም የትምህርት ቤቶች ቤተ መጽሐፍትን ለማሻሻል ሥራዎች እየተሠሩ እንዳሉ አብራርተዋል።

እንደ አቶ አድማሱ ገለጻ ሴቶች፤ አካል ጉዳተኞችንና ሕፃናትን በሚመለከትም የአቅም ማሻሻያ እና ተጠቃሚ ሊያደርጓቸው የሚችሉ ፕሮግራሞች ተቀርጸው ሥራዎች እየተሠሩ ይገኛሉ።

በሌላ በኩል በክፍለከተማው የትምህርት ሥርዓቱን ለማገዝ የሚያስችሉ የተለያዩ ሥራዎች እየተከናወኑ መሆኑን የሸገር ሕፃናት እና ቤተሰብ ልማት ዋና ሥራ አስፈጻሚ ተናግረዋል።

ዋና ሥራ አስፈጻሚው አቶ ሲሳይ አለማየሁ እንደተናገሩት፤ በሦስት ቅድመ መደበኛና አንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች እና አንድ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ



6 ሺ 200 ተማሪዎችን ተጠቃሚ የሚያደርጉ 4 ባለ 12 ቧንቧ የእጅ መታጠቢያ ጣቢያዎች እና አራት የውሃ ማጠራቀሚያ ታንከሮች ከነውሃ ፓምፖቻቸው የተገነቡ ሲሆን የፕሮጀክቱ አጠቃላይ ወጪም አምስት መቶ ሰማንያ አምስት ሺህ ብር ነው።


ሥራ አስፈጻሚው እንደገለጹት፤ አንድ ባለ አራት መቀመጫ የሴቶች መፀዳጃ እና የንጽህና መጠበቂያ መቀየሪያ ቤቶች እንደተገነቡም አያይዘው ገልጸዋል። መጸዳጃ ቤቶቹም አካል ጉዳተኛ ተማሪዎችን ጭምር ታሳቢ ያደረጉ ናቸው።

የአጼ ልብነድንግል የመጀመሪያና ቅደመ መደበኛ ርዕሰ መምህርት ወይዘሮ ነፃነት መኮንን እንደገለጹት፣ በትምህርት ቤታቸው ከወረዳው የትምህርት ጽሕፈት ቤት እና ከአጋር ግብረ ሰናይ ድርጅቶች ጋር በመሆን የጥናት ፕሮግራሞችን በትምህርት ቤቱ በማስጀመር የተማሪዎች ውጤት ለማሻሻል እየሠሩ ይገኛሉ። በተጨማሪም የሴቶች ንጽህና መጠበቂያ ለሴት ተማሪዎች በማዳረስ ተማሪዎቹን ለመጥቀም ተችሏል።

የድል በር ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪ የሆነችው ኤደን ብርቁ እንደተናገረችው፣ ከዚህ ቀደም በትምህርት ቤቱ የመጸዳጃ ቤት ችግር መኖሩን ተናግራ፤ አሁን ላይ የተገነቡት የመጸዳጃ ቤቶች ችግሩን እንደሚቀርፉ አብራርታለች። በትምህርት ቤቱም በሥርዓተ ጾታ በኩል ሴቶችን ለማብቃት የተለያዩ የአቻ ለአቻ ስልጠናዎች እየተሰጡ መሆኑን አብራርታለች።

በብርሃነ ህሊና የቅድመ መደበኛና አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ምክትል ርዕሰ መምህር የሆኑት አቶ ፋንታሁን አማና በበኩላቸው በትምህርት ቤቱ ውሃ አቅርቦት ችግር እንደነበረ ገልጸዋል። አሁን ላይ የተገነቡት የውሃ ቧንቧዎች የነበረውን ችግር እንደሚቀርፉና ተማሪዎች ለትምህርታቸው ትኩረት እንዲሰጡ እንደሚያበረታታ ተናግረዋል።

በዕለቱም በክፍለከተማው በሚገኙ አራት ትምህርት ቤቶች፤ በድጋፍ የተሠሩ የሴት እና የአካል ጉዳተኞች መጸዳጃ ቤቶች እና የመጠጥ ውሃ አቅርቦቶችን ለማስፋት የተሠሩ ፕሮጀክቶች በወረዳው የትምህርት ጽሕፈት ቤት ኃላፊዎች እና ርዕሰ መምህራን ተመርቆ ወደ ሥራ ገብቷል።



# 500 ሺህ የቁርአን ኮፒዎችን ለማሰባሰብ ታቅዷል

**ማህሌት ብዙነህ**

አዲስ አበባ፡- የአዲስ አበባ ከተማ እስልምና ጉዳዮች ከፍተኛ ምክር ቤት ከኑር የቁርአን ባንክ ጋር በተመባበር ከየካቲት 15 ቀን 2015 ዓ.ም ጀምሮ ለመጪው ረመዳን ተደራሽ የሚሆን 500 ሺ የቁርአን ኮፒዎችን ለማሰባሰብ ማቀዱን አስታወቀ።

የአዲስ አበባ ከተማ እስልምና ጉዳዮች ከፍተኛ ምክር ቤት ከኑር የቁርአን ባንክ ጋር በትናንትናው ዕለት በሰጡት የጋራ መግለጫ፤ የዘንድሮን የረመዳን ወር ምክንያት በማድረግ የቁርአን እጥረቱን ለመቅረፍ 500ሺ የቁርአን ኮፒዎችን በመሰብሰብ ተደራሽ ለማድረግ እየተሠራ ነው።

የአዲስ አበባ ከተማ እስልምና ጉዳዮች ከፍተኛ ምክር ቤት ዋና ጸሐፊ ሼህ ሁሴን በሽር በመግለጫው ላይ እንደተናገሩት፤ የአዲስ አበባ ከተማ እስልምና ጉዳዮች ከፍተኛ ምክር ቤት ሃይማኖታዊ፣ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ኃላፊነቱን ለመወጣት የሚያስችለውን መዋቅር መተግበር ከጀመረ ወራትን አስቆጥሯል። በአሁኑ ጊዜም የረመዳን ወርን መነሻ በማድረግ ያለውን የቁርአን ፍላጎት እና አቅርቦት ለማመጣጠን በትኩረት እየሠራ ይገኛል።

ይህንን ቁርአን የማሰባሰብ ሥራ ላይ በከተማው ከፍተኛ ምክር ቤት የተዋቀሩ የክፍለ ከተማ፣ የወረዳ የመስጂድ አደረጃጀቶች የሚሳተፉ መሆኑን ገልጸው፤ ከየካቲት 15 ቀን 2015 ዓ.ም ጀምሮ በመላው አዲስ አበባ በሚገኙ ከ360 በላይ በሚሆኑ መስጂዶች ቁርአንን የማሰባሰብ ሥራ እንደሚሠራ ተናግረዋል።

ሼህ ሁሴን መጪው የረመዳን ወር ቁርአን በከፍተኛ ሁኔታ የሚፈለግበት ወር በመሆኑ ሙስሊም ማኅበረሰብ ይህንን የፍላጎት እና የአቅርቦት አለመጣጣም ከግምት ውስጥ በማስገባት ለሚከናወነው የመፍትሄ ማፈላለግ ሥራ የበኩሉን ድርሻ እንዲወጣ ይጠበቃል ብለዋል። ምክር ቤቱም ትኩረት በመስጠት የቅርብ ክትትል የሚያደርግበት መሆኑንም ተናግረዋል።

የኑር የቁርአን ባንክ ምክትል ሥራ አስኪያጅ አቶ አባስ በያል እንደገለጹት፤ በአገሪቱ በሚገኙ መስጂዶች፣ሐሪማዎች፣ ዛዊያዎችና መድረሳዎች የቁርአን ኮፒዎች እጥረትን ለመቅረፍ አላማ አድርጎ የሚሠራ ነው፤ እስካሁንም በጥቅሉ ከ165 ሺህ 237 በላይ የቁርአን ኮፒዎችን ማሰራጨት ችሏል።

ይህ የቁርአን ማሰባሰብ መርሀ ግብር ከአዲስ አበባ ከተማ እስልምና ጉዳዮች ከፍተኛ ምክር ቤት ጋር በመተባበር ለአንድ ወር ከአስራ አምስት ቀን የሚቆይ መሆኑን አመልክተው 500 ሺ የቁርአን ኮፒዎችን ከአዲስ አበባ ከተማ እና ከአጎራባች ከተሞች ከሚገኙ የሙስሊም ማህበረሰብ አባላት የማሰባሰብ ሥራ ይሠራል ብለዋል።

ይህም በመላው ኢትዮጵያውያን ለሚገኙ ቁርአን ላልተዳረሰባቸው ገጠራማ አካባቢዎች ለማከፋፈልና ተደራሽ ለማድረግ እንደሚረዳ አቶ አባስ ተናግረዋል።

መላው የአዲስ አበባ ሙስሊም ነዋሪዎች እንዲሁም በአጎራባች ከተሞች ነዋሪ የሆኑ የሙስሊም ወገኖች እንዲሳተፉም ጥሪ አቅርበዋል።

ዜና

# በስድስት ወራት ከሁለት ሚሊዮን ሄክታር በላይ መሬት በደን ተሸፍኗል

**አማን ረሺድ**

አዲስ አበባ፡- ባለፉት ስድስት ወራት በተፋሰስ ልማት ከሁለት ሚሊዮን ሄክታር በላይ መሬት በደን መሸፈኑን የግብርና ሚኒስቴር አስታወቀ።

በግብርና ሚኒስቴር የተፈጥሮ ሀብት ዘርፍ ሚኒስቴር ዴኤታ ፕሮፌሰር እያሱ ኤልያስ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ እንደ አገር በ2015 በጀት ዓመት በተፋሰስ ልማት አምስት ሚሊዮን ሄክታር መሬት በደን ለመሸፈን የታቀደ ሲሆን ባለፉት ስድስት ወራት ከሁለት ሚሊዮን ሄክታር በላይ መሬት በደን ተሸፍኗል።

በተፋሰስ ልማት አርሶ አደሮች በየአካባቢው የተጎዱ ተፋሰሶችን መልሰው እንዲያገግሙ የማድረግ ሥራ በስፋት እየሠሩ መሆኑን ፕሮፌሰር እያሱ ተናግረዋል።

በደን ልማቱ ሂደት ሥነምህዳሩን የመጠበቅ ሥራ ቁልፍ ቦታ እንደተሰጠው ጠቅሰው፤ ከተፋሰስ ልማት ሥራ ጎን ለጎን ለኅብረተሰቡ ጥቅም የሚሰጡ ለእንስሳት መኖና ለምግብ ፍጆታ ችግኞችን መተከላቸውን አስታውቀዋል።

በተጨማሪም አንድ ነጥብ አምስት ሚሊዮን ሄክታር መሬት ላይ የተተከሉ ችግኞች ከሰውና ከእንስሳት ንክኪ ነፃ ሆነው እንዲጠበቁ ለማድረግ ታቅዶ በአጠቃላይ ከሁለት ሚሊዮን ሄክታር መሬት በላይ የደን ልማት ጥበቃ ሥራ ተከናውኗል ብለዋል።

በአጠቃላይ በተለያዩ አካባቢዎች ላይ የደን ችግኞችን የማልማትና የመጠበቅ ባህሉ እያደገ መሆኑን ገልጸው፤ ኅብረተሰቡ የተፋሰስ ልማቱን በእኔነት ስሜት የሚመራበት ሥርዓት መፈጠሩን አስረድተዋል።

የተፋሰስ ልማት ተጠቃሚ ኅብረት ሥራ ማህበራትን በማደራጀት የለሙ ተፋሰሶችን በዘላቂነት እንዲጠቀሙ እየተደረገ ይገኛል ሲሉ ገልጸዋል።

የደን ልማቱ በዋናነት የአካባቢ አየር ንብረት ለውጥን ከመከላከል ባለፈ ለግብርና ሥራዎች ምርታማነት ጉልህ አስተዋጽኦ ያደርጋል። ይህን የተረዳው ማህበረሰቡ የደን ልማት ሥራዎች ላይ በንቃት የሚሳተፍበትን መንገድ እንዲያሳድግ የሚረዱ ሥራዎች በቀጣይም ይከናወናሉ ብለዋል።



ፕሮፌሰር እያሱ ኤልያስ

ከዚህ ጋር በተያያዘ በአሁኑ ወቅት ሰባት ሚሊዮን ሄክታር መሬት በአፈር አሲዳማነት የተጠቃ ሲሆን፤ ከዚህ ውስጥ ሦስት ሚሊዮን ሄክታር መሬቱ የአሲዳማነት ደረጃ ከፍተኛ መሆኑን ፕሮፌሰር እያሱ አስታውቀዋል።

የአሲዳማነት ችግሩን በኖራ የማከም አሠራር ተግባራዊ ቢደረግም የኖራ አቅርቦት እጥረት ችግር መሆኑን ጠቁመዋል።

የአፈርን ለምነትና ጤንነት የማስጠበቅ ሥራ ብዙ የሚጠበቅ መሆኑን የገለጹት ፕሮፌሰር እያሱ የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ሥራው በአገራዊ ንቅናቄ እንዲሁም የፖለቲካ አመራሩን በማሳተፍ መሥራት እንደሚያስፈልግ አስረድተዋል።

ከተግዳሮቶቹ ውስጥ በተለይ ትርፍ አምራች ከሚባሉት ክልሎች በምዕራብ አማራ፣ በአብዛኛው ኦሮሚያ፣ ሲዳማ፣ ደቡብና ደቡብ ምዕራብ አካባቢዎች የአፈር ሆምጣጤነት በከፍተኛ ደረጃ እየተስፋፋ መሆኑን ጠቁመዋል።

የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ሥራው በተለይ ከአየር ለውጥና ከኢኮኖሚ አንፃር አወንታዊ ሚናው የጎላ መሆኑን የገለጹት ፕሮፌሰር እያሱ አየር ለውጥ በዋናነት የሚከሰተው የደኖች መመናመንና የአፈር መከላት በሚኖርበት ጊዜ ሲሆን አፈር ደግሞ የካርበን ትልቁ ጎተራ ነው ብለዋል።

የአፈር መከላት በሚኖርበት ጊዜ በአፈር ውስጥ የሚኖረው ካርበን ወደአየር ውስጥ ይለቀቃል፤ ደኖች ደግሞ የሚለቀቀውን ካርበን የሚቀንሱ ናቸው፤ ነገር ግን ደኖች በሚጨፈጨፉበት ጊዜ የአየር ንብረት ለውጥ እንዲፈጠርና እንድንጎዳ ያደርጋሉ ሲሉም አስረድተዋል።

ፕሮፌሰር እያሱ እንደገለጹት፤ እኛ የምንጎዳው በዋናነት በዝናብ እጥረት ሲሆን በዚህም የደቡብ ኦሞና የሱማሌ ክልል አካባቢዎችን ብዙውን ጊዜ ድርቅ ተከስቶ ይገኛል፤ ከዚህ ጋር ተያይዞ ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ ምክንያት በጎርፍ ይገጥማቸዋል።

ይህን ችግር ለመመከት ደኖችን መትከል እንዲሁም የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃን ማስፋፋት ጠቀሜታው የጎላ ሲሆን በተጨማሪም ይህን ስናደርግ ከተፈጥሮ ጋር የታረቀች አገር መገንባት እንችላለን ብለዋል።

# ዩኒቨርሲቲዎቹ ተማሪዎችን ለመቀበል ዝግጁ መሆናቸውን አስታወቁ

**ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ፡- አርባ ምንጭ፣ ባህርዳርና ወልድያ ዩኒቨርሲቲዎች በትምህርት ሚኒስቴር የተመደቡላቸውን አዲስ ተማሪዎች ለመቀበል ቅድመ ዝግጅታቸውን ማጠናቀቃቸውን አስታወቁ።

የአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ የአካዳሚክ ጉዳዮች ምክትል ፕሬዚዳንት ዶክተር አለማየሁ ጩፋሞ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ትምህርት ሚኒስቴር በወሰነው መሠረት 1ሺህ 452 ተማሪዎች በአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ በመመደባቸው ተማሪዎቹን ለመቀበል በቂ ዝግጅት ተደርጓል።

ዩኒቨርሲቲው ለተማሪዎቹ የሚያስፈልጋቸውን ቅድመ ዝግጅቶች በማጠናቀቁ በሚቀጥለው ሳምንት ተማሪዎቹን ለመቀበል ጥሪ እንደሚያደርግ አስታውቀዋል።

ከተለያዩ አካባቢዎች የሚመጡ ተማሪዎች በዋናው ካምፓስ አርፈው ወደ ተመደቡበት ካምፓስ እንዲጓጓዙ ይደረጋል። ለዚህም የትራንስፖርት አገልግሎት ተዘጋጅቷል ብለዋል።

ተማሪዎቹ ወደ ተመደቡበት ካምፓስ ሲገቡ የተማሪዎች ህብረት ፕሬዚዳንቶች በተገኙበት የማስተባበር ሥራ እንደሚያከናውኑ ጠቁመዋል።

ዩኒቨርሲቲው በ2014 ዓ.ም የትምህርት ዘመን 3ሺህ 100 ተማሪዎችን የመቀበል አቅም እንደነበረው ዶክተር አለማየሁ ጠቁመው፤ በ2015 ዓ.ም ላይ ከነበረው አቅም አንጻር ግማሽ ያህሉ ብቻ እንደተመደቡለት ጠቁመዋል።

በቀጣይ የአቅም ማሻሻያ የሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች በተጨማሪነት እንደሚመደቡ ታሳቢ ሲደረግ በሙሉ አቅማችን የመማር ማስተማር ሥራውን እንደምናከናውን ይታመናል ብለዋል።

የባህርዳር ዩኒቨርሲቲ የተማሪዎች ህብረት ፕሬዚዳንት ተማሪ ጥበቡ ሰለሞን በበኩሉ እንደገለጸው፤ በዩኒቨርሲቲው ከአንድ ዓመት በላይ የቆዩ ተማሪዎች አዲስ የሚገቡትን ተማሪዎች ወደግቢው ሲመጡ መልካም አቀባበል እንዲያደርጉ የሚያስችል ዝግጅት ተከናውኗል።

የዩኒቨርሲቲ አመራሮች፣ የተማሪዎች ህብረት፣ የመኪና ስምሪቶች፣ የአስተዳደር አካላትና የከተማ ወጣቶች ያሉበት ጊዜያዊ ኮሚቴ ተቋቁሞ ተማሪዎችን ለመቀበል አስፈላጊው ቀድመ ዝግጅት ሁሉ ተጠናቋል ብሏል።

ተማሪዎቹ ጥሪ ተደርጎላቸው ወደባህርዳር በሚመጡበት ወቅት በሦስት ፌርማታዎች ላይ በመቀበል ወደተመደቡበት ጊሽ ዓባይና ዘንዘልማ ካምፓስ የማድረስ ሥራ ይከናወናል። ከምዝገባ ጀምሮ ማንኛውንም አገልግሎት እንዲያገኙ ከዩኒቨርሲቲው አስተዳደር በተጓዳኝ የተማሪዎች ህብረት እገዛ ያደርጋል ሲል ተናግሯል።

ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ በ2014 ዓ.ም የትምህርት ዘመን በአገር አቀፍ ደረጃ የዩኒቨርሲቲ መግቢያ ፈተና ወስደው ከ50 በመቶ በላይ ውጤት ያስመዘገቡ 5 ሺህ 187 ተማሪዎችን ከየካቲት 20 እስከ የካቲት 22 ቀን 2015 ዓ.ም እንደሚቀበል አስታውቋል።


የወልድያ ዩኒቨርሲቲ የኮሚኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክተር አቶ ተፈራ አስናቀ በበኩላቸው እንደገለጹት፤ በ2014 ዓ.ም የ12ኛ ክፍል አገር አቀፍ ፈተና ከ50 በመቶ በታች ውጤት ላመጡ ተፈታኞች ለመጀመሪያ ጊዜ የሚሰጠው የአቅም ማሻሻያ (ሬሚዲያል) ትምህርት ፕሮግራም በዩኒቨርሲቲው ይሰጣል።

ዩኒቨርሲቲው የሚመደቡለትን ተማሪዎች ለመቀበል የሚረዱ የማደሪያ፣ የመመገቢያ ስፍራና መማሪያ ክፍሎችን እንዲሁም ሌሎች ዝግጅት አጠናቋል ያሉት አቶ ተፈራ፤ የአቅም ማሻሻያ የሚማሩ 3 ሺህ ተማሪዎችን የመቀበል አቅም እንዳለው ገልጸዋል።

ዩኒቨርሲቲው እንደከዚህ ቀደሙ ሁሉ አዲስ ተማሪዎችን በሚቀበልበት ወቅት ኮሚቴ በማቋቋም ከከተማው አስተዳደር አካላት ጀምሮ መላው ኅብረተሰብ ተገቢውን አገልግሎት እንዲያቀርብላቸው የሚያግዝ ሥራ ይከናወናል ብለዋል።

በትምህርት ሚኒስቴር የሚመደቡልንን ተማሪዎች ምን ያክል እንደሆኑ እስካሁን ባይታወቅም፤ በቀጣይ እንደታወቀ ተማሪዎች የሚገቡበትን ቀን በማስታወቂያ ይገለጻል ሲሉ አቶ ተፈራ አስታውቀዋል።

በአገር አቀፍ ደረጃ የዩኒቨርሲቲ መግቢያ ፈተና ወስደው ከ50 በመቶ በላይ ውጤት ያስመዘገቡ ተማሪዎች በተመረጡ 11 ዩኒቨርሲቲዎች እንደሚማሩ ትምህርት ሚኒስትር ማስታወቁ የሚታወስ ነው። በተጨማሪ የአቅም ማሻሻያ የሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች ደግሞ በተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች የሚመደቡ ይሆናል።



ፎቶ - ሃዲስ አብርሃ

# የፊታውራሪ ሃብተጊዮርጊስ ዲነግዴ መኖሪያ ቤት የነበረው ታሪካዊ ቅርስ ዕድሳት ተጠናቆ ተመረቀ

**በሪሁ አረጋ**

አዲስ አበባ፡- የአሜሪካ ኤምባሲ ከዓለም ቅርሶች ፈንድ ጋር በመተባበር በአሜሪካ ግቢ የሚገኘውን በፊታውራሪ ሃብተጊዮርጊስ ዲነግዴ የታነፀ ታሪካዊ ሕንፃ አድሶ አስመረቀ።

በኢትዮጵያ የአሜሪካ ኤምባሲ ተወካይ አምባሳደር ትሬስይ ጃኮብሰን በምርቃ ሥነ-ሥርዓቱ ላይ እንደተናገሩት፤ የአሜሪካ ኤምባሲ ከዓለም ቅርሶች ፈንድ ጋር በመተባበር ታሪካዊ ቅርሱን የማደስ ሥራ አጠናቆ አስመርቋል።

ኤምባሲው ለቅርሱ እድሳት ሥራ ለዓለም ቅርሶች ፈንድ 240 ሺህ ዶላር ድጋፍ ማድረጉን የገለፁት አምባሳደሯ፤ አሜሪካን ግቢ የሚገኘው ይህ ቅርስ ፊታውራሪ ሃብተጊዮርጊስ ዲነግዴ አንፀው ይኖሩበት እንደነበርና በ1930 ዎቹም የአሜሪካ ኤምባሲ ቆንፅላ ጽሕፈት ቤት ሆኖ ያገለገለ ሲሆን በኋላም የየመን ኮሚኒቲ ትምህርት ቤት ሆኖ ያገለግል እንደነበርም ገልፀዋል።

የዓለም ቅርሶች ፈንድ የቅርሱ ጥገና ዋና አርክቴክት ፍቅረሥላሴ ስፍር ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለፁት፤ ቅርሱን ለማደስ በታሰበበት ወቅት የየመን ኮሚኒቲ ትምህርት ቤት እንደነበርና ከሁለት ዓመት በላይ አገልግሎት አቋርጦ እንደ ዕቃ መደብር ሲያገለግል ቆይቷል።

ሕንፃው በተለይ የጣሪያው ክፍል ከፍተኛ ጉዳት ደርሶበት እንደነበር የገለፁት አርክቴክት ፍቅረሥላሴ፤ ጣሪያውን እንደ አዲስ በመሥራት ኮርኒሱን በማስተካከል የቀለምና ሌላ የማደስ ሥራዎች መሠራታቸውን አብራርተዋል። የ16 ወር ጊዜ የፈጀ የእድሳት ሥራ እንደተሠራም ገልፀዋል።

የእድሳት ሥራው የሚመራው በዓለም ቅርሶች ፈንድ መሆኑንና የቁጥጥር ሥራውም በራሱ እንደተሠራ የተናገሩት አርክቴክቱ፤ በሥራው የአሜሪካ መንግሥት ድጋፍ አድርጓል ብለዋል።

የእድሳት ሥራውን የአዲስ አበባ ባህልና ቱሪዝም ቅርስ ጥናትና ጥበቃ ቢሮ እና የመርካቶ ከተማ ወረዳ አንድ የባህልና ቱሪዝም ቢሮ በጋራ ማከናወናቸውንም ጠቅሰዋል።

ዜና

# ከአፍሪካ ነፃ ገበያ ጀርባ ያሉ የነፃነት ተግዳሮቶች

**ዋቅሹም ፍቃዱ**

የአፍሪካ መሪዎች በአህጉሪቱ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ትኩረት በማድረግ ችግሮቻቸውን ለመፍታት ጥረት ማድረግ ከጀመሩ እነሆ ከስድስት አስርት አመታት በላይ ጊዜያት ተቆጥረዋል። ነገር ግን ችግሮቻቸውን ለመፍታት ያደረጓቸው ጥረቶች በተለያዩ ምክንያቶች የሚጠበቀውን ያህል ውጤት አላመጡም በሚል ትችቶችም ይቀርቡበታል። በዚህም የተነሳ አህጉሪቱ ዛሬም በድህነት ተምሳሌትነቷ ትጠቀሳለች።

ዘንድሮም 36ኛው የመሪዎች ጉባኤ «የአፍሪካ ነፃ የንግድ ቀጣና ስምምነት ትግበራን ማፋጠን» በሚል መሪ ሃሳብ ከየካቲት 11- እስከ 12 በአዲስ አበባ ተካሂዷል። ለመሆኑ የዘንድሮ መሪ ሃሳብ ለአፍሪካ ምን ትርጉም ይኖረዋል? አፍሪካስ ከኢኮኖሚ ጥገኝነት ለመውጣት በቀጣይ ምን መልካም አጋጣሚዎችና ፈተናዎች አሉባት?

የምጣኔ ሀብት ባለሙያው ዶክተር ጉቱ ቴሶ እንደሚሉት የዛሬ ስምንት ዓመት ገደማ የአፍሪካ መሪዎች ጉባዔ መሪ ቃል በምግብ ራስን መቻል መሆኑ ለብዙ አፍሪካውያን ትልቅ ተስፋ የሰጠ ነበር። ከዚህ ቀደም እንደ አፍሪካ አስከፊ ረሃብ ውስጥ የነበሩ እንደ ደቡብ ኤሲያ፤ ኤሲያን ፓስፊክና ላቲን አሜሪካ ያሉ አገራት ቃል በተግባር ቀይረው ተግተው በመሥራታቸው ከድህነት ተላቅቀዋል። በአፍሪካ የዳቦ ጥያቄ እስካሁን ትልቁ አጀንዳ ነው። አሁን ባለው ነባራዊ ሁኔታ በምግብ እጥረት ከድህነት ወለል በታች ያለችው አህጉር አፍሪካ ብቻ ነች።

በሩሲያና ዩክሬን ጦርነት ሳቢያ ወደ ተለያዩ የዓለም አገራት የሚላኩ የምግብ እህሎች መታገዳቸው እና የዓለም ኢኮኖሚን በእጅጉ የጎዳው የኮሮና ቫይረስ ወረርሽኝ መከሰት አህጉሪቱን ይበልጥ የድህነት ተጋላጭ አድርጓታል።

የነፃ ንግድ ቀጣና ዙሪያ በአህጉረ አፍሪካ ብዙ ተሞክሮዎች ቢኖሩም ነገር ግን በተጋረጠባቸው አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ ተጽእኖዎች የጨነገፉ መሆናቸውን ያነሱት የምጣኔ ሀብት ባለሙያው፤ ከዚህ አንጻር በአህጉሪቱ 30 ዓመታትን ያስቆጠሩ ነገር ግን ተጨባጭ ለውጥ ያላመጡ የምሥራቅና ምዕራብ አፍሪካ አገራት ነፃ የጋራ ንግድ (ኮሜሳ)፣ የደቡብ አፍሪካ አገራት ነፃ የጋራ ንግድ (ሳዳክ)፣ የምሥራቅ አፍሪካ አገራት ነፃ የጋራ ንግድ(ኢአክ) እና ሰሜን አፍሪካ የመግሪብ ዓረብ ሕብረት ነፃ የጋራ ንግድ መኖራቸውን አብራርተዋል። በአንጻሩ የምሥራቅና ምዕራብ አፍሪካ አገራት ነፃ የጋራ ንግድ (ኮሜሳ) የለውጥ ጎዳና ላይ መሆኑንም አልሸሸጉም።

እንደ ዶክተር ጉቱ ማብራሪያ፣ ነፃ የንግድ እንቅስቃሴዎቹ ተጨባጭ ለውጥ ያላመጡበት ምክንያት በቀጣናው መሪዎች መካከል ፍጹም መተማመን አለመኖር እና የፖለቲካ አለመግባባቶች ትልቁ አህጉራዊ ችግር ነው። በብዙ አፍሪካ አገራት መካከል መልካም ጉርብትናንና አብረው ሠርተው መለወጥን የሚያበላሹ የድንበር ውዝግቦች ዛሬም እንደቀጠሉ ናቸው። የአህጉሪቱ የፖለቲካ አለመረጋጋት ነፃ ንግዱ በነፃነት እንዳይካሄድ እንቅፋት ሆኖበታል።

በሌላ በኩል ደግሞ አፍሪካውያንን በብዙ መልኩ የሚደግፉ ሀብታም አገራት በአፍሪካውያን መካከል ነፃ ንግድ እንዲካሄድ ፍላጎት የላቸውም ያሉት የምጣኔ ሀብት ባለሙያው፤ ለዘመናት ጥሬ ዕቃን በትንሽ ዋጋ ከአፍሪካ በመግዛት በቴክኖሎጂ እሴት ጨምረው ወደ አፍሪካ በመላክ የሚያገኙትን ገቢ ስለሚጎዳባቸው አፍሪካውያን እርስበርሳቸው እንዲገበያዩ አይፈልጉም። በአህጉረ አፍሪካ የሚደረጉ ማናቸውም የልማት ሥራዎች ከሀብታም አገራት ድጋፍ የጸዳ ስለማይሆን ከዚህ አንጻር የነፃ ገበያው እንቅስቃሴ ነፃነቱ ያጠራጥራል ነው ያሉት።

ምቹ የንግድ ቀጣናዎችን ያለማበጀት፣ ውጤታማ የነፃ ንግድ ስትራቴጂዎችን ያለመንደፍና የመረጃ ፍሰት ነፃነት ያለመኖር ለነፃ የንግድ እንቅስቃሴ ማነቆዎች ናቸው የሚሉት ዶክተር ጉቱ፣ በመሆኑም በአንድ ጊዜ በርካታ ነጋዴዎችን የሚያስተናግድ አማካይ የገበያ ቦታዎችን ማበጀት፣ የጋራ ጥቅምን ባረጋገጠ መልኩ መብትና ግዴታን በግልጽ የሚያሳይ ስትራቴጂ መንደፍ እንዲሁም በተለይ የገበያውን ሁኔታ የሚያትት የመረጃ ፍሰት ፍጹም ነፃ ማድረግ ጠቃሚ መሆናቸውን መክረዋል።

በአፈር ለምነት፣ በምቹ የአየር ሁኔታና ከተፈጥሮ አደጋዎች ጫና ነፃ ከመሆን አንጻር ከላቲን አሜሪካ አገሮች በስተቀር አፍሪካን የሚወዳደሩ አህጉራት የሉም ያሉት ዶክተር ጉቱ፣ አፍሪካውያን የውስጥ ችግሮቻቸውን በቁርጠኝነት ፈትተው በቴክኖሎጂ በመታገዝ ፊታቸውን ወደ ልማት ካዞሩ ለም መሬታቸውን የምግብ ዋስትናቸውን ከማረጋገጥና የቀጣናውን ንግድ ከማገዝ አልፎ አፍሪካ ለዓለም የምትተርፍ መሆኗን አስገንዝበዋል። ከዚህ አንጻር ኢትዮጵያ በመስኖ ስንዴ፣ በተፋሰስ ልማትና ወንዞቿን በማልማት ያደረገችው ተጋድሎና ያሳየችው ጅምር ውጤት ትልቅ ማሳያ ነው ብለዋል።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ኢትዮጵያ የምግብ ዋስትናዋን ለማረጋገጥ ብሎም የውጭ ምንዛሬ ለማግኘት ለስንዴ ምርት በሰጠችው ትኩረት በአጭር ጊዜ ውስጥ የስንዴ ምርትን ወደ ውጭ መላክ መጀመሯ ትልቅ እምርታ ነው ያሉት ዶክተር ጉቱ፤ ይህ ደግሞ ስንዴ በብዙ የአፍሪካ አገራት ዘንድ ተፈላጊ በመሆኑ በነፃ ንግድ ቀጣናው ውስጥ ተፈላጊነቷንና ተጠቃሚነቷን በእጅጉ እንደሚያጎላ ጠቁመዋል።

በተመሳሳይ መልኩ አገሪቱ ለተፋሰስ ልማት ሥራዎች እንዲሁም ሰፋፊ እርሻዎችን በዘመናዊ የእርሻ መሣሪያዎች በመታገዝ የጀመረችው የግብርና ሥራ አበረታችና ተወዳዳሪ እንደሚያደርጋትም ገልጸው፤ ክፍተቶች እንዳሉ ሆኖ አገር በቀል የኢኮኖሚም ሪፎርም ሥራዎች በጎ ጅምር ላይ በመሆናቸው በቁርጠኝነት ከቀጠለ ለሌሎች አገራትም አርአያ የሚሆን ነው ብለዋል።

በጥቅሉ አፍሪካውያን ከምንም ጊዜ በላይ የራሳቸውን ችግር በራሳቸው የመፍታት፣ አገር በቀል ቴክኖሎጂዎችን የማበልጸግና ያሉ እምቅ ሀብቶችን የመለየትና በጋራ የማልማት አቅሞችን ማሳደግ አሁን ካለው በብዙ እጥፍ ማሳደግ ያስፈልጋል ያሉት የምጣኔ ሀብት ባለሙያው፤ ይህ ደግሞ ነፃ የንግድ እንቅስቃሴን ጨምሮ ብዙ የአፍሪካውያን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ፍላጎቶች ከኃያላን አገራት ተፅዕኖ እንዲላቀቁ አሊያም በመከባበር ላይ እንዲመሠረት ጉልህ አስተዋጽኦ እንደሚያደርግ ተናግረዋል።

ከሁሉም በላይ አፍሪካውያን ለንግዱ ሥራ ውጤታማነት፣ ለሥራ ዕድል ፈጠራ፤ ብሎም ለአህጉሪቱ ኢኮኖሚያዊ ዕድገት የግሉ ዘርፍ ተሳትፎ እጅግ ጠቃሚ መሆኑን አውቀው ለዘርፉ ልዩ ትኩረት እንዲሰጥ የምጣኔ ሀብት ባለሙያው መክረዋል።

# የአፍሪካ ኅብረት ጉባኤ ለሆቴል ዘርፉ መነቃቃት ጉልህ አስተዋጽኦ እንደነበረው ተገለጸ

**አማን ረሺድ**

አዲስ አበባ፡- 36ተኛው የአፍሪካ ኅብረት የመሪዎች ጉባኤ የኢትዮጵያን የሆቴል ዘርፍ በማነቃቃት ረገድ ጉልህ ሚና ተጫውቷል ሲሉ ኢትዮጵያን ስካይላይትና የሒልተን አዲስ አበባ ሆቴሎች አስታወቁ።

የኢትዮጵያን ስካይላይት ሆቴል የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ አቶ ዮሐንስ አፈወርቅ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በጉባኤው ለመሳተፍ ወደመዲናዋ የመጡ እንግዶች የሆቴሉን ገቢ አሳድገዋል።

በጉባኤው የተሳተፉ እንግዶች አዲስ አበባ ላይ በነበራቸው ቆይታ እንደሆቴላችን ብቻ ሳይሆን እንደአገር ያለው የውጭ ምንዛሬ ገቢ እንዲያድግ የሚረዳ ሥራ ተከናውኗል። ጉባኤው የሆቴል ዘርፉን ኢኮኖሚ ለማሳደግ ትልቅ አስተዋጽኦ አበርክቷል ብለዋል።

ስካይ ላይት ሆቴል በአዲሱ የማስፋፊያ ሕንፃ ጭምር እንግዶቹን ተቀብሎ አስተናግዷል፤ አብዛኞዎቹ ከአፍሪካና ከተለያዩ አገራት የመጡ እንግዶችም በቆይታቸው ደስተኛ መሆናቸውን ገልጸዋል ሲሉ ተናግረዋል።

ሆቴላችንም ለእንግዶቹ ማረፊያ፣ ምግብና የተለያዩ የመዝናኛ ዝግጅቶችን እንዲሁም በተጓዳኝነት ለሚካሄዱ ውይይቶች የስብሰባ አዳራሾችን በማዘጋጀት እንግዶቹን አስተናግዷል ብለዋል።

አቶ ዮሐንስ እንዳስታወቁት፤ የአፍሪካ ኅብረት ጉባኤ በሚካሄድበት ወቅት የኢትዮጵያን ስካይላይት ሆቴል አገልግሎቱን በማሳደጉ ምክንያት የደንበኞች ቁጥር ከወትሮው በተለየ በእጥፍ አድጓል።

ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ አገልግሎት በማቅረብ ለስብሰባው መሳካት የበኩላችንን ድርሻ በመወጣታችን ትልቅ ኩራት ተሰምቶናል ያሉት አቶ ዮሐንስ፤ ተሳታፊዎች በሆቴል የነበራቸው ቆይታ የተሟላ እንዲሆን ቀንና ማታ ላገለገሉ ሠራተኞች ምስጋና ይገባል ብለዋል።

የሒልተን አዲስ አበባ ሆቴል የገበያ ልማት ረዳት ዳይሬክተር አቶ ዳንኤል ገላው በበኩላቸው እንደገለጹት፤ በአፍሪካ ኅብረት ጉባኤ ላይ ለመሳተፍ የመጡ አፍሪካውያንን ኢትዮጵያዊነትን በተላበሰ እንግዳ ተቀባይነት ማስተናገድ ተችሏል፤ በዚህም የሆቴሉ ደንበኞች ቁጥር ጨምሯል።

በጉባኤው ወቅት የተለያዩ አገራት መሪዎችና ሚኒስትሮች በሆቴሉ ተስተናግደዋል፤ በዚህም በወትሮው አገልግሎት በተጨማሪነት በቀን እስከ 450 የሚደርሱ እንግዶችን ማስተናገድ ተችሏል ሲሉ አስረድተዋል።

ጉባኤው በአዲስ አበባ መካሄዱ በኮቪድ ወረርሽኝና በሰሜኑ ጦርነት የተነሳ ተቀዛቅዞ የነበረውን የሆቴል ኢንዱስትሪ ዘርፍ ማነቃቃት ችሏል ሲሉ አስረድተዋል።

እንደ አቶ ዳንኤል ገለጻ፤ ከዚህ ቀደም የነበሩ ልምዶችን በመጠቀም ኢትዮጵያዊ ባህልን የሚያንጸባርቁ የቡና አፈላል ሥርዓቶችንና ሌሎች ሁነቶችን በማዘጋጀት ከገቢ ባለፈ የአገራችንን መልካም ገጽታ በሚገነባ መልኩ እንግዶችን ማስተናገድ ተችሏል።

ሆቴሉ ለጉባኤው ሲባል የመኝታ ክፍሎቹንና አጠቃላይ አገልግሎቱ ላይ ያተኮረ በቂ ዝግጅት አድርጎ እንደነበር ያስታወሱት አቶ ዳንኤል፤ ቀደም ብሎ ተገቢው ዝግጅት በመደረጉ አፍሪካዊ ወንድምና እህቶቻችንን በተሻለ ጥራት ማገልገል ተችሏል ብለዋል።

36ተኛው የአፍሪካ ኅብረት የመሪዎች ጉባኤ ከየካቲት 11 እስከ የካቲት 12 ቀን 2015 ዓ.ም ድረስ በአዲስ አበባ መካሄዱ ይታወሳል።

# ጉባኤው የኢትዮጵያን...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

ውይይት መደረጉን ጠቅሰውም፤ ኢትዮጵያ ንቁ ተሳትፎ አድርጋለች ብለዋል። በውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች ደረጃ ሃያ የሚሆኑ አጀንዳዎች ላይ በተመሳሳይ ንቁ ተሳትፎ ነበር። እንዲሁም በመሪዎች ደረጃ ሃያ አጀንዳዎች ላይ የተሳተፈችው ኢትዮጵያ ብሔራዊ ጥቅሟን ለማስከበር ሠርታለች ሲሉ አስረድተዋል።

ዝግጅቱ የተሳካ እንዲሆን በመንግሥት በኩል በቂ ዝግጅት ሲደረግ ቆይቷል ያሉት አምባሳደር መለስ፤ ኢትዮጵያ በብቃት ኃላፊነቷን ተወጥታለች። ጉባኤው ከክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ጀምሮ እስከ ውጭ ጉዳይ ሠራተኞች ድረስ በእቅድ ጊዜ ተወስዶበት ተመክሮበት የተገባበት ሥራ መሆኑ፤ ለበርካታ ዘመናት የካበተው ልምድና ባለድርሻ አካላት የነበራቸው ተሳትፎ መናበብና ለጉባኤው ትኩረት መስጠታቸው ለስኬታማነቱ ከፍተኛ ሚና እንደነበረው ገልጸዋል።

በተዋረድ የተደረጉ ውይይቶች የአገሪቱን ወቅታዊ ሁኔታ በሚገባ ማስረዳት መቻሉንና አዲስ የሰላም ምዕራፍ መከፈቱን እንዲረዱ መደረጉንም አብራርተዋል። የፕሪቶሪያው የሰላም ስምምነት የተወደሰበትና ሌሎች አፍሪካውያን ከኢትዮጵያ መማር እንዳለባቸው የተገለጸበት ጉባኤ እንደነበርም አስረድተዋል።

በጉባኤው አፍሪካውያን ብቻ ሳይሆኑ ከአውሮፓ፣ ከአሜሪካ፣ ከኤዥያ፣ ከመካከለኛው ምሥራቅና ከላቲን አሜሪካ አገራት እንግዶች የተሳተፉበት ነው። በጥቅሉ ማዕቀብ ላይ ያሉትን ሳይጨምር ከአፍሪካ 53 አገሮች ውስጥ 29 የሚሆኑ አገራት መሪዎች፣ አራት ጠቅላይ ሚኒስትሮች፣ አምስት ምክትል ፕሬዚዳንቶች፣ አንድ የፓርላማ ምክትል ፕሬዚዳንት፣ 14 የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች እንደተሳተፉ አብራርተዋል።

እንዲሁም ከአፍሪካው ውጭ ያሉ የበርካታ አገራት ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች መሳተፋቸውን በመጠቆም፤ 358 የተለያዩ አገራት ዲፕሎማቶች፣ 297 ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች ተገኝተዋል። የተባበሩት መንግሥታት ድርጅትን ጨምሮ ሦስት የዓለም አቀፍ ተቋማት ዋና ጸሐፊዎች፣ ዳይሬክተሮችና ፕሬዚዳንቶች የተሳተፉበት መሆኑን ገልጸዋል።

እንደ አምባሳደር መለስ አለም ማብራሪያ፤ ጉባኤው ከኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታው ባሻገር ከፍተኛ የሆነ የዲፕሎማሲና የፖለቲካ ውጤት ነበረው። አገሪቱ የአፍሪካ የዲፕሎማሲና የፖለቲካ መዲና መሆኗን ያረጋገጠችበት ነው። በጥቅሉ ጉባኤው አንድ ሺህ 184 ጋዜጠኞች ሽፋን የሰጡት ሲሆን፤ ከአገር ውስጥ 332 ጋዜጠኞች በተለያዩ ፕሮግራሞች ዘግበውታል።

# ተወዳዳሪ ኢኮኖሚ...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

ጠቅሰዋል። የዜጎችን ገቢ ለማሻሻል፣ ሰፊ የሥራ ዕድል ለመፍጠር፣ የገበያና የኑሮ ወድነትን ጫና ለመቀነስ የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፉን መደገፍ እንደሚያስፈልግም አስገንዝበዋል።

አገራዊ የሪፎርም አጀንዳ ውስጥ የአምራች ኢንዱስትሪ የሚጠበቅበትን መወጣት እንዲችል ቀደም ሲል የነበሩ ፖሊሲዎችን የማሻሻልና አዳዲስ አሠራሮችን የመዘርጋት ሥራዎች እየተሠሩ መቆየታቸውንም ሚኒስትሩ አንስተዋል።

ለዜጎች የሥራ ዕድል መፍጠር፣ የውጭ ምንዛሬ ግኝትንና የምርታማነትን ደረጃ አሁን ካለበት ማሳደግ እንደሚገባ በመጠቆም፤ ይህ እንዲሰካ ለዘርፉ አስፈላጊ ድጋፍ ሊደረግለት እንደሚገባ አመላክተዋል።

በተለይ የፋይናንስ ጉዳይ ለአምራች ኢንዱስትሪዎች ምርታማነትና ዕድገት ከፍተኛ ሚና ያለው መሆኑን ጠቅሰው፤ ለአገር ውስጥ ብቻ ሳይሆን ለውጭ ገበያ ጭምር ምርት ማቅረብ እንዲችሉና ተወዳዳሪ እንዲሆኑ የፋይናንስ ተቋማት ሚና ከፍተኛ መሆኑን ገልጸዋል።

እንደ ሚኒስትሩ ገለጻ፤ አምራች ኢንዱስትሪ ዘርፎች አሁን ካለባቸው ዋነኛ ማነቆዎች መካከል በቀዳሚነት የፋይናንስና ፋይናንስ ነክ ጉዳዮች ተጠቃሾች ናቸው። ዘርፉ በፋይናንስ ችግር ምክንያት በአቅርቦትና በአገልግሎት ጥራት ተወዳዳሪ መሆን አልቻለም። በመሆኑም የፋይናንስ ተቋማት ለአምራች ኢንዱስትሪዎች ብድር ከመስጠት ጀምሮ ቀልጣፋ አሠራርን በመዘርጋት ዘርፉን ማበረታታት ይኖርባቸዋል።

በአፍሪካ ኢንፖርት ኤክስፖርት ባንክ የኢስት አፍሪካ ዋና ሥራ አስኪያጅ ኩዳኩሼ ማተሬኬ በበኩላቸው፤ ቀጣናዊ የኢኮኖሚ ትስስርን በሚፈጥር መልኩ ከኢትዮጵያ መንግሥትና የንግድ ባንኮች ጋር አብረው እየሠሩ እንደሚገኙ ገልጸዋል።

አገር ውስጥ ካሉ ባንኮች ጋር በመሆን አምራች ኢንዱስትሪውን የሚደግፍ ሥራ እንደሚሠሩ ጠቅሰው፤ መንግሥት በሚዘረጋው የአሠራር ሥርዓት አማካኝነት ዘርፉን ለማሳደግ በሚደረገው ጥረት ውስጥ ለማገዝ ቁርጠኛ መሆናቸውንም ጠቁመዋል።

የአምራች ኢንዱስትሪዎች የማምረቻ ዕቃዎች ውድነት፣ የውጭ ምንዛሬ እጥረትና የብድር አቅርቦት ችግር እንዳለባቸው በውይይቱ ተገልጿል። ዘርፉን ለመደገፍ የፋይናንስ ሥርዓቱን በሚገባ ማወቅ እንደሚገባና ተግዳሮት የሆኑ የአሠራር ሥርዓቶች በመንግሥት በኩል እንዲስተካከሉም ተነስቷል።

በ10 ዓመቱ የመንግሥት እቅድ ትግበራ በአምራች ኢንዱስትሪው ዘርፍ ለአምስት ሚሊዮን ዜጎች የሥራ ዕድል ለመፍጠርና ዘጠኝ ቢሊዮን ዶላር ገቢ ለማግኘት መታቀዱ ይታወቃል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የቻይና መንግሥት የሰጠው የቀረጥ ነጻ ዕድል ለኢትዮጵያውያን ከዕድል በላይ ነው

ባለንበት ወቅት በፈጣን ሁኔታ ከማደግ ባለፈ ፤ ነገዎቻቸው ላይ ተስፋ ሰንቀው ለመሮጥ ለሚንደረደሩ ህዝቦች እንደ አንድ ትልቅ አቅም ሆነው ከሚያገለግሉ አገራት መካከል አንዷ ቻይና ነች ። በዚህም እያገኘችው ያለው ዓለም አቀፍ እውቅና እለት እለት እየጨመረ ይገኛል።

በተለይም በቀደሙት ዘመናት በነበሩ የቅኝ አገዛዝ ሆነ ከዛም በኋላ በተፈጠሩ የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ስርአቶች ውስብስብ በሆኑ ውጪያዊ ችግሮች ብዙ ዋጋ ለመክፈል ለተገደዱት የአፍሪካ ሕዝቦች እያደረገችው ያለው ድጋፍ በታሪክ ውስጥ ትልቅ ስፍራ የሚኖረው ነው።

ከአስገዳጅ የፖለቲካ ጫና በወጣ፤ የጋራ ተጠቃሚነትን መሰረት ባደረገ፤ ከሁሉም በላይ የአህጉሪቱን ህዝቦች ነገዎች ተስፋ ሰጭ በሚያደርግ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ አስተሳሰብ የተቃኘው የቻይና አሁነኛ አካሄድ በብዙ መልኩ ዘመኑን የዋጀ እንደሆነም ይታመናል።

የአህጉሪቱን ህዝቦች በተሻለ መንገድ በባቡር ትራንስፖርት ለማቀናጀት የያዘችው ፕሮጀክት ዋን ቤልት ዋንሮድ ስትራቴጂን / One Belt One Road Strategy/ ጨምሮ ፤ የልማት ስራዎችን በገንዘብና በቴክኖሎጂ በመደገፍ፤ ለልማት የሚሆን የገንዘብ ብድሮችንና እርዳታዎችን በመስጠት እያደረገች ያለው ድጋፍ የአህጉሪቱ ህዝቦች ለመሻታቸው አማራጭ እንዲያገኙ አስችሏቸዋል።

ከዛም ባለፈ ከነጻነት ማግስት ያለሟትን የበለፀገች አፍሪካ የመፍጠር ራእይ፤ በአዲስ ተስፋና መነቃቃት ለመተግበር የሚያስችል አቅም መፍጠር እያስቻላቸው ነው። ድምጻቸው በዓለም አቀፍ መድረኮች የተሻለ ተደማጭነት የሚያገኙበትንም እድል እየፈጠረ ነው ።

የአህጉሪቱ ህዝቦች አህን አሁን በሀብታቸው መደራደር ፤ ተደራድረው ተጠቃሚ የሚሆኑበት ዓለም አቀፍ ሁኔታዎች እየታዩ ነው፤ በዚህም በቀደሙት ዘመናት አማራጭ አጥተው / ተስፋ ቢስ ሆነው/ ያጧቸውን ፤ ፖለቲካዊ ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ መብቶቻቸውን በተሻለ አማራጭ በእጃቸው እንዲያስገቡ ተጨማሪ አቅም እየሆነ ነው ።

ኢትዮጵያም በነገዎቻቸው ተስፋ አድርገው ለመለወጥ ከሚተጉ አገሮች አንዷ እንደ መሆኗ፤ በአጭር ጊዜ ሁለንተናዊ እድገት እያስመዘገበች፤ በዚህም ለብዙዎች ተስፋ እየሆነች ካለችው ቻይና በብዙ መልኩ ተጠቃሚ የመሆኗ እውነታ የአደባባይ ሚስጥር ነው።

በተለይም ባለፉት ሁለት አስርት ዓመታት የቻይና መንግስት በኢትዮጵያ የተጀመረውን ልማት በሁለንተናዊ መልኩ ለመደገፍ የሄደበት መንገድ፤ በሁለቱ አገራት የነበረውንና ዘመናት ያስቆጠረውን ግንኙነት ከማደስ ባለፈ በአዲስ መልክ በተጠናከረ መልኩ እንዲቀጥል አስችሏል።

በለፉት ሁለት አስርት በአገሪቱ የተከናወኑ የልማት ስራዎች በአብዛኛው ከቻይና መንግስት በተገኙ በረጅም ጊዜ በአነስተኛ ወለድ በሚከፈሉ ብድሮች እና የልማት ድጋፎች ነው። በዚህም አገርን እንደአገር ተጠቃሚ ያደረጉ ብዙ እድሎች ተፈጥረዋል።

ከቴክኖሎጂና ከእውቀት ሽግግርም አንፃር ቻይና እንደ አንድ አቅም ሆና እያገለገለችን ነው። በዚህም አገሪቱ ዘመኑን የሚመጥን እውቀት ባለቤት የምትሆንበት መልካም አጋጣሚዎች ተፈጥረዋል። የእድሉ ተጠቃሚ የሆኑ ዜጎቻችን ቁጥር ቀላል አይደለም።

ከዚህም ባለፈ ከነገ በስቲያ ጀምሮ 80 የሚጠጉ የኢትዮጵያ ምርቶች በቻይና ገበያ ከቀረጥ ነጻ እንዲገቡ የቻይና መንግስት የደረሰበት ውሳኔ ፤ አገሪቱ ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያውያን ያላትን ከፍያለ ከበሬታ በአደባባይ ያመላከተ ነው።

የፕሬዚዳንት ጆ ባይደን አስተዳደር ባልተገባ መንገድ ኢትዮጵያን አሜሪካ ለአፍሪካ ከሰጠችው የቀረጥ ነጻ እድል /አግዋ / ባገደችበት፤ እገዳው የራሱን የሆነ ችግር ይዞ በመጣበትና አገርን እየተፈታተነ በሚገኝበት በዚህ ወቅት፤ የቻይና መንግሥት የሰጠው ይህ የቀረጥ ነጻ እድል ለኢትዮጵያውያን ከእድል በላይ ነው።


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## የሰላማችንን መሰረት እናጽና

ፍሬሕይወት አወቀ

የሰላምን ዋጋ ለመግለጽ፤ ሰላም ከሌለ በሰላም ወጥቶ መግባት የማይታሰብ ነው ማለት ብቻ ዋጋውን በእጅጉ ያሳንሰዋል። ምክንያቱም ሰላም በዋጋ አይተመንምና ነው። ሰላም ለሰው ልጆች ብቻ አይደለም ለእንስሳት አራዊቱ ሁሉ የግድ አስፈላጊ ነው። በተለይም ለሰው ልጆች የመኖር ዋስትና ነው። በዕለት ተዕለት ተግባር ውስጥ ከምንተነፍሰው አየር ያልተናነሰ ዋጋም አለው። በጠፋ ጊዜ ታድያ ሰዎች በተስፋ መቁረጥ ድባቴ ውስጥ ይወድቃሉ። ተስፋ በመቁረጥ፣ በፍርሃትና በጥርጣሬም ይሸበባሉ።

እርግጥ ነው አገራት በተለያየ ምክንያት ሰላም ሲያጡ ማስተዋል የተለመደ ነው። ብዙዎቹም ያጡትን ሰላም ለመመለስ ጦርነትን ብቸኛ አማራጭ በማድረግ ጦር መዘው ቃታ ስበው ሲጨራረሱ ማየት የተለመደ ነው። የሰላም አስፈላጊነት ከማንኛውም የግል ጥቅም፣ ፍላጎት እና የጦር መሳሪያ ኃይል የሚበልጥ ሆኖ ሳለ ብዙዎች ጦር ይመዛሉ።

ብዙ አገራት ለሰላማቸው መደፍረስ አይነተኛ ምክንያት ቢኖራቸውም ሰላማቸውን የማረጋጋጥ ኃላፊነትም በእጃቸው መዳፍ ላይ መሆኑ ሳይታለም የተፈታ ነው። ይሁን እንጂ ብዙዎቹ ለሰላም ዋጋ ሲከፍሉና ቅድሚያ ሲሰጡ አይስተዋልም። እንደሌሎች አገራት ሁሉ ኢትዮጵያም ሰላሟን ማደፍረስ የሚችሉ ከበቂ በላይ ምክንያቶች አሏት።

አንዱን ችግር ተሻገርኩ ስትል እግር በእግር ተከታትለው ከልማት ጉዞዋ የሚያስተጓጉሏት ግን ደግሞ ፍጹም ሊያስቀሯት የማይችሉ ብዙ ችግሮች በዙሪያዋ አሉ። በውል ተለይተው እየናጧትና እየተጋሏት ካሉ ችግሮቿ በተጨማሪ ነገ ከነገ ወዲያ ሊፈነዱ የሚችሉ ፈንጂዎች ላለመኖራቸውም ማረጋገጫ የለም።

ኢትዮጵያን በየጊዜው ከሚፈትናት ችግር፣ ድርቅ፣ ረሃብና ሰቆቃ ባሻገር ጦርነትም እጣ ፈንታዋ እስኪመስል ኖራበታለች አሁንም አለችበት። እርግጥ ነው ሁሌም ቢሆን ጥፋት፣ ውድመትና ኪሳራን ብቻ የሚያስከትለውን ጦርነትን መምረጥ የግድ የሚሆንበት ጊዜ አለ። ጦርነት አማራጭ ጠፍቶ የግድ የሚገባበት ቢሆንም ቅሉ መጨረሻው መስማማትና መደራደር እንደሆነም ይታመናል።

በተግባርም እየሆነ ያለው ይኸው ነው። የኢትዮጵያ መንግሥት ከሕወሓት ጋር የግድ ሆኖበት በገጠመው ጦርነት የሆነው ይሄው ነው። ጦርነት ያው ጦርነት ነውና ዜጎች በጦርነቱ ሰላም አጥተዋል፤ ብዙ ዋጋም ከፍለዋል። ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ምስቅልቅሎሽ ተፈጥሯል።

ሁለት ዓመታትን ያስቆጠረው የሰሜኑ ጦርነት ባስከተለው ምስቅልቅሎሽ በሕይወትና በንብረት ላይ ከደረሰው ውድመት በተጨማሪ የሕዝቦችን ችግር ተመልክተን እንደ ሰው በተለይም እንደ ኢትዮጵያዊ በብዙ ታመናል ቆስለናል።

ከቁስላችን እንድንሽር አልያም ከህመማችን እንድንፈወስ ታድያ ሰላም የግድ በመሆኑ ሰላም እንዲሰፍን ሆኗል። ጦርነትን አስወግዶ ሰላምን ለማምጣት ቆም ብሎ ማሰብና መስከን ቀዳሚው ጉዳይ በመሆኑ መንግሥት ‹‹ሰላምን ለማስፈንና ብልጽግናን ለማስቀጠል ብቸኛው አማራጭ ጦርነቱን ማቆም ነው›› ብሎ በማመኑ የሰላም እጆቹን መዘርጋቱ ይታወቃል።

ለሰላም የተዘረጉት የመንግሥት እጆችም ዛሬ ለተፈጠረው ሰላም የነበራቸው ሚና ጉልህ ነው። ከጦርነት ወጥተን የሰላም አየር መተንፈስ መቻላችንም ለዚሁ ነው። ለተፈጠረው ሰላም ተግባራዊነቱና አፈጻጸሙ ምንም ይሁን ምን ጦርነት መቆሙ ለብዙዎች እፎይታን ሰጥቷል።

‹‹ጦርነት ቆመ›› የሚለውን ዜና በመስማት ብቻ የብዙ የእናቶች እንባ ታብሶ ጭንቀታቸው ረገብ ብሏል። በጦርነት ቀጠና ውስጥ የሚገኙ ዜጎችም ዛሬ ከባሩድ ሽታ ከተኩስ ሩምታ ነጻ ወጥተው የሰላም አየር መተንፈስ ጀምረዋል። ይህ ለብዙዎች እፎይታን የሰጠ ትልቅ ተግባር ነው።

ትልቅ ዋጋ ያለውን ሰላም ማረጋገጥ ለመንግሥት ብቻ የሚተው ተግባር አይደለም። እያንዳንዱ ዜጋ ጉልህ አበርክቶ ያለው በመሆኑ ለሰላሙ ዘብ ሊቆም ይገባል። በአካል ከሚከናወነው ጦርነት ውጭ ዛሬም የኢትዮጵያን ሰላምና ደህንነት ለማደፍረስ የተዘጋጁ እዚህም እዚያም የተቀበሩ ፈንጅዎች ስለመኖራቸው ለቁጥር የበዙ ማሳያዎች አሉ።

ሕዝብ ሁሌም ቢሆን ነገሮችን በሰከነ መንገድ ሊያስተውልና ሀቅን አንጥሮ ሊረዳ ይገባል፡፡ ከጦርነት ወጥተን ኡ…ፎ…ይ ስንል ሌላ ችግር እየተፈጠረ የሰላም እጦት አየሩን እንዳይሞላው ሃይ ማለት ይገባል፡፡ ይህ ካልሆነ ግን ፍርሃት፣ ጥርጣሬና ስጋት ሸብቦ በመያዝ ከብልጽግና ጉዟችን ያዘናጋናል

ቁምነገሩ ግን እነዚህ ፈንጂዎች እንዲፈነዱ ዕድል የመስጠትና ያለመስጠት ጉዳይ ነው። መሽቶ በነጋ ቁጥር ሰላማችንን የሚያደፍርሱና እርስ በርስ እንድንጋጭና እንድንፋጭ አጀንዳ የሚቀርጹልን እልፍ ናቸው። እኛም ‹‹የዋህዎች የተቀባበሉ ሽጉጦች ናቸው›› እንደሚባለው አንድ ጊዜ እንኳ ቆም ብለን አናስብም። ከፉዎች ባዘጋጁልን የጥፋት ወጥመድ ዘው ብለን ገብተን ሰላማችንን ለጠላቶቻችን አሳልፈን ስንሰጥ ይታያል።

በዚህም የጠብ፣ የጦርነትና የመገዳደል ምንጭ የሆነውን ጥላቻ እናረግዛለን። እርስ በእርስ እንገፋፋለን። ነገር ግን ቆም ብለን ብናስብና ሰከን ብለን ብናሰላስል ዛሬ ብሔርተኝነትና ጽንፈኝነት መሬት ረግጦ ሊውጠን ባልተገዳዳረ ነበር። አሁን ላይ በዙሪያችን የምናስተውላቸው ለቁጥር ብዙ ግራ መጋባቶችም ባለመስከናችን የመጡ ችግሮቻችን ናቸው።

እርግጥ ነው የእኔ ብቻ የሚል አስተሳሰብን ያነገበ ቡድን በጉልህ ተንሰራፍቶ ቀፎው እንደተነካ ንብ ግር እያለ እዚህም እዚያም ፈንጂውን ማፈንዳት ጀምሯል። ይሁንና “አንድ እንጨት አይነድም…” እንዲሉ አበው ህዝቡ በአንድነት፣ በፍቅር፣ በይቅርታና በመቻቻል ስሜት የጋራ በሆነችው አንድ አገር ውስጥ በሰላም ተጠልሎ ለመኖር ግርታውን ማጽዳት ከህዝብ ይጠበቃል።

ህዝብ ሁሌም ቢሆን ነገሮችን በሰከነ መንገድ ሊያስተውልና ሀቅን አንጥሮ ሊረዳ ይገባል። ከጦርነት ወጥተን ኡ…ፎ…ይ ስንል ሌላ ችግር እየተፈጠረ የሰላም እጦት አየሩን እንዳይሞላው ሃይ ማለት ይገባል። ይህ ካልሆነ ግን ፍርሃት፣ ጥርጣሬና ስጋት ሸብቦ በመያዝ ከብልጽግና ጉዟችን ያዘናጋናል።

ከዚህም ባለፈ የህዝቡ የልማት ፍላጎትና የሥራ ዕድል ፈጠራ ገና ብዙ የሚቀር ሆኖ ሳለ፣ በሁከት ምክንያት የልማት ተቋማት መውደማቸው ቀሪ የቤት ሥራዎቻችንን ያበዛዋል፤ የውጤቱን ጊዜም ያርቀዋል። የአገሪቱ እድገትም የውድመቱን ያህል ወደኋላ ይጎተታል።

ስለዚህ የህዝብን ሰላም ከሚያውኩ ማናቸውም ድርጊቶች በመጠበቅ የሁሉም ነገር መሰረት የሆነውና ትልቅ ዋጋ ላለው ሰላም ዋጋ ከፍለን የአገርን አንድነት፣ ሰላምና ፍቅር፤ ዕድገት ብልጽግናን ማረጋገጥ ከእያንዳንዳችን ይጠበቃል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ በአንድ ወቅት ባደረጉት ንግግር ስለ አገር የተናገሩትን ልዋስና ላብቃ “አገር እንደሰው ናት፤ እኛ እንደሆነው ትሆናለች። ብንፋቀር ፍቅር ታዘንባለች፣ ይቅር ከተባባልን ፈውስ ታፈልቃለች፣ ብንተጋ ብልፅግናን ታጎርፋለች፣ ብንማር ትሰለጥናለች፣ ብንከባበር ብንተባበር ትከብራለች፣ ትገዝፋለች፣ ትልቃለች…”

# ነፃ ሃሳብ



ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል። በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)
fenote1971@gmail.com

## የካቲት 12 ያልሻረው ጠባሳ፤

መቼም ስለ የካቲት 12፣ 1929 የፋሺስት የአዲስ አበባ ጭፍጨፋ በተወሳ ቁጥር በግንባር ቀደምነት ከሚጠቀሱ መጽሐፍት የኢያን ካምቤል ፤ "THE MASSACER OF ADDIS ABABA"ይገኝበታል ። የወቅቱ የጣሊያን ፋሽስት መሪ ቢኒቶ ሙሶሊኒ ፋሽዝምን በመላው ዓለም ለማስፋፋት ካለው የቀን ቅዠትና በአገሬው ዘንድ ያለውን ተቀባይነትና ድጋፍ ለማሳደግ ሲል ኢትዮጵያን ወረረ ። ጀግኖች ኢትዮጵያውያን በኋላ ቀር የጦር መሳሪያ፣ በጦር፣ በጎራዴና በጋሻ ለተከታታይ ስምንት ወራት ገትረው ቢዋጉም፤ የፋሽስቱን የመርዝ ጭስ፣ የአውሮፕላን ድብደባና ሜካናይዝድ ጦር መቋቋም ባለመቻላቸው አዲስ አበባን በፋሽስት እጅ ከመውደቅ አላዳኗትም ።

ወረራው በሌላ በኩል የመንግስታቱን ማህበር / League of Nations/ ከማኮስመኑ ባሻገር የ2ኛውን የዓለም ጦርነት ወደ አዲስ ምዕራፍ እንዳሸጋገረው ኢያን በዚህ ገራሚ መጽሐፉ ያትታል። በእለቱም ሰላማዊ ዜጎች በፋሽስቱ ጎልቶ መሳፍርት የሌለው ሰቆቃና ጭፍጨፋ አለቁ ። የሚያሳዝነው አዲስ አበባ እንዲህ በደም ጎርፍ ስትታጠብ አብዛኛው ዓለም መረጃው አልነበረውም። የሚያውቁም ስለጉዳዩ እንዲነሳ ካለመፈለጋቸው ባሻገር የወራሪውን ፋሽስት ግፍ ደፍሮ ያወገዘ አልነበረም።

የፋሽስት ወታደሮች ጭፍጨፋውን የፈጸሙት በተቻላቸው መጠን ምንም አይነት መረጃ እንዳይወጣ ብርቱ ጥንቃቄ በማድረግ ነው። በአዲስ አበባና በአካባቢው የሰዓት እላፊ በመጣል ፤ የስልክ አገልግሎትን በማቋረጥ ፤ ማንም ከአዲስ አበባ እንዳይወጣ በመከልከልና ከእነሱ ውጭ ካሜራ ይዞ የተገኘን የውጭ አገር ዜጋን ሳይቀር በመቀማት ፤ ጭፍጨፋው ሲፈጸም ያዩ ኢትዮጵያውያን ሳይቀር ሆን ተብሎ ተገድለዋል ።

ጭፍጨፋውን በፊትአውራሪነት የመሩና ያስተባበሩ አብዛኛዎቹ የፋሽስቱ አዛዦችም ሆን ብለው መረጃ በጹሑፍም በፎቶም አላስቀሩም። ሌላው ይቅርና ወደ ሮም የላኩት መረጃ የለም። ቢኖርም እምጥ ይግባ ስምጥ አይታወቅም ይለናል ኢያን መጽሐፉን ለማዘጋጀት የገጠመውን ፈተና ሲገልጽ ።

ጀግኖች አርበኞች በዱር ገደሉ ተዋድቀው የጣሊያን የአምስት አመቱ ቆይታ በሽንፈት ከተጠናቀቀ በኋላ ደግሞ እንግሊዝ ጣሊያን በጦር ወንጀለኝነት እንድትጠየቅ ስለማትፈልግ ስለ ጭፍጨፋው በመረጃነት የሚያገለግሉ ማስረጃዎችን ኢትዮጵያ እንዳታገኝ ሰነዶችን ከመደበቅ አንስቶ ክልከላ እያደረገች በሌላ በኩል ደግሞ የፋሺስቱ ተጠርጣሪዎች በመንግስታቱ ማህበር የጦር ወንጀል ኮሚሽን እንደሚከሰሱ የማይጨበጥ ተስፋ በመስጠት ንጉሱን የማዘናጋት ሥራ ሰርታለች ።

ናዚዎች በኑረምበርግ ለፍርድ ቀርበው በአይሁዶች በጂፕሲዎች ፣ በሮማዎችና በሌሎች ለፈጸሙት ሰቆቃና ግፍ እንዲሁም በ2ኛው የዓለም ጦርነት በፈጸሙት የጦር ወንጀል ሲጠየቁ ፋሺስቶች ግን ለፈጸሙት የየካቲት 12 የአዲስ አበባና የደብረ ሊባኖስ ጭፍጨፋና ሰቆቃም ሆነ የጦር ወንጀል ተጠያቂ ሳይሆኑ መቅረታቸው የዓለማችንን ፍርደ ገምድልነት ማሳያ ሌላ የታሪክ መታጠፊያ ነው ።

በግሌ የአክሱምን ሀውልት ለማስመለስ እንደተደረገው እልህ አስጨራሽ ጥረት ያህል ጭፍጨፋውንና የጦር ወንጀሉን ለዓለም ለማሳወቅ ጥረት ቢደረግ ኑሮ እውቅና ይሰጠውና በጣሊያን መንግስት ላይም ይቅርታ እንዲጠይቅና ካሳ እንዲከፍል ጫና ማድረግ ይችል ነበር ። አገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ በግል ጥረት ያደርጉ እንደነበር መረጃ ቢኖረኝም የመጡ የሄዱ መንግስታት በቂ ዲፕሎማሲያዊ ድጋፍ ስላላደረገላቸው ዛሬ ድረስ ውጤታማ ሊሆን አልቻለም ። አሁን ስልጣን ላይ ያለው አስተዳደር ፤ ከአገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን ጋር በመቀናጀት የጣሊያን መንግስት የፋሽስት ወራሪ በአገራችን ለፈጸመው ግፍና ጭፍጨፋ እውቅና እንዲሰጥና ይቅርታ እንዲጠይቅ ግፊት ሊያደርግ ይገባል ።

በአገር ቤትም ትውልድ ይህን አሰቃቂ ጭፍጨፋ እንዲያውቀው ማስተማር ስለሚገባ በስርዓተ ትምህርቱ ማካተት ያስፈልጋል ። ብዙዎቻችንም ስለዚህ ጭፍጨፋ ያለን እውቀትና መረጃ የሚያወላዳ ስላልሆነ መለስ ብለን በወፍ በረር እንቃኝ ።

"ራስን ካንገት ላይ ፣ ቆራርጦ እየጣለ፤
በችንካር ቸንክሮ ፣ ሰው እየገደለ፤
ሰውን ከእነቤቱ ፣ አብሮ እያቃጠለ፤
ማነው እንደ ፋሺስት በሰው ግፍ የዋለ?
ሥጋችንን ገድለው ፣ ሊቀብሩት ከጀሉ፤
በዚህ ያልነበሩ ፣ ሐሰት እንዳይሉ፤
እኒህ አስከሬኖች ይመሰክራሉ።
ይህን ታላቅ ሥቃይ ፣ መከራና ግፍ፤
ሲያስታውስ ይኖራል የታሪክ መጽሐፍ።..."

እነዚህ ስንኞች ፡- ከ86 ዓመታት በፊት፣ በፋሺስት ጣሊያን ጭፍራ ማርሻል ሮዶልፎ ግራዚያኒ አማካይነት በአዲስ አበባ ከተማ ከየካቲት 12 ቀን 1929 ዓ.ም. ጀምሮ ለሦስት ቀናት በዘለቀው ጭፍጨፋ ሰማዕት ለሆኑት ከ30 ሺ ለሚበልጡ ኢትዮጵያውያን በቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ዐፀድ በቆመው ሐውልት ግርጌ ከሠፈረው ግጥም የተወሰደ ነው ይለናል"ያቺ የካቲት 12 ቀን ! "በሚል ርዕስ ሔኖክ ያሬድ በአማርኛው ሪፖርተር ከሁለት ዓመት በፊት ባስነበበን ማለፊያ የሰማዕታት ዝክረ እንጉርጉሮ አዘል መጣጥፉ ።

ፕሮፌሰር ባህሩ ዘውዴ"የኢትዮጵያ ታሪክ ከ1848 እስከ 1966" በተሰኘውና በ1989 ዓ.ም በታተመው መጽሐፋቸው እንደገለጹት፣ የጣሊያን ፋሺዝም ጽልመታዊ ገጽታ ቁልጭ ብሎ የወጣው በየካቲት 12 ቀን 1929 ዓ.ም ነው። አብርሃ ደቦጭና ሞገስ አስገዶም የተባሉ ሁለት ወጣቶች በግራዚያኒ ላይ ቦምብ ጥለው ካቆሰሉት በኋላ አዲስ አበባ ላይ መዓት ወረደባት።"ጥቁር ሸሚዝ"እየተባሉ የሚታወቁት የፋሺስት ደቀመዛሙርት መንግሥት አይዟችሁ እያላቸው አዲስ አበባን ቄራ አደረጓት። የሰው ልጅ ጭንቅላት እንደ ዶሮ እየተቀነጠሰ ወደቀ። ቤቶች ከእነ ነዋሪዎቻቸው ጋዩ።

እርጉዝ ሴቶች በሳንጃ ተወጉ። የጭፍጨፋው ተቀዳሚ ዒላማ የተማሩ ኢትዮጵያውያን ነበሩ። በተለይም የጥቁር አንበሳ አባላት ከራስ እምሩ ጋር እጃቸውን ከሰጡ በኋላ በከተማይቱ ይገኙ ስለነበር በወረንጦ እየተለቀሙ ተረሸኑ። ይህ የምሁራን ጭፍጭፋ አንድ ትውልድ እንዳለ ያጠፋ በመሆኑም በአገሪቱ የፖለቲካና ምሁራዊ ታሪክ ላይ የማይሽር ቁስል ጥሎ አለፈ።"

በዘመኑ የነበሩት ደራሲ ተመስገን ገብሬ "የዓይን እማኙ ሊቀ ጠበብት እውነቱና የካቲት 12" በተሰኘ ጽሑፋቸው እንዲህ ጽፈዋል፡-"ከሦስት ቀን የከተማ ጥፋት በኋላ ከሆለታ የመጡ የፋሺስት አውሬዎች በሚመለሱበት ካሚዮን በኋላው በኩል አቶ አርዓያን እግራቸውን ጠርቅመው አሠሯቸው። ካሚዮኑ ሳይጐትታቸው 'እኔ ወደ ሰማይ እንድገባ ሰማይ ተከፍቶ ይጠብቀኛል። ኢየሱስንም በዚያ አየዋለሁ። ደስ ይለኛል። ደስ ይለኛል። ደስ ይለኛል!' የሚለውን የሚሲዮን መዝሙር ዘመሩ። ፋሽስቶቹም የተሻለውን መዝሙር ብትሰማ ይሻልሃል አሏቸውና ዱኪ ዱኪ የሚለውን መዝሙራቸውን ዘመሩ። ካሚዮኑም ሞተሩን አስነስቶ ሲነዳ ታስረው ቁመው ነበርና ያን ጊዜ ዘግናኝ አወዳደቅ አቶ አርዓያ ወደቁ። ካምዮኑም እየፈጠነ ጐተታቸው።

ከአዲስ አበባ እስከ ሆለታ አርባ ኪሎ ሜትር ይሆናል። ካምዮኑ ከዚያ ሲደርስ ያ ከካሚዮኑ ጋር የታሰረው እግራቸው ብቻ እንደተንጠለጠለ ነበርና የካሚዮኑ ነጂ ከካሚዮኑ ፈታና ለውሾች ወረወረው። እኔንም ያለሁበትን ቤት ሰብረው ከዚያ ቤት ያለነውን አውጥተው ከየመንደሩም ሕዝቡን አጠራቅመው ኑረዋል። ከዚያም መሀል ጨመሩን። ስምንት መትረየስ በዙሪያችን ጠምደዋል። በዚያም ቦታ ቁጥራቸው በብዙ የሆኑ ሐበሾችን አስቀድመው ገለዋቸዋል። ሬሳቸውም ተቆላልፎ በፊታችን ነበረ። እኛንም በዚያ ሊገድሉን ተዘጋጁ። ለመትረየስም ተኩስ እንድንመች ያንዳችንን እጅ ካንዱ ጋር አያይዘው አሰሩን። አሥረውን ወደ መተኰሱ ሳይመለሱ አንድ ታላቅ ሹም መጣ። የርሱም ፖለቲካ ልዩ ነበረ። ፋሺስቶች የሚያደርጉትን የሰላማዊ ሕዝብ መግደል፤ ሕፃናቶችን ከአባትና እናታቸው ጋራ በቤት ዘግቶ ማቃጠል መልካም ብሎ ቢወድ እንኳን እኒያ ቦምብ በቤተ መንግሥቱ ስብሰባ የወረወሩት ሐበሾች ሳይታወቁ እንዲቀሩ አይወድም ነበርና ስለዚህ ካሚዮኖች ይዞ እየዞረ ፋሽስቶች የሚገድሉትን እያስጣለ ወደ እስር ቤት ለምርመራ ይወስድ ኑረዋል ።

እኛንም እንዲተኮስብን ታስረን ከቆምንበት ከቅዱስ ጊዮርጊስ ጠበል አጠገብ ካለው ሸለቆ እስራታችንን አስፈትቶ በአምስት ረድፍ ወደላይኛው መንገድ ለመድረስ ስንሄድ በአካፋ ራሳቸውን የተፈለጡ እጅግ ብዙ ሰዎች ነበሩ። ምራቄ ደረቀ። በካሚዮኑ ወደ እስር ቤት አስወሰደን። ለጊዜው እስር ቤት ያደረጉት ማዘጋጃ ቤትን ነበር።"

ስድስት ኪሎ በሚገኘው የያኔው ገነተ ልዑል ቤተ መንግሥት ያሁኑ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ቅጥር ግቢ ውስጥ፣ ለኔፕልስ ልዑል ልደት ክብር ተብሎ በተዘጋጀው መሰናዶ አጋጣሚ፣ በወቅቱ የተፈጠረውን የፋሺስት ጣሊያን ጭፍጨፋ የታዘበው ሀንጋሪያዊው ሐኪም ዶ/ር ላዲስላስ ሳቫ ዓይኑ ያየውንና የታዘበውን በማስታወሻው መግለጹን በጳውሎስ ኞኞ "የኢትዮጵያና የኢጣሊያ ጦርነት" መጽሐፍ ላይ እንዲህ ተመልክቷል፡-

"ከዚህ በኋላ በግቢውና በአካባቢው ወዲያውኑ ጅምላ ጭፍጨፋ ተጀመረ። በገነተ ልዑል ቤተ መንግሥት ግቢ ውስጥ ከነበሩት ኢትዮጵያውያን አንድም በሕይወት የተረፈ ሰው አልነበረም። ቦታው ላይ የተካሄደው የጅምላ ጭፍጨፋ የተሰበሰቡት ሰዎች ዕድሜያቸው የገፋ፣ ዓይነ ሥውራን፣ አካል ጉዳተኞች፣ የኔብጤዎችና ሕፃናትን የያዙ ድሃ እናቶች ስለነበሩ በዚህ ቦታ የተፈጸመው ሰቆቃ ትርጉም የሌለው፣ የሚሰቀጥጥና የሚያሳፍር ነበር።"

እርመኛ አርበኞቹ አብርሃ ደቦጭና ሞገስ አስገዶም በግራዚያኒ ላይ ጥቃት ከፈጸሙ በኋላ በተሽከርካሪው ወደ ፍቼ የወሰዳቸው ስምዖን አደፍርስ ነበር።የፋሺስቶች የግፍ ሰለባ ስለሆነው ስምዖን አደፍርስ በጴጥሮስ ጳውሎስ የካቶሊክ መካነ መቃብር በሚገኘው ሐውልቱ ላይ ገድሉን እንዲህ ጽፎታል። «ወጣቱ አርበኛ ስምዖን (1905-1929) የአብርሃና የሞገስ የልብ ጓደኛ ነበር። ከአደጋውም በኋላ ከአዲስ አበባ ያሸሻቸው በታክሲ መኪናው ነበር። ከዚያም በኋላ ተይዞ ደጃች ውቤ ሠፈር በግራዚያኒ ወህኒ ቤት ማቅቆ አካሉ ከሰውነቱ ውጭ ሆኖ በመርዝ ተገደለ። ዘመዶቹ በድብቅ ቀበሩት።"

አበው"ነውን ለማወቅ ነበርን ጠይቅ፤" ይላሉ። ኢትዮጵያ ከአፍሪካ ከጥቁር ዓለም ልቃ በነፃነት የኖረችበት በቅኝ ገዢዎች በአካል ያለ መንበርከክዋ ምሥጢር የሚቀዳው ከነበር ታሪኳ ለመሆኑ እነዚያው አበው ብሂሉን ማጣቀሻ አድርገው ያቀርባሉ። ኢትዮጵያ ከ136 ዓመታት በፊት በአፄ ዮሐንስ አራተኛ ዘመን በዶግአሊ የኢጣሊያ ወራሪ ሠራዊትን በራስ አሉላ ጠቅላይ አዝማችነት የደመሰሰችበት የመጀመሪያው በአውሮፓ ላይ የተገኘ ድል ነበር።

ከዶግአሊ ዘጠኝ ዓመት ቆይታ በኋላ የካቲት 23 ቀን 1888 ዓ.ም ግዙፉን የጣሊያን ወራሪ ሠራዊት በዳግማዊ ምኒልክ ጠቅላይ አዝማችነት ዓድዋ ላይ በድል መደምደሙ በተለይ የጥቁር ዓለም መኩሪያ ለመሆን በቅቷል። የ40 ዓመት ቂም የቋጠረው የኢጣሊያ ፋሺስታዊው መንግሥት በ1928 ዓ.ም በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመን የፈጸመው ወረራ ከአምስት ዓመት የአርበኞች እርመኛ ትግል በኋላ በድል ተደምድሟል። በአምስቱ ዓመት የፋሺስት ወረራ ዘመን ከተፈጸሙት ግፎች አንዱ ደግሞ የካቲት 12 ቀን 1929 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ የተፈጸመው ነው።

ከፍ ብሎ እንደተመለከተው በፋሽስት ኢጣሊያ ጭፍራ ማርሻል ሮዶልፎ ግራዚያኒ አማካይነት በአዲስ አበባ ከተማ ለሦስት ቀናት በዘለቀው ጭፍጨፋ ሰማዕት ለሆኑት ከ30 ሺሕ በላይ ኢትዮጵያውያን መታሰቢያ እንዲሆን በአዲስ አበባ ስድስት ኪሎና በመንበረ ጸባኦት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ሐውልቶች ቆመዋል ። እነዚህን ሰማዕታት ለመዘከር ከ1934 ዓ.ም ጀምሮ በኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት በብሔራዊ በዓልነት እስከ 1966 ዓ.ም ሲከበር ኖሯል።

የኅብረተሰብአዊት ኢትዮጵያ ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት (ደርግ) ሥልጣን ከያዘበት 1967 ዓ.ም ወዲህ ግን በመሠረዙ እስካሁን ታስቦ እየዋለ ነው። ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ 14ኛ ዓመት የዘውድ በዓላቸውን ሐሙስ ጥቅምት 23 ቀን 1937 ዓ.ም ሲያከብሩ በተመረቀውና ለአርበኞችም የተጋድሎ ሜዳሊያ ባበረከቱበት አዲሱ ሐውልት ግርጌ በግእዝ ቋንቋ የተጻፈው ጽሑፍ ዘመነ ፍዳውን የሚያስታውስ ነው።"

ዝንቱ ውእቱ ምዕራፈ አዕጽምቲሆሙ ለብዙኃን ኢትዮጵያውያን እለ ተቀትሉ በግፍዕ በእደዊሆሙ በሕዝበ ኢጣሊያ ፋሽስታውያን አመ ፲ወ፪ ለየካቲት በ፲ወ፱፻፳ወ፱ ዓ.ም ..."ይህ የአፅሞች ማረፊያ በኢጣሊያ ፋሽስታውያን እጅ በግፍ የካቲት 12 ቀን 1929 ዓ.ም የተገደሉ የብዙኃን ኢትዮጵያውያን መታሰቢያ ነው፤ በሚል የሚንደረደረው የሐውልቱ ጽሑፍ አገዳደላቸው በድንጋይ በመወገር፣ በዱላ በመቀጥቀጥ፣ በአካፋ፣ በዶማ በመብረቀ ሐፂን/የብረት መብረቅ (መትረየስ)፣ በየቤታቸው ውስጥ በእሳት በመቃጠል፣ ወዘተ እንደሆነ ይዘረዝራል።

የግፍ አገዳደሉ በተፈጸመ በአራተኛው ዓመት ከብሪታኒያ በድል አድራጊነት የተመለሱት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የነፃነት ምልክት የሆነውን ሰንደቅ ዓላማ ካቆሙ በኋላ በግፍ የተገደሉትን አፅሞች ከየቦታው እንዲሰበሰቡ ሹማምንቱን በማዘዝ ለዝክረ ነገር እንዲሆንም በቅዱስ ስፍራም መታሰቢያውን አቆሙላቸው።ዝክረ ነገሩ እንደታሰበው ዓመት ታመት በክብር እየዘለቀ እንዳልሆነ የሚናገሩት መምህር መንክር ገብሩ፣ በባሕር ማዶ ያሉ ኢትዮጵያውያን መታሰቢያውን በማክበር ብቻ ሳይወሰኑ የኢጣሊያ መንግሥት ለኢትዮጵያ ተገቢውን ካሳ እንዲከፍል እየጠየቁ መሆኑ ያስደስታል፤ እኛም የነሱን አርአያ መከተል አለብን፤» ይላሉ።

የሮዶልፎ ግራዚያኒ የያኔዋ የፋሺስት ጣሊያን በአምስት ዓመቱ ወረራ ወቅት በዓለም የተከለከለ መርዝ ጋዝ ከአውሮፕላን መወርወርን ጨምሮ በርካታ የጭካኔ ተግባራትን በኢትዮጵያውያን ላይ ፈጽማለች። በአዲስ አበባ እና በደብረሊባኖስ ገዳም የተጨፈጨፉትን ጨምሮ በአምስት ዓመቱ የወረራ ወቅት በብዙ መቶ ሺህዎች የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን መስዋእት መኾናቸው ይጠቀሳል።

ይሁንና ለዚህ ግፍ ፣ ሰቆቃና ጭፍጨፋ የጣሊያን መንግስት በአደባባይ ይቅርታ መጠየቅ ይቅርና በስርዓት እውቅና አልሰጠም ። በፋሺስት ጣሊያን የካቲት 12 ቀን 1929 ዓ.ም በአዲስ አበባና በደብረ ሊባኖስ በንጹሐን ላይ ለተፈጸመው ጭፍጨፋ ግፈኞች ለሕግ ስላልቀረቡ፣ ተጸጽተው ይቅርታ ስላልጠየቁና አገራቸውም እውቅና ስላልሰጠ ፤ አገር በቅጡ ያልተጽናናችበትና ጠባሳዋም ያልሻረበት ጥቁር ቀን ነውና ፤ መንግስት ከአገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን ጋር በመቀናጀት የጣሊያን መንግስት ለተፈጸመው ግፍ እውቅና እንዲሰጥ ፣ ይቅርታ እንዲጠይቅና ተገቢውን ካሳ እንዲከፍል ከማድረግ ጎን ለጎን በአገር ውስጥ ደግሞ የሰማዕታት ቀን ታስቦ ከመዋል ይልቅ እንዲከበር በማድረግ ትውልዱ እንዲማርበት ሊያደርግ ይገባዋል ብዬ አምናለሁ ።

ሻሎም ! አሜን ።

# ወቅታዊ

# ‹‹ምንም ተማሪ ያላሳለፉ ትምህርት ቤቶች ቀዶ ህክምና ያስፈልጋቸዋል››

*- ዶክተር አማኑኤል ኤሮሞ*
*በኮተቤ የትምህርት ዩኒቨርሲቲ መምህር*

አስቴር ኤልያስ

**አንድ አገር ሁለንተናዊ እድገት ሲኖረው የሚችለው ብቁ የሰው ኃይል ሲኖረው እንደሆነ ይታመናል። ብቁ የሰው ኃይል ለማግኘት ደግሞ ትምህርት ግንባር ቀደሙ መሣሪያ ነው። ትምህርትን በተሻለ ጥራት መስጠት ሲቻል፤ የአገሪቱን ራዕይ በቀላሉ ለማሳካት አያዳግትም። በጥራት የተማረ የሰው ኃይል፣ በቴክኖሎጂውም የተሻለ ሐሳብ በማመንጨቱ ረገድ ሚናው ከፍ ያለ ሲሆን እንደሚችል አያጠራጥርም።**

**ኢትዮጵያም ጥራት ያለው የተማረ የሰው ኃይል ከማብቃት አኳያ በዚህ ዓመት የጀመረችው የ12ኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተናን በጥንቃቄ መፈተን አንደኛው እንደሆነ ይታወቃል። በዚህ ፈተና የመጣው የተማሪዎች ውጤት ከሚጠበቀው በላይ አስደንጋጭ ሆኖ ተመዝግቧል። ይህንን ዝቅተኛ ውጤት በመቀልበስ የተሻለ ነጥብ ማስመዝገብ የሚቻለው እንዴት ነው? ለትምህርት ጥራት ከፍተኛ ትኩረት በመስጠቱ ረገድ መንግስትን ጨምሮ ከባለድርሻ አካላትስ ምን ይጠበቃል? በሚሉና በሌሎች ተያያዥ ጥያቄዎች ዙሪያ በኮተቤ ትምህርት ዩኒቨርሲቲ የትምህርት አመራርና አስተዳደር መምህርና በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ የቀድሞ የመምህራን፣ የሱፐርቫይዘሮችና የርዕሳነ መምህራን ክፍል ዳይሬክተር ከነበሩት ከዶክተር አማኑኤል ኤሮሞ ጋር አዲስ ዘመን ቃለ ምልልስ አድርጎ ተከታዩን ጽሑፍ አጠናቅሯል።**

**አዲስ ዘመን፡- የትምህርት ጥራት ሲባል ምን ማለት ነው? ከሚለው ጥያቄ ቃለ ምልልሳችንን ብንጀምርስ ?**

**ዶክተር አማኑኤል፡-** የትምህርት ጥራት ቀጥተኛ የሆነ ትርጉም ባይኖረውም በተለያየ መንገድ ሊገለጽ ይችላል። ከዚህም አንዱ በትምህርት ስርዓት ውስጥ የሚገለጸው ነው፤ በተመሳሳይ በምርት ብሎም በአገልግሎት ይገለጻል። ለምሳሌ ጥራት ሲባል የላቀ አገልግሎት ወይም ልሕቀት እንደማለት ነው። ልህቀት ሲባል ደግሞ በየጊዜው የሚሻሻልና የሚስተካከል ነገር ነው።

በትምህርት ስርዓት ውስጥ የላቀ አገልግሎት ማለት የላቀ የተማሪዎች ውጤት ብለን እናስቀምጣለን። የላቀ የተማሪዎች ውጤት ሲባል ደግሞ መገለጫው በየደረጃው ባሉ ክፍሎች ላይ ሲሆን፤ ይኸውም ስታንዳርዱን ጠብቀው የሚዘጋጁ እንደ ስድስተኛ፣ ስምንተኛና 12ኛ ክፍሎች ላይ የሚዘጋጁ ፈተናዎች ልህቀትን ያመለክታሉ። ተማሪዎች በየደረጃው የሚጠበቅባቸውን ትምህርት አጠናቅቀው ምን ያህል ያሉበት ደረጃ ላይ እንደደረሱ የሚያሳይ ነው። ይህ ከተማሪዎች ውጤት ጋር ቀጥታ ግንኙነት ያለው ነው።

ከዚህም አልፎ ጥራት ልክ እንደገንዘብ ሁሉ ዋጋ አለው። በትምህርት ስርዓታችን ውስጥ ብዙ የሆነና ከፍተኛ የሰው ኃይል፣ የቁሳቁስና የፋይናንስ ወጪዎች አሉ። እነዚያ ወጪዎች በሙሉ ተሰልተው ጥራት ካላመጡ ብክነት ነው። እንግዲህ በትምህርት ስርዓታችን ውስጥ ጥራት ስንል ከብክነት ነጻ የሆነ ነው። ለምሳሌ የዘንድሮው የ12ኛ ክፍል ተማሪዎችን ውጤት ስንመለከት 97 በመቶ አካባቢ ያላለፉ ናቸው፤ በዚህ ውጤት መሠረት ጥራት የለም የሚያሰኝ ነው። ስለዚህ እዚህ ላይ የታየው ብክነት ነው።

ሌላው ጥራት ሲባል ቀጣይነት ያለው ማሻሻል ነው። ጥራት በሌላ አገላለጽ ደግሞ መሰረታዊ ለውጥ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ጥራት ማለት የላቀ አገልግሎት መስጠት እንደማለት በመሆኑ የደንበኛ እርካታን የሚያመጣ ነው። ለምሳሌ ደንበኛው ከሚጠብቀው በላይ እንዲረካ ማድረግ ነው። ነገር ግን ከዚህ አኳያ ሲታይ በጥራት በኩል ውጤት ማስገኘት



ፎቶ - በሳሙኤል ተስፋዬ

**የትምህርት ጥራት ማለት ለምሳሌ አንድ ሰው ስንዴ መዝራት ፈልጎ ከጎተራ ሲያወጣ ምርቱን ከእነ እንክርዳዱና ከሌሎች ቆሻሻዎች ሳይለይ ወስዶ ዘራው:: ከዘራ በኂላ ምንም አይነት እንክብካቤ ባለማድረጉ ስንዴው ከነአረሙ በቀለ:: ያንኑ ከነአረሙ የበቀለውን ስንዴ አጭዶ ከመረ:: የከመረውንም ወቅቶ ሲያየው እንክርዳዱ ከስንዴው ጋር እኩል ሆነ:: የእኛም የትምህርት ስርዓት የሆነው እንደዚሁ ነው**

አልተቻለም።

**አዲስ ዘመን፡-በአገራችን በአንደኛና በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እየተሰጠ ያለው የትምህርት አሰጣጥ አግባብነትን እንዴት ይገመግሙታል?**

**ዶክተር አማኑኤል፡-** ጥራት ማለት ስህተትን ለይቶ ማውጣት ማለት አይደለም። የትምህርት ጥራት ማምጣት ማለት ስህተት ከመፈጸሙ በፊት መከላከል ማለት ነው። ስህተት ከመፈጸሙ በፊት መለየት ማለት እንደትምህርት ስርዓት የሚጀምረው የት ላይ ነው? ቢባል ከቅድመ መደበኛ ነው። የትምህርት ስርዓት መሰረት ቅድመ መደበኛ ነው ሲባል፤ ቅድመ መደበኛ ላይ አንድ የአምስት ዓመት ህጻን አዕምሮው 95 በመቶ ይሰራል ተብሎ ይታሰባል። መሰራት ያለበት ቅድመ መደበኛ ላይ ነው። እዛ ላይ ግን አልተሰራም። ቅድመ መደበኛ ላይ ይቅርና አንደኛ ደረጃ ላይም አልተሰራም፤ ለምሳሌ በአንደኛ ደረጃ ከአንድ እስከ አራተኛ ክፍል የሚማሩ ተማሪዎች በነጻ ዝውውር ማለፍ አለባቸው በሚል ሲያልፉ እንደነበር የሚታወቅ ነው።

ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን ስናይ ስምንተኛ ክፍል ላይ በጣር ያለፉ ናቸው\ ስምንተኛ ክፍል አብዛኛው ያለፈው ከ50 በታች የሆነ ውጤት አምጥቶ ነው። በዚህ አይነት ሁኔታ እስከ 12ኛ ክፍል መጥቶ 12ኛን ክፍል ተፈተን ተባለ፤ 12ኛ ክፍልን ሲፈተን በቅርቡ ይፋ የሆነ ውጤት ተመዘገበ።

ስለዚህ የትምህርት ጥራት ማለት ለምሳሌ አንድ ሰው ስንዴ መዝራት ፈልጎ ከጎተራ ሲያወጣ ምርቱን ከእነ እንክርዳዱና ከሌሎች ቆሻሻዎች ሳይለይ ወስዶ ዘራው። ከዘራ በኋላ ምንም አይነት እንክብካቤ ባለማድረጉ ስንዴው ከነአረሙ በቀለ። ያንኑ ከነአረሙ የበቀለውን ስንዴ አጭዶ ከመረ። የከመረውንም ወቅቶ ሲያየው እንክርዳዱ ከስንዴው ጋር እኩል ሆነ። የእኛም የትምህርት ስርዓት የሆነው እንደዚሁ ነው።

ገና ከመነሻው ላይ አልለየነውም፤ ይዘነው መጣን። 12ኛ ክፍል ደርሶ ውጤቱን ስናይ ግን ያገኘነው የወደቀ ውጤት ነው። ስለዚህ የትምህርት ጥራት እንዲኖር ከተፈለገ መሰራት ያለበት ከቅድመ መደበኛ ጀምሮ ነው። ይህ በየደረጃው መስተካከል የነበረበት ነው።

**አዲስ ዘመን፡- የመጣውን የሶስት በመቶ ዝቅተኛ ውጤት ለመቀልበስ ምን መደረግ አለበት ?**

**ዶክተር አማኑኤል፡-** ዝቅ ያለውን ውጤት ለመቀልበስ መከተል ያለብን የተለያየ አቅጣጫ ነው። አንደኛ ትምህርት ቤቶቻችን ምን ይመስላሉ? ብለን ልናያቸው ይገባል። ከዚህ አንጻር ትምህርት ቤቶቻችንን ስናይ አንድም ተማሪ ያላሳለፉ ትምህርት ቤቶች አሉ። ሁለተኛ ደረጃ ደግሞ የተወሰኑ ማለትም ከአስር በታች ተማሪዎችን ያሳለፉ ትምህርት ቤቶች አሉ። ሶስተኛው ደግሞ የተሻለ የተማሪ ቁጥር ያሳለፉ ትምህርት ቤቶች አሉ።

ምንም ተማሪ ያላሳለፈው ትምርት ቤት መርከቡ ተንሳፏል ማለት ሳይሆን ሰምጧል ነው። ይህን መርከብ ከተቀበረበት ማውጣት የምንችለው እንዴት ነው? ሌላው ደግሞ ሶስትና አራት ተማሪዎችን ብቻ ያሳለፉ ትምርት ቤቶች መርከቡ ተንሳፏል እንጂ እየሄደ ነው ማለት አንችልም፤ ባለበት የቆመ ነው። ሌላው የተሻለ የተማሪ ቁጥር ማሳለፍ የቻለ ትምህርት ቤት አለ፤ እርሱ የሚታገል ትምህርት ቤት ነው።

የተሻለ ቁጥር ያሳለፉ ትምህርት ቤቶችን ለሌሎቹ ሞዴል እንዲሆኑ በማድረግ ተሞክሯቸውን የሚያካፍሉበትን መንገድ ማመቻቸት ይገባል። ዝቅተኛ ቢሆኑም በተወሰነ ደረጃ እየታገሉ ያሉ ትምህርት ቤቶችን ደግሞ በተሻለ ሁኔታ ማብቃትን ይጠይቃል። ምንም ተማሪ ባለማሳለፋቸው የሰመጡ ትምህርት ቤቶች ግን ከፍተኛ ቀዶ ህክምና ያስፈልጋቸዋል። የሰው ልጅ ኩላሊት አልሰራ ካለ ወይ ማከም አሊያም በቀዶ ህክምና ማውጣት የግድ ይላል። እነዚህ የሰመጡ ትምህርት ቤቶችም ቀዶ ህክምና ያስፈልጋቸዋል። ቀዶ ህክምና ደግሞ የሚጀምረው ከአመራሩ፣ ከመምህሩ፣ ከተማሪው፣ ከወላጁ እንዲሁም ከሌላውም ኅብረተሰብ ነው።

አንድም ተማሪ ማሳለፍ ያልቻሉት አንድ ሺ 162 ትምህርት ቤቶች ናቸው። እነዚህን ትምህርት ቤቶች ቀደም ሲል በሚደረገው አይነት በተመሳሳይ አመራር እና በተመሳሳይ አካሄድ እንዲሄዱ ማድረግ አይገባም። ምክንያቱም ልዩ ክትትል የሚያስፈልጋቸው ናቸው። በእኛ በትምህርት ስርዓት የተለያዩ ዓለም አቀፍ ተሞክሮዎች የሚያሳዩት፤ ትምህርት ቤት ማንን ይመስላል ሲባል የትምህርት ቤቱን ርዕሰ መምህር ነው። ስለዚህም የእነዚህ አንድም ተማሪ ማሳለፍ የተሳናቸው ትምህርት ቤት ርዕሳነ መምህራን መፈተሽ አለባቸው፤ መጠየቅም አለባቸው።

የትምህርት ቤት ርዕሰ መምህር ሲጠየቅ ተማሪውም ወላጅም እንዲሁም የየራሳቸውን ስራ መስራት ይጀምራሉ። ለመጠየቃቸው ምክንያቱ በርዕሰ መምህርነት የሚመሩት ትምህርት ቤት ሰምጧል፤ ስለዚህ ተቸግረው ወይም አማራጭ በማጣት ካልሆነ በስተቀር ወደሰመጡት ትምህርት ቤቶች ወላጆች ልጆቻቸውን መላክ እንደማይፈልጉ እርግጠኛ ነኝ። ህልውናውን ባጣ ትምህርት ቤት ውስጥ ወላጅ ልጁን በመላክ እንዲማር አይፈልግም።

ስለዚህ በቀጣይ የትምህርት ስርዓቱ እንዲስተካከል ከተፈለገ ትምህርት ቤቶች ከላይ እስከ ታች በትኩረት ሊሰራባቸው ይገባል። ሌላው በየትኛው የትምህርት ስርዓት ዓለም አቀፍ ጥራት የሚያሳየው በመጀመሪያ በጥራት ትልቅ ሚና የሚጫወተው ተጠያቂው መሪው ነው። መሪ ሲባል የትምህርት ቤት መሪ ብቻ አይደለም። የቀበሌ፣ የወረዳ፣ የዞን ወይም የክልል መሪ ብቻ ሳይሆን የአገር መሪም የትምህርት ጥራት ጉዳይ አጀንዳው መሆን አለበት።

ለምሳሌ በአሜሪካ የአገሪቱ ፕሬዚዳን የነበሩት ሬገን በ1983 የአገራቸው የትምህርት ጥራት ሲወድቅ አገር አደጋ ላይ ነው (Nation at risk) የሚል አዋጅ አወጡ። በወቅቱ ራሽያ ወደህዋ ስትመጥቅ አሜሪካ ወደኋላ ቀርታ ነበር። በዚያን ወቅት 700 ገጽ ያለው አዋጅ ወጣ። በዛ አዋጅ መሰረት የአገሪቱ ትምህርት ሊስተካከል ችሏል።

ሁለተኛ ቡሽ በ2000 (No childe left behind) ማንኛውም ተማሪ በትምህርት ወደኋላ አይቀርም ብለው አዋጅ አወጡ። በዛ አዋጅ የትምህርት

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ወቅታዊ

ጥራት ተስተካክሏል። በተመሳሳይ አባማ በ2009 ላይ (Every Student Succeeds) ሁሉም ተማሪ ውጤታማ ይሆናል ሲሉ ሕግ አወጡ። በዚህም ሕግ አስተካክለዋል። አመራሮቹ በየዘመናቸው ያንን በማድረጋቸው በዓለም ላይ ተጽዕኖ ፈጣሪ አገር ሆነው እየኖሩ ነው። ስለዚህ የትምህርት ጥራት ጉዳይ የዜጎች ጉዳይ ነው። አንድ አገር የሚመራ መሪ ስለዜጎቹ ትኩረት ማድረግ አለበት። ወደእኛ አገር ስንመጣ ግን የትምህርት ጥራትን አጀንዳው አድርጎ የሰራው የትኛው መንግስት ነው? የሚለው ብዙ ያነጋግራል።

ዳግማዊ አጼ ሚኒልክ ዘመናዊ ትምህርትን አስተዋውቀው ሊሆን ይችላል። ጥያቄው ግን ከዛ በኋላ ምን ተሰርቷል ነው። ስለዚህ አሁን መሆን ያለበት የትምህርት ጥራት ሲጓደል ተጠያቂ የሚያደርግ ሕግ መውጣት አለበት። ተጠያቂ የሚያደርግ ሕግ በሌለበት አዲስ ነገር ማምጣት አይቻልም። አንድም ተማሪ ያላሳለፉ ትምህርት ቤቶችን ተጠያቂ ማድረግ ይቻል የነበረው ሕግ መኖር ሲችል ነው። ስለሆነም አጀንዳችን ከላይ እስከታች መሆን አለበት። የትምህርት ቤቱ አመራር ተማሪውም መምህሩም መማር ማስተማሩ የሚካሄደው እርሱ ባለበት ስለሆነ ተጠያቂ መሆን አለበት።

ሌላው ደግሞ ዋናው የትምህርት ትልቁ ስራ ክፍል ውስጥ ያለው ነው። በክፍል ውስጥ ሶስት አካላት አሉ። አንዱ ስርዓተ ትምህርቱ ነው፤ ሁለተኛው መምህሩ ሲሆን፣ ሶስተኛው ተማሪው ነው። እነዚህ ሶስቱ አካላት ላይ በሚገባ መሰራት አለበት። ለምሳሌ ከመምህሩ ዘንድ የሙያ ስነምግባር፣ ብቃት ብሎም ተነሳሽነት ስለመኖሩ መምህሩን ብንፈትሽ የሚገኘው ውጤት ከባድ ነው። ምክንያቱም መምህሩ በስራው እርካታ የለውም፤ እያስተማረ ልቡ ያለው ሌላ ዘንድ ነው። ግን ደግሞ ከመቶ 35 ያህሉ የተማሪው ውጤታማነት ያለው መምህሩ ዘንድ ነው። ተማሪው 40 በመቶ የሚያዝ ሲሆን፣ የተማሪ ውጤት መምጣት አለበት ከተባለ በእነዚህ ሁለቱ አካላት ላይ መሰራት አለበት። ስርዓተ ትምህር ተገቢነት ከተነሳ፤ የስርዓተ ትምህርቱ ተገቢነት ላይ ደግሞ ችግር የለውም።

የተማሪው ችግር ምንድን ነው? ቢባል ተማሪው ራሱ አንደኛ ለመማር ዝግጁ ነው ወይ? የሚለው መጤን ያለበት ነው። በክፍል ውስጥ ባለው የመማር ማስተማር ሒደት ውስጥ እውን ተሳታፊ ነው የሚለው ተመሳሳይ ጥያቄ ነው። ተማሪ ለመማር ዝግጁ ካልሆነና ተነሳሽነት ከሌለው ብሎም በመማር ማስተማሩ ሒደት ላይ ካልተሳተፈ ባልሰማ ምጣድ እንጀራ እንደመጋገር ማለት ነው። ስለዚህ ተማሪው ላይ መሰራት አለበት። ለምሳሌ በሌላ አገር ተማሪ የሚማረው በዘመናዊ ቴክኖሎጂ በመታገዝና በኮምፒውተር በመደገፍም ጭምር ነው።

ሌላው ደግሞ ተማሪ ልጁን እያንዳንዱን እንቅስቃሴ መከታተል ያለበት ወላጅ ነው። ይሁንና ይህንን ኃላፊነት በአግባቡ አልተወጣም። ወላጅ ከራሱ ኑሮ አልፎ የልጁን ኃላፊነት ከመውሰድ አኳያ ችግር አለ። ለምሳሌ የግል ትምህርት ቤት ብንመለከት ወላጅ ገንዘብ ስለሚያወጣ ይከታተላል። ወላጅ ስለልጁ መከታተልና ከትምህርት ቤት ጋር ተባባሪ መሆን አለበት።

ከዚህ ሌላ በቤተ መጽሐፍ እና በቤተ ሙከራ ያለው ሁኔታ ተማሪውን የሚስብ መሆን አለበት። በአጠቃላይ ትምህርት ቤቱ ተማሪውን የሚስብ መሆን ይጠበቅበታል። ይህን ለማድረግ ደግሞ በየደረጃው ያሉ አካላት ኃላፊነት አለባቸው።

**አዲስ ዘመን፡- ትምህርት ቤቶችን ተጠያቂ ሲያደርግ የሚችል ሕግ የለም ሲሉ ጠቅሰዋልና በስትራቴጂዎችና በፖሊሲዎች ዙሪያ እየተካሔደ ያለው ነገር ምን ይመስላል?**

**ዶክተር አማኑኤል፡-** እኔ የትምህርት ሕግ ረቂቁን አይቸዋለሁ። የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲም በአዲስ የመጣበት ሁኔታ አለ። ይሁንና አሁንም በሰፊው ማወያየትን ይጠይቃል። የትምህርት ሕጉም ጸድቋል እየተባለ ነው፤ ይሁንና ተጠያቂነትን ያሰፈነ አይደለም። ስለዚህ መፈተሽ ያለበት ነገር ነው። በዚህ ጉዳይ ክልሎችም ትኩረት አድርገው መስራት አለባቸው። የፌዴራሉን መንግስት መጠበቅ ብቻ ሳይሆን በየክልሉ ያሉት ትምህርት ቤቶች የእውቀት ማዕከል መሆን አለባቸው። ክልሎች በራሳቸው አውድ የትምህርት ጥራትን አጀንዳ ማድረግ አለባቸው። ከዚህ ውጪ ከማዕከላዊ መንግስት በሚወርደው ጉዳይ ብቻ መወሰን የለባቸውም። ሌላው ቀርቶ ትምህርት ቤቶች አስቀድመው ከተማሪዎች ከፍተኛ ውጤት በመጠበቅ ውጥናቸውን ማሻሻልና ማስተካከል አለባቸው። የትምህርት ቤቶችም የስራ ባህል መለወጥ አለበት።

**አዲስ ዘመን፡- ዘንድሮ ሶስት በመቶ የሆነው የተማሪዎች ፈተና ውጤት በእርግጥ ጥራት ያለው ነው ማለት ይቻላል?**

**ዶክተር አማኑኤል፡-** አንድ ነገር ልብ ልንል ይገባል፤ የመጨረሻው የትምህርት ግቡ ምንድን ነው የሚለው? የትምህርት ግቡ ብቁ፣ ተወዳዳሪ እንዲሁም መልካም ስነ ምግባር ያለው ተማሪ ማፍራት ነው። ይህ ዘንድሮ የመጣው ሶስት ነጥብ አምስት በመቶ ጥራት አይደለም። ጥራት የሚባለው አንድ ሰው ዝቅተኛውን ስታንዳርድ አሟላ ማለት በመሰረቱ ጥራት አይደለም። ሶስት ነጥብ አምስት በመቶ የተባለው ሃምሳና ከሀሃምሳ በላይ ያመጣው ተቆጥሮ ነው። በመሆኑም 50 ቀርቶ 75 ማምጣት ጥራት አይደለም። እንዲያውም በእኛ አገር የሚታቀደው ጥራት ማለት 85 በመቶ እና ከዛ በላይ ያመጣ ነው። ስለዚህ በዘንድሮው ውጤት 85 በመቶ እና ከዛ በላይ ያመጡ ተማሪዎች አንድ በመቶ እንኳ የማይሞሉ ናቸው። ከዚህ የተነሳ ጥራት ሙሉ ለሙሉ የለም። የጥራት ስሙ እንጂ ተግባሩ የለም ለማለት ያስደፍራል።

ስለዚህ ጥራት እንዲመጣ መሰራት ያለበት ቀድሞውኑ ሲሆን፣ በየትምህርት ቤቱ ከፍተኛ ውጤት ለማምጣት ታቅዶ መሆን አለበት። እቅዳቸው ተለጣጭ ግብ ማስቀመጥ መሆን አለበት። ለምሳሌ ሲታቀድ በጥቂቱ መሆን የለበትም። ሁሉም ተማሪ ያልፋል የሚል መሆን አለበት። የማንም ልጅ እንዲወድቅ መታቀድ የለበትም። በሚታቀደው እቅድ ደግሞ ተማሪው፣ መምህሩ ብሎም ወላጅ መስማማት አለበት። አሁን የመጣው ውጤት ግን ጥራት አይደለም። የትምህርት ጥራት ሽታው ራሱ እንኳ አለ ማለት ይከብዳል። ስለዚህ መንግስት ትምህርት ቤት ላይ እና ትምህርት ስርዓት ላይ ሪፎርም ማድረግ ይጠበቅበታል። ይህ ካልሆነ አሁን ባለው ሁኔታ ቀደም ሲል በምናደርገው በአጫጭር ስልጠና እንዲሁም አጫጭር መመሪያዎችንና ደንቦችን አውጥተን በመወርወር የትምህርት ጥራትን ማምጣት አንችልም። የትምህርት ስርዓቱ ሪፎርም መደረግ አለበት። የመምህሩም የርዕሰ መምህሩም ስታንዳርድ መፈተሽ አለበት። ስርዓቱ ባለበት ቆሟል። የትምህርት ስርዓቱ መስራት ስላቆመ እንደገና መስራት እንዲችል መፈተሽ የግድ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ለትምህርት ጥራቱ መጓደል አንዱ የመምህሩ የገቢ ሁኔታ ዝቅተኛ መሆን ነው የሚሉ አሉና እርስዎ ይህን እንዴት ያዩታል?**

**ዶክተር አማኑኤል፡-** በየትኛውም አገራት የተደረጉ ጥናቶች የሚያሳዩት ለመምህሩ ተወዳዳሪ የሆነ ደመወዝ ያስፈልጋቸዋል። አገሪቱ አሁን ባላት አቅም ይህን ታደርጋለች አታደርግም ወደሚለው ስንመጣ መክፈል ባትችል እንኳ ከመምህሩ ጋር መደራደር መቻል አለባት እላለሁ። ለመምህሩ እውቅና መስጠት አለበት። የመምህሩን ቁርጠኝነትና ተነሳሽነት የሚጨምር ነገር ካለ መምህሩ ሰርቶ ለውጥ ያመጣል ብዬ አምናለሁ። ስለዚህ ከመምህሩ ጋር መተማመን ላይ መድረስ ያስፈልጋል።

**አዲስ ዘመን፡- የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን ነጻና ገለልተኛ ሆነው እየሰሩ ነው ማለት ይቻላል?**

**ዶክተር አማኑኤል፡-** የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ነጻ ናቸው፤ ገለልተኛ ናቸው? የሚባለው ነገር አጠያያቂ ነው። ከዚህ መረዳት የሚቻለው የከፍተኛ ትምህርት አመራሩ ዩኒቨርሲቲው ካለበት አካባቢ የተገኘ ሰው ነው። እውቀት ደግሞ ዓለም አቀፍ ነው። እነዚህም አመራሮች የመደባቸው ማን ነው? ብንል የሚታወቅ ነውና ነጻና ገለልተኛ ናቸው መባባሉ በጣም አስቸጋሪ ነው። የትምህርት ተቋማት መሆን ያለባቸው ግን ነጻና ገለልተኛ ነው።

እውቀት ዓለም አቀፍ ነው፤ በዓለም ላይ ያሉ ታላላቅ ዩኒቨርሲቲዎች ነጻና ገለልተኛ ናቸው። የሚያስታዳድሩትም ራሳቸውን በራሳቸው ነው።



ከዚህ የተነሳ የእውቀት ማዕከል ናቸው። እኛ ማፍራት የምንፈልገው ምሩቅ ችግር ፈቺ፣ አዲስ አሰራር አመንጪ እንዲሁም በአግባቡ የሚያስብ ዜጋን ነው። ከዚህ አንጻር ተቋማቱ ነጻና ገለልተኛ ሆነው እንዲሰሩ ምቹ ሁኔታን መፍጠር አስፈላጊ ነው። ከዚህ ጎን ለጎን ደግሞ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በየአካባቢዎቻቸው ያሉትን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን እየደገፉና እያበቁ የሚሄዱበትን ምቹ ሁኔታ እየፈጠሩ የመሄዱ ጉዳይ አስፈላጊ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ዘንድሮ የመጣውን ዝቅተኛ ውጤት ተከትሉ ‹‹በልጄ ስምን ይጀመራል›› የሚሉ ወላጆችም አሉና እነዚህን አካላት ምን ይላሉ?**

**ዶክተር አማኑኤል፡-** የትምህርት ጉዳይ የዜጎች ጉዳይ ነው፤ ዜጋ ስንል ደግሞ ሕዝብ ነው። መንግስት ደግሞ ጥራቱን የማስጠበቅ ኃላፊነት አለበት። በዩናይትድ ኔሽን ሂዩማን ራይትስ ላይ መንግስታት ጥራት ያለው ትምህርት ተደራሽ የማድረግ ግዴታ እንዳለባቸው ያስቀምጣል። ይህ ነጥብ ኢትዮጵያም የተቀበለችው ዓለም አቀፍ ስምምነት ነው። በአገራችንም የትምህርት ጉዳይ የመንግስት ጉዳይ በመሆኑ መንግስት ኃላፊነት አለበት።

ትምህርትን ተደራሽም ፍትሐዊም ማድረግ እንችላለን። ትምህርትን በብቃት ማድረስ ብሎም ተገቢም ማድረግ እንችላለን። ይህ ሁሉ ግን ጥራት ከሌለው ከንቱ ነው። ስለዚህ ጥራት ያለው ትምህርት ለማዳረስ ደግሞ መንግስት ኃላፊነት አለበት። ስለዚህ ወላጅ፣ ኅብረተሰቡ፣ ባለሀብቱም ሆኑ ባለድርሻ አካላት በሙሉ ‹‹ልጆቻችን የተመዘኑበት መንገድ አግባብ አይደለም›› ብለው ጥያቄ የሚያነሱ ቢሆን ተገቢ ጥያቄ አይደለም። ለአብነት ቀላል ምሳሌ ልጥቀስ፤ አንድ ሰው አየር መንገድ ቀርቦ አውሮፕላን ለመሳፈር ቢሄድ ተቋሙ እፈትሻለሁ ቢልና ተሳፋሪው ፈቃደኛ አይደለሁም አለ እንደማለት ነው። ልክ ለአውሮፕላኑ ተሳፋሪዎችም ሆነ ለተቋሙ ደህንነት ሲባል መፈተሽ ግድ እንደሆነ ሁሉ መንግስትም በትምህርት ጥራት ላይ ያለውን ስጋት ለማስወገድ ለብዙ ዓመታት ያስተማራቸውን ተማሪዎች ሊመዝን የግድ ነው።

መመዘኑ መንግስት የሚያስመሰግን እንጂ የሚያስወቅሰው መሆን የለበትም። ይህ በቀጣይም ሊሰራበት የተገባው ጉዳይ ነው። ይልቁኑ በ12ኛ ክፍል ላይ ብቻ ሳይሆን ወደፊት በ6ኛ፣ በ8ኛ፣ በ10ኛ እና በየደረጃው ባሉ ክፍሎች ላይ የትምህርት ጥራት መፈተሽ አለበት። ተፈትሾ በተገኘ ግብረ መልስ መስተካከል አለበት። ይህ ሳይሆን ቀርቶ እንዳለፈው ጊዜ ሁሉ ‹ኮርጀህ እለፍ› ማለት አንደኛ እና ሁለተኛ ዲግሪ ያላቸውን ሙሰኞች እንደማፍራት ይቆጠራል። ስለዚህ የተማሪዎችን ውጤት መንግስት በእውቀትና ክህሎት ተንተርሶ መፈተሽ መጀመሩ መንግስትን የሚያስመሰግን ስራ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- በጥራት ተፈትነው አልፈዋል የተባሉት አነስተኛ ቁጥር ያላቸውን ተማሪዎች በጥራት በማስተማሩ በኩል የዩኒቨርሲቲ መምህራንስ ምን ያህል ብቁ ናቸው ይላሉ?**

**ዶክተር አማኑኤል፡-** አብዛኛውን ጊዜ የዩኒቨርሲቲ ትምህርት የሚወሰነው በተማሪዎችም ፍላጎት ላይ ነው። ተማሪ የመረጠው የትምርት መስክ (ፊልድ) ወሳኝነት አለው። ሌላው ደግሞ በዩኒቨርሲቲ ውስጥ መምህሩ ተማሪዎችን የእሱን እውቀት ብቻ የሚያጎርስበት ስፍራ አይደለም። ዩኒቨርሲቲ ውስጥ የገባ ተማሪ ከመምህሩ ውጪ የራሱ ልፋትና ትጋት በእጅጉ ይጠበቅበታል። መምህሩ አመቻች ነው። ስለዚህ ዩኒቨርሲቲ የሚገቡ ተማሪዎች ራሳቸውን በሚጠበቅባቸው ልክ ማዘጋጀት የግድ ይላቸዋል እንጂ ከመምህሩ በሚሰጣቸው ብቻ ውጤታማ ይሆናሉ ተብሎ አይታሰብም።

በዩኒቨርሲቲዎቻችን የምናፈራቸው ተማሪዎች በአገራችን ብቻ ተወስነው የሚቀሩ ሳይሆን በዓለም አቀፍ ደረጃም ተቀባይነት ያላቸው መሆን ይጠበቅባቸዋል። ተማሪዎቹ አዳዲስ ሐሳቦችን ማመንጨት የሚችሉ መሆን አለባቸው።

በዚህ አግባብ በጥራት አለፉ ለተባሉ ተማሪዎች ዩኒቨርሲቲ ቀላል ቦታ ነው ብዬ አልገምትም። ምክንያቱም ከ700፤ 350 ይዞ የገባ ተማሪ የማብቃቱ ስራ በዩኒቨርሲቲው ላይ የተጣለ ቢሆንም ሌሎችም ባለድርሻዎች ብዙ መስራት ይጠበቅባቸዋል። መምህሩን የበኩልን ለመወጣት ብዙ ሚና ይጫወታል ብለን እናስባለን። የተማሪውም ቁጥር አነስተኛ ስለሚሆን ጥራት ያላቸውን ተማሪዎች ለማፍራት ግን ምቹ ሁኔታ ይገኛል የሚል ሐሳብ አለኝ።

**አዲስ ዘመን፡- ስሰጡን ሙያዊ ማብራሪያ ከልብ እናመሰግናለን።**

**ዶክተር አማኑኤል፡-** እኔም ስለተሰጠኝ እድል አመሰግናለሁ።

ኢኮኖሚ

# ኢንቨስትመንት

## ለወረቀት ምርት ተስፋ የተጣለበት የእንሰት ተረፈ ምርት

**አንተነህ ቸሬ**

የኢንዱስትሪው ዘርፍ ከግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ ጋር ተመጋጋቢ ሆኖ በሀገራዊ ምጣኔ ሀብቱ ላይ ላቅ ያለ ድርሻ እንዲኖረው የሚያስችል የምጣኔ ሀብት አቅጣጫ ነድፋ ስትንቀሳቀስ የቆየችው ኢትዮጵያ፣ የኢንዱስትሪው ዘርፍ በሀገራዊ ምጣኔ ሀብቱ ውስጥ ያለው ድርሻ እንዲሻሻል የሚያስችሉ ውጤቶችን አስመዝግባለች። አገሪቱ ያላትን ግዙፍ አምራች ኃይል፣ ወሳኝ ተፈጥሯዊ አቀማመጥ፣ ምቹ ሕጋዊ ማዕቀፎችና ለኢንዱስትሪ ዘርፉ እድገት አወንታዊ አስተዋጽኦ የሚያበረክቱ ሌሎች መልካም አጋጣሚዎችና አስቻይ ሁኔታዎች ተጠቅማ ያከናወነቻቸው ተግባራት ከዚሁ ዘርፍ የሚገኘውን ገቢ በማሳደግ ረገድ ጉልህ ሚና ተጫውተዋል።

ዘርፉ በግብዓት (ጥሬ ዕቃ)፣ በሰው ኃይል፣ በቦታ፣ በኃይል፣ በፋይናንስና በውጭ ምንዛሬ አቅርቦት ችግሮች ተተብትቦ የተያዘ ነው። በዚህም ምክንያት ኢንዱስትሪዎች እያመረቱ ያሉት የአቅማቸውን ግማሽ ያህል ብቻ እንደሆነ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር መረጃዎች ያሳያሉ። በአሁኑ ወቅት የአምራች ኢንዱስትሪው ዘርፍ ከአጠቃላይ ጥቅል አገራዊ ምርት ያለው ድርሻ ከሰባት በመቶ ያልበለጠ ሲሆን፣ በ10 ዓመታት ጊዜ ውስጥ ይህን ድርሻ ወደ 17 ነጥብ ሁለት በመቶ ለማሳደግ ታቅዷል። ከዚህ በተጨማሪም አሁን ያለውን 50 በመቶ የኢንዱስትሪዎች የምርታማነት አቅም ወደ 85 በመቶ የማድረስ እቅድም ተይዟል።

ሀገር በቀል የምርት ዘዴዎችን ዘመኑ ካፈራቸው የቴክኖሎጂ ስርዓቶች ጋር በማጣመር መተግበር የአምራች ዘርፉን ችግሮች በዘላቂነት ለመፍታት ከሚያስችሉ አዋጭ የመፍትሄ አማራጮች መካከል ተጠቃሽ ነው። በኢትዮጵያ የአምራች ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት የኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓቶች ማዕከል ይፋ ያደረገው የጥናት ውጤት የእንሰት ተረፈ ምርት ወረቀትን ለማምረት እንደሚያስችል በተግባር አሳይቷል። ይህ የምርት ዘዴ በግብዓት (ጥሬ ዕቃ)፣ በፋይናንስ፣ በውጭ ምንዛሬ አቅርቦትና በሌሎች ችግሮች ምክንያት ከፍተኛ ፈተና ውስጥ ከሚገኙት አምራች ዘርፎች መካከል አንዱ ለሆነው የወረቀትና የወረቀት ውጤቶች አምራች ኢንዱስትሪ ትልቅ ተስፋ የሚሰጥ እንደሆነ ታምኖበታል።

በአምራች ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት የማኑፋክቸሪንግና የኬሚካል ዘርፍ የቴክኖሎጂና ምርምር መሪ ስራ አስፈፃሚ ዶክተር ደሲሳ ያደታ ከእንሰት ተረፈ ምርት ወረቀትንና የወረቀት ግብዓቶችን የማምረት ዘዴው በስፋት ሲተገበር የኢትዮጵያን የወረቀት ምርት ችግር በዘላቂነት የመፍታት አቅም እንዳለው ይናገራሉ። እርሳቸው እንደሚሉት፣ የሀገሪቱ የወረቀት ኢንዱስትሪ ዘርፍ በዋጋ ንረትና በውጭ ምንዛሬ እጥረት ምክንያት በእጅጉ በመዳከሙ ከእንሰት ተረፈ ምርት ወረቀትንና የወረቀት ግብዓቶችን የማምረት ዘዴው ለዘርፉ ትልቅ ብስራት ነው።

‹‹የወረቀት ምርት ፍላጎትን ለማሟላት እየተሞከረ ያለው ያገለገለ ወረቀትን ለአምስት ወይም ለስድስት ጊዜያት ያህል መልሶ ጥቅም ላይ በማዋል (ሪሳይክል) በማድረግ ነው። ይህ ዓይነት የምርት ዘዴ ደግሞ የወረቀት ግብዓት የሆነው የፋይበሩ ርዝመትና ጥራት እንዲቀንስና እንዲበጣጠስ ያደርጋል፤ በዚህም ምክንያት የሚመረተው የወረቀት ጥራት እጅግ ዝቅተኛ ይሆናል። ከእንሰት ተረፈ ምርት ወረቀትንና የወረቀት ግብዓቶችን የማምረት ዘዴው ግን የተሻለ ጥራት ያለው የወረቀት ምርት ለማግኘት ያስችላል። ይህ የምርት ዘዴ በዋጋ፣ በጊዜ፣ በቴክኖሎጂ እና በአካባቢ ጥበቃ ረገድ አዋጭና ተመራጭ ነው። የምርት ወጪው ከእንጨት ነክ የፐልፕ ምርቶች ጋር ሲነፃፀር አነስተኛ ነው። በቀላል ቴክኖሎጂ የሚሰራ እና ለአካባቢ ብክለት መንስዔ ሊሆኑ የሚችሉ ግብዓቶችን በመሰብሰብ ለምርት ግብዓትነት የሚጠቀም በመሆኑ ለፈጣን የቴክኖሎጂ ሽግግርና ለአካባቢ ጥበቃ በጎ አስተዋፅኦዎችን ያበረክታል›› ይላሉ።

‹‹ኢትዮጵያ ‹የሰው ዘር መገኛ ናት› ከተባለ በቴክኖሎጂውም ቀዳሚ መሆን ነበረብን›› የሚሉት ዶክተር ደሲሳ፣ ‹‹ሀገሪቱ እምቅ ሀብት እያላት ለምርት እጥረት መዳረግ አልነበረባትም። የወረቀት ኢንዱስትሪዎች የማምረት አቅማቸው ዝቅተኛ ነው። የዚህ ምክንያቱ የግብዓት እጥረት ነው። ለምርት ግብዓት የሚሆን ሀብትና አቅም ግን አለ። ከዚህ ሀብት ጥቂቱን እንኳ መጠቀም ቢቻል ብዙ ችግር መፍታት ይቻላል›› በማለት ለምርት ግብዓት የሚሆኑ ሀብቶችን በመጠቀም የምርት እጥረትን ማስወገድ እንደሚገባ ያስረዳሉ። በቀጣይ ከእንሰት ተረፈ ምርት ወረቀትን በማምረት ዘዴ የተገኘው ውጤት ጥራቱ እንዲሻሻልና በስፋት ለገበያ እንዲቀርብ እንደሚደረግም ጠቁመዋል።



**‹‹ኢትዮጵያ ታምርት›› የተሰኘው ሀገራዊ ንቅናቄ ከእንሰት ተረፈ ምርት ወረቀትን ማምረትን የመሰሉ ሀገር በቀል የምርት ዘዴዎችን ለማበረታታት ትልቅ አቅም እንደሚሰጥ ገልጸዋል**

እንሰት በብዛት ከሚመረትባቸው የኢትዮጵያ አካባቢዎች መካከል የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ቀዳሚውን ስፍራ ይይዛል። የክልሉ የኢንተርፕራይዝ ልማትና የስራ እድል ፈጠራ ቢሮ ኃላፊ አቶ ቢረጋ ብርሃኑ ከእንሰት ተፈረ ምርት ወረቀትን የማምረት ተግባር እንሰት አምራች ለሆኑ አካባቢዎች ተጨማሪ ጥቅም የሚያስገኝ እርምጃ እንደሆነ ይናገራሉ። እርሳቸው እንደሚሉት፣ እንሰት በሚመረትባቸው አካባቢዎች ወጣቶችን በማደራጀትና በማሰልጠን ለፋብሪካዎች የወረቀት ምርት ግብዓት የሚሆን የእንሰት ተረፈ ምርት የሚሰበሰብበትን ሁኔታ ማመቻቸት ይገባል። በቀበሌ ደረጃ ተረፈ ምርቱን ሰብስበው ለወረዳዎችና ከዚያም ለፋብሪካዎች የሚያቀርቡ አደረጃጀቶችን መፍጠር ያስፈልጋል። ለስራ አጥ ወጣቶች፣ በተለይም ምንም ዓይነት የገቢ ምንጭ ለሌላቸው ሴቶች፣ የግንዛቤ ማስጨበጫ እና የስራ ፈጠራ ስልጠናዎችን በመስጠት በስራው ላይ እንዲሰማሩ ማድረግ ያስፈልጋል።

ከዚህ በተጨማሪም፣ የእንሰት ተረፈ ምርት ፍላጎት ሲጨምር የአቅርቦት እጥረት እንዳይከሰት የእንሰት ተክልን በስፋት በመትከል ስራውን ዘላቂ ማድረግ እንደሚገባም ያሳስባሉ። ለዚህም የእንሰት በሽታን በመከላከል አቅርቦቱን አስተማማኝ የማድረግ ስራዎችን መስራት እንደሚገባ አቶ ቢረጋ ይናገራሉ።

የደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞንም እንሰት ከሚመረትባቸው የሀገሪቱ አካባቢዎች አንዱ ነው። የዞኑ ዋና አስተዳዳሪ አቶ ታዬ ሙሊሳ ከእንሰት ተረፈ ምርት ወረቀትን ለማምረት ያስቻለው የምርት ዘዴ ለአርሶ አደሩ ጥቅም የሚያስገኝ መሆኑን ያስረዳሉ። እንደርሳቸው ገለፃ፣ ከእንሰት ተረፈ ምርት ተጨማሪ ጥቅም ማግኘት እንደሚቻል ለአርሶ አደሩ ብቻ ሳይሆን በየደረጃው ላለው አመራርም ግንዛቤ መፍጠር ያስፈልጋል።

‹‹ከእንሰት ተረፈ ምርት ወረቀትን የማምረት ተግባር በዞኑ የሚገኙ ስራ አጥ ወጣቶችን በማደራጀት ስራ ለማስያዝ መልካም አጋጣሚ ይፈጥርልናል። ተረፈ ምርቱን ሰብስቦ ለፋብሪካዎች የማቅረቡ ስራ አስቸጋሪ አይሆንም። አርሶ አደሩ፣ በተለይም ሴቶች ተደራጅተው፣ ተረፈ ምርቱን ሰብስበው በቀጥታ ለፋብሪካዎች እንዲያቀርቡ ማድረግ ይቻላል። ከዚህ በተጨማሪ ወጣቶችን በማደራጀትና ከአርሶ አደሩ ጋር ትስስር እንዲፈጥሩ በማድረግ ግብዓቱን እንዲያቀርቡ ማድረግ ይቻላል›› በማለት ከዚህ የምርት ዘዴ ተጠቃሚ ለመሆን ዞኑ ዝግጁ መሆኑን ይገልፃሉ።

የአምራች ኢንዱትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር ዶክተር ሚልኬሳ ጃገማ በሀገር ውስጥ ያሉት የወረቀትና የወረቀት ውጤቶች ማምረቻ ፋብሪካዎች በግብዓት እጥረት ምክንያት በሚፈለገው ልክ እያመረቱ ባለመሆኑ ሀገሪቱ የወረቀት ምርትንና ግብዓቶችን ከውጭ እንደምታስገባ ይናገራሉ።

‹‹የእንሰት ተረፈ ምርት ለወረቀት ምርት ግብዓት እንደሚያገለግል በምርምር ተረጋግጧል። የሙከራ ምርትም እውን ማድረግ ተችሏል። ቴክኖሎጂው የቴክኖሎጂ ሽግግር ይፈጥራል፤ ከውጭ የሚገባውን የወረቀት ምርት በሀገር ውስጥ ለማምረት ያስችላል። ወጣቶችን በማደራጀት ወደ ስራ ለማስገባት ተጨማሪ እድል ይፈጥራል። እያንዳንዱ ተቋም ወረቀትና የወረቀት ውጤቶችን ስለሚጠቀም ፍላጎቱ ከፍተኛ ነው። ይህን ከፍተኛ ፍላጎት ለማሟላት ምርትን መጨመር ያስፈልጋል። ከእንሰት ተረፈ ምርት ወረቀትን የማምረት ተግባር ደግሞ ምርትን ለመጨመር የሚያግዝ ነው። ስለሆነም በቀጣይ ወጣቶችን በማደራጀት በግብዓት አቅርቦት ስራ ላይ እንዲሳተፉ ይደረጋል። ተረፈ ምርቱን በብዛት ለማግኘት ለተፈረ ምርቱ ብቻ ሳይሆን ስለእንሰት በሽታዎች፣ ስለምርታማነቱና ተያያዥ ጉዳዮችም ጠቅላላ ትኩረት መስጠት ያስፈልጋል። ይህ ተግባር ደግሞ የግብርናና የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትንና እና የሌሎች ባለድርሻ አካላትን የጋራ ቅንጅት ይፈልጋል›› ይላሉ። የምርት ግብዓቶችን በሀገር ውስጥ የማምረት ተልዕኮን ለማሳካት ከከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ጋር ትስስር መፍጠር፣ ግብዓት አቅራቢዎችን ከኢንዱስትሪዎች ጋር ማገናኘት እንዲሁም የአቅም ግንባታ ስራዎችን ማጠናከር እንደሚያስፈልግ ይገልፃሉ።

የአምራች ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት የተደራጀው የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችን እና የጥናትና ምርምር ተግባራትን በማከናወን የአምራች ኢንዱስትሪዎች ምርትና ምርታማነታቸው እንዲጨምር ለማድረግ፣ ተጨማሪ የሥራ እድሎችን ለመፍጠር፣ ተኪ ምርቶችን በሀገር ውስጥ ለማምረት በአጠቃላይ የኢንዱስትሪዎቹን ችግሮች በመፍታት የአምራች ኢንዱስትሪውን ውጤታማነት ለማሳደግ መሆኑን የሚናገሩት ዶክተር ሚልኬሳ፣ ኢንስቲትዩቱ ለአምራች ኢንዱስትሪው የስልጠና፣ የቤተ ሙከራ ፍተሻ፣ የማማከር፣ የአዋጭነት ጥናት፣ የጥናትና ምርምር፣ የቴክኒክ ድጋፎችን እየሰጠ እንደሚገኝ ጠቁመዋል።

መንግሥት የኢንዱስትሪው ዘርፍ ችግሮችን ለማቃለል እየተገበራቸው ከሚገኙ የመፍትሄ እርምጃዎች መካከል ባለፈው ዓመት ይፋ የተደረገው የ‹‹ኢትዮጵያ ታምርት›› ሀገራዊ ንቅናቄ ተጠቃሽ ነው። የሀገራዊ ንቅናቄው ዋና ዋና ዓላማዎች የአምራች ኢንዱስትሪውን ችግሮች በጋራ በመፍታት ለዘርፉ ዘላቂ ልማትና ተወዳዳሪነት ምቹ ሁኔታዎችን በመፍጠር ዘርፉ ለኢኮኖሚያዊ መዋቅራዊ ሽግግር የበኩሉን አስተዋጽኦ እንዲወጣ ማስቻል እንዲሁም በዘርፉ ያለውን የስራ ባህል ማሻሻል ብሎም የኢንዱስትሪ ምርቶችን ጥራትና ተወዳዳሪነት በማሻሻል ገቢ ምርቶችን የመተካት ሽፋንን ማሳደግ ናቸው። ንቅናቄው የአምራች ኢንዱስትሪዎችን ምርትና ምርታማነት ለመጨመር ብሎም የዘርፉን ልማት ለመደገፍ እንዲሁም አምራች ኢንዱስትሪዎችን በጥራትና በቁጥር ለማሳደግ የሚያስችሉ ተግባራት የሚከናወኑበት ሲሆን የኢንዱስትሪ ዘርፉን ከተለመደው አሰራር በማሻገር ምርታማነትን ለመጨመር እንደሚያግዝ ታምኖበታል። በአሁኑ ወቅት ኢንዱስትሪዎች ለሀገር ውስጥ ምርት እድገት እያበረከቱት ያለውን አነስተኛ አስተዋፅኦ እንደሚያሳድግም ተስፋ ተጥሎበታል።

ዶክተር ሚልኬሳ ‹‹ኢትዮጵያ ታምርት›› የተሰኘው ሀገራዊ ንቅናቄ ከእንሰት ተረፈ ምርት ወረቀትን ማምረትን የመሰሉ ሀገር በቀል የምርት ዘዴዎችን ለማበረታታት ትልቅ አቅም እንደሚሰጥ ይገልፃሉ። በኢንስቲትዩቱ የኮንስትራክሽንና ኬሚካል ምርምር ማዕከል አማካኝነት በተደረገ የጥናትና ምርምር ስራ ስኬታማ የሆነው ይህ የምርት ዘዴ፣ በንቅናቄው ከተቀመጡ ዓላማዎች ጋር ተመጋጋቢ የሆኑ ጥቅሞችን የሚያስገኝ ነው። ሀገር በቀል የምርት ዘዴዎችንና ግብዓቶችን በመጠቀም የቴክኖሎጂ ሽግግርን፣ የሥራ እድል ፈጠራን፣ የውጭ ምንዛሬ ግኝትንና ተኪ ምርቶችን የማምረት ተግባራትን ለማሳካት የሚያግዝ ነው።

የአገሪቱን የምጣኔ ሀብት መዋቅር ከእርሻ መር ወደ ኢንዱስትሪ መር ኢኮኖሚ ለማሸጋገር የሚያግዙ በርካታ መልካም አጋጣሚዎችና እድሎች እንዳሉ አይካድም። ይሁን እንጂ እነዚህን መልካም አጋጣሚዎች በመጠቀም የኢኮኖሚውን መዋቅራዊ ሽግግር ለማሳካት የተከናወኑ ተግባራት ሀገሪቱ ካላት አቅምና ፍላጎት የሚመጣጠኑ በመሆናቸው ለወቅቱ የሚመጥን ተግባራዊ ምላሽ መስጠት እጅግ አስፈላጊ ነው። ለዚህ ደግሞ የአምራች ዘርፉን ችግሮች መፍታት ከፍተኛ ትኩረት የሚሻ የመፍትሄ አቅጣጫ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል።

# ጎሜ

# ተጠያቂው ማን ነው?

ገርማ መንግሥቴ

ወደ ርእሰ ጉዳያችን ከመዝለቃችን አስቀድመን ቁልፍ ቃላትን እናስተዋውቅ። በዚህ ጽሑፍ ውስጥ "ኃላፊነት" በስነምግብር ንድፈ ሀሳብ (ethical theory) ስር የሚታቀፈው (Social responsibility) "ማኅበራዊ ኃላፊነት"ና የመሳሰሉት ተዘወታሪ ፅንሰ ሀሳቦች ናቸው። ለተዘወታሪነታቸው ቀዳሚ ምክንያቱ ደግሞ ተዛማጅ፣ ተጠራሪና አብሮ ሂያጅ መሆናቸው ነውና "አንዱን ጥሎ ሌላውን . . ." እንዳይሆን በዚያ መንገድ መሄዱ ስለማያዋጣ ነው።

ይህ የዛሬውን ርእሰ ጉዳይ ይዘን ስንነሳ ጉዳዩ እንደው በቀላሉ፣ በዋዛ ፈዛዛ ሊኬድበት የሚቻል እንዳልሆነ፤ "ሙዝ ላጥ ዋጥ" አለመሆኑንም አውቀን ነው፡፡ ለሰነፍ ጸሐፊም አልጋ ባልጋ እንዳልሆነም ገብቶን ነው፤ እንደ ሌሎች ርእሰ ጉዳዮች ለተሳልቆ የቀለለ፣ ለአሽሙርም የከበደ እንዳልሆነ ተረድተን ነው፤ . . . ነው፤ . . . ነው። በመሆኑም፣ ጉዳዩን ብስል ተቀሊል አድርገን እንደሚከተለው ለታዳሚ፣ አንባቢያን ማቅረቡን መርጠናል፤ ችርስ!!!

እንደ ባለፈው አመት የጠገናው ጎሹ ብያኔ ከሆነ፣ ተጠያቂነት (Accountability) በኃላፊነት ተቀብለን የምንፈፅመው ወይም የምናከናውነው ጉዳይ (ሥራ) ስኬታማ ሲሆን ምሥጋና እና ማበረታቻ የሚቸረንን ያህል ኃላፊነትን በአግባቡ ለመወጣት ባለመቻላችን ለሚፈጠረው ጉድለት ወይም ውድቀት የሚቀርብብንን ትችት (ወቀሳ)፣ የሥነ ምግባር ማስተካከያ እና ህጋዊ ወይም አስተዳደራዊ እርምጃ በፀጋና በቅንነት ከመቀበል አልፎ የሚያስከፍለን ዋጋ የሚኖር ከሆነም ለመክፈል ዝግጁዎች ሆነን የመገኘታችንን አስፈላጊነት የሚነግረን ጽንሰ ሃሳብ ነው።

እኛም እናክልበት፤ ተጠያቂነት ኃላፊነትን መውሰድ ነው፣ ተጠያቂነት ኃላፊነትን መሸከም ነው። ተጠያቂነት ለጠፋው፣ ለወደመው፣ ላልተሠራው፣ መሆን እያለበት ላልሆነው፣ መሆን እየሌለበት ለሆነው ወዘተርፈ ሁሉ "... ተጠያቂው እኔ ነኝ" ብሎ እራስን ለፍርድ ማቅረብ ነው። ተጠያቂነት፣ በማርኪስዝም-ሌኒኒዝም ቋንቋ ሂስን መዋጥ ("እከሌ ሂሱን ውጧል" እንዲል የዘመነ ደርግ ታሪክ) ነው። ተጠያቂነት ከሁሉም በላይ ለራስ ታማኝ ሆኖ ለደረሰው ሁሉ ሙሉ ሀላፊነትን ወስዶ ራስን ማጋለጥ፣ አጥፍቻለሁ፣ አውድሜያለሁ፣ ዘርፌያለሁ፣ የተሰጠኝን ስልጣን ለግል ጥቅሜ አውያለሁ ብሎ መናዘዝ ነው። ተጠያቂነት በሕግ የበላይነት ማመን ነው!!!

ተጠያቂነት ከስግብግብነትና ንዝህላልነት ፅድት ያለ፤ ተጠያቂነት ሁሌ ሰንካላና ሽባ ምክንያቶችን ከመደርደር፤ የእናቴ ቀሚስ አደናቀፈኝን የማይቀበል . . . የላቀ መስዋእትነትን የሚጠይቅ ተግባር ነው። ተጠያቂነት . . . ብዙ ነገር ማለት ነውና ጉዳዩ እዳው ገብስ አይደለም እያልን ነው። ( እኛም፣ ፈረንጆቹ ኃላፊነቱ የማን እንደ ሆነ "who is responsible?" እንደሚሉት ሁሉ ለዚህ ነው "ተጠያቂው ማን ነው?" በማለት ሳናውቅ በስህተት ሳይሆን፣ ስናውቅ በድፍረት የገባንበት። ግን፣ ግን . . . ለዚህ ሁሉ አገራዊም ሆነ አህጉራዊ፣ ወይም አለማዊ ትርምስ፣ ኢኮኖሚያዊ ውድመት፣ ከሁሉም በላይ ለሆነው ሰብዓዊ ቀውስና የሕይወት መጥፋት . . . ተጠያቂው ማን ነው???)

ተጠያቂነት ልክ እንደ መሞገስ ሁሉ መወቀስንም እልል............ ብሎ የመቀበል ፍላጎትና አቅምን ይጠይቃል። ተጠያቂነት የመሪነት ተግባርና ሀላፊነት ነውና ለህዝብና ለሀገር መቆርቆርን የግድ ይላል (ያ ካልሆነ ኃላፊነትን ለመውሰድ አቅም ስለማይኖር)፣ ተጠያቂነት ከኃላፊነት፣ ተጠያቂነት ከእምነት፣ ተጠያቂነት ከአርአያነት . . . ጋር ሳይቀር ትስስሩ ጥብቅ ነው።

ተጠያቂነትን ለመውሰድ የሞራል ልእልናን መላበስ ያስፈልጋል። ከተጠያቂነት ፊት ለመቆም የማይበገር ጀግንነትን የግድ ይላል። ተጠያቂነትን ለመቀበል የመንፈስ ጥንካሬን ይፈልጋል። ተጠያቂነትን ለመውሰድ የተሟላ ሰው መሆንን አጥብቆ ይሻል። ተጠያቂነትን ለመውሰድ በራስ መተማመንን የመፈለጉን ያህል፣ ተጠያቂነትን አለመውሰድ ከሰብእና የመውደቅ ልዩ ምልክት ነው። ተጠያቂነትን ለመውሰድ በራስ ላይ የተሀድሶ ፕሮግራም ማካሄድን ይፈልጋል። ተጠያቂነትን ለመውሰድ ኃላፊነትን ይፈልጋል። ኃላፊነትና ተጠያቂነት በአግባቡ ሥራ ላይ የሚውሉበት ሁኔታ የተመቻቸ ይሆን ዘንድ ተግባርን ይፈልጋል። እንቀጥል . . .

ተጠያቂነትን ለመውሰድ የለየለት ዲሞክራት መሆንን ይጠይቃል። ተጠያቂነትን ለመውሰድ ለሺህ ዘመናት እግር ከወርች አስሮ ከያዘን የከፋ ድንቁርና፣ አስከፊ ድህነትና ረሀብ፤ የእርስ በ'ርስ ተላልቆ . . . ለመገላገል ሀሞተ ኮስታራ መሆንን ሁሉ ይጠይቃል። ተጠያቂነትን መውሰድ ከፖለቲካ ክስረት ለመዳን የሚደረግ ብርቱ ጥረት ነውና ሰው ተኮር ርእዮትን ይፈልጋል። ተጠያቂነትን ለመውሰድ ከአድርባይነትና ሌብነት ተፋ'ቶ የፀረ-ሙስና ትግሉ አካል መሆን ያስፈልጋል። ተጠያቂነትን ለመውሰድ የፈሪሀ እግዚአብሔር በልብ መኖር የግድ ነው። (አሁን ጥያቄው፣ "እነዚህ ሰብእናዎች አሉ ወይ?" ነውና ጉዳዩ ያነጋግራል፤ ያወያያል . . . )

ተጠያቂነት ለደረሰው ውድመት፣ ድቀት፣ ለተፈፀመው ወንጀል፣ ሙስና . . . ሁሉ "ተጠያቂው ማን ነው?" ሲባል "እኔ" የማለት ሰብዓዊ ልእልናን ይፈልጋል።

ቀደም ሲል የጠቀስናቸው ጸሐፊ (ጠገናው) "'በኃላፊነትና በተጠያቂነት አምላክ አትግደሉን፣ አታስገድሉን፣ አታገዳድሉን፣ አታሳዱን፣ አታሰድዱን፣ በርሃብና እርዛት አለንጋ አታስገርፉን፣ ወዘተ' እያሉ ከመማፀን የባሰ ትውልዳዊ ውድቀት የለም።" በማለት ለንባብና ታሪክ ያበቁትን ሃሳባቸውንም እዚህ ማስቀመጡ ከታሪካዊ ኃላፊነት አኳያ ተገቢ ይሆናልና አድርገነዋል።

ኃላፊነት (Responsibility) እንደ ግለሰብ ወይም እንደ ቡድን ወይም እንደ ማህበረሰብ ወይም እንደ መንግሥት የሚጠበቅብንን ትክክለኛ ጉዳይ (ተግባር) ሁሉ ተፈፃሚ አድርገን የመገኘታችንን እና የማይጠበቅብንን እና ትክክል ያልሆነ ነገር ደግሞ አድርገን ያለመገኘታችንን አስፈላጊነት የሚገልፅ ጽንሰ ሃሳብ ነው።

እንደሚታወቀውና እንደተለመደው ዓለማችን ቅጣንቧሯ በጠፋባት ጉዳዮች ሁሉ መንግሥታት ከእግር ጥፍር እስከ ራስ ጠጉራቸው ድረስ ያገባቸዋል። በመሆኑም፣ ". . . የለሁበትም" ማለት አይቻላቸውም እና፣ በአንድ ሀገር ውስጥ ተጠያቂነት ይሰፍን ዘንድ መስራት የእነሱ ተግባርና ኃላፊነት (ግዴታ) ነውና፣ ሕዝብ "ለደረሰው ውድመት፣ ጥፋት፣ ሰብዓዊ መብት ጥሰት . . . ወዘተ ተጠያቂው ማን ነው?" ብሎ ሲጠይቅ ". . . ተጠያቂው እከሌ ነው።" ማለት የእነሱ ሙሉ ሃላፊነት ነውና፣ የተጠያቂነት ስርአት መዘርጋት የእነሱ ቀዳሚ አጀንዳ ነውና . . . ወደ መንግሥታዊ ሰነዶች፤ በተለይም (አሾልቀንም ቢሆን) ወደ ውስጥ እናይ ዘንድ (አለ/የለም ብለን የምንወዛገብ ካለን) ወደ ራሳችን ሰነዶች እናዝግም።

በየም አማካሪ ተቋም የተዘጋጀው፣ በትግራይ ክልል (የትግራይ ሴቶች ማህበር የማህበረሰብ አገልግሎት መመዘኛ ካርድ (2001 ኢ.ም)) ሥራ ላይ እንዲውል የተደረገውና "የማህበረሰብ ተሳትፍ ውጤት መመዝገቢያ ካርድ ተመራጭ የማህበራዊ ተጠያቂነት መሳሪያ ነው። . . . ብቃት፤ ጥራት፤ አስተማማኝነትና ቅልጥፍናን" ይለካል የሚለው መመሪያ (ሰነድ) "ተጠያቂነት"ን "ስልጣን ላይ የተቀመጡ ሰዎች የሚያከናውኑት ሥራ (ተግባር) ሁሉ ተጠያቂ የሚሆኑበትና ኃላፊነትን እንዲወስዱ የሚገደዱበት ሂደት (ሥርዓት) ነው።" ሲል ይፈታዋል። (ያነሳነው ችግር መሬት ላይ ስለመኖሩ አንዱ ማሳያ መሆኑን ልብ ይሏል።)

"ማህበራዊ ተጠያቂነት"ን በተመለከተ ደግሞ ወደ ሀረሪ ክልል ሄደን ሀሳብ እንምዘዝ። በቅርቡ (ከታኅሳስ 7-8/2015 ለሁለት ቀናት) የሀረሪ ክልል ገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ቢሮ በጉዳዩ ላይ ከሚመለከታቸው ጋር ሲመክር "ማህበራዊ ተጠያቂነት ፕሮግራም ትግበራ" ማህበራዊ ተጠያቂነት ዜጎች በማንኛውም ደረጃ በሚገኝ የመንግሥት አገልግሎት ተሳትፎ የሚያደርጉበት ሂደት ሲሆን፤ በተሳትፎውም የመንግሥት አገልግሎት ግልፅ፣ ተጠያቂነት ያለበት፣ ውጤታማ የሆነ፣ መልካም አስተዳደርን በማስፈን የመንግስት አስተዳደር እንዲሻሻል እንደሚያደርግ እና በተጨማሪም የአንድ ሀገር ዜጎች መብታቸውንና ግዴታቸውን በውል እንዲረዱ በማድረግ ንቁና ነፃ የሆነ ዴሞክራሲያዊ ማህበረሰብ መፍጠር" የሚያስችል የተመሰከረለት ብቻ ሳይሆን የተጨበጨበለት አሰራር መሆኑን፤ እንዲሁም፣ "በአጠቃላይ ማህበራዊ ተጠያቂነት የመንግሥት አገልግሎት ከሙስና የፀዳና ውጤታማ እንዲሆን በማስቻል በአንድ ሀገር ውስጥ ሁለንተናዊ ልማት እንዲረጋገጥ ማድረግ" መሆኑም ጮክ ብሎ ይነገረናል። ይህንን የመሰለ ወርቃማ (ሳይንሳዊ) ብያኔ ይዞ "እልል በቅምጤ" አለማለት አይቻልምና እልል በቅምጤ ስንል ቆመን ነው።

"ማህበራዊ ተጠያቂነት ፕሮግራም ዜጎች ችግሮቻቸው እንዲፈቱ ለመንግስት ጥያቄ የሚያቀርቡበት የአሠራር ስርአት ነው" ከሚለንና ጉዳዩን በባለቤትነት ከያዘው፣ ከወደ ገንዘብ ሚኒስቴር የተገኘው መረጃ ሹክ እንደሚለን ከሆነ "ፕሮግራሙ መሰረታዊ የአገልግሎት ማሻሻያ ስር ያለ ፕሮግራም ሆኖ ሁለቱን አካላት በማወያየትና ግልጸኝነት በመፍጠር አገልግሎቱን ለማቀላጠፍ በሚያስችል መልኩ የሚፈፀም ተግባር ነው።" ይህ እውነት ከሆነ፣ መሬት ላይ ካለ፤ አሁንም እልል በቅምጤ . . . የማይል ካለ እሱ ራሱ ተጠያቂ ነውና እጁን በማውጣት "እኔ" ሊል፣ ኃላፊነቱን ሊወስድ ይገባል።

ከላይ የጠቀስነውና በየም አማካሪ ተቋም የተዘጋጀው ሰነድ በበኩሉ "ማሕበራዊ ተጠያቂነት ስንል ተጠያቂና ኃላፊነት የሚሰማው አስተዳደርን መገንባት የህብረተሰብ ተሳትፍ ላይ የተመሰረተ አካሄድ ነው።" ሲል ደስ በሚሉ ቃላት ይፈታዋል። አሠራሩንም "ህብረተሰብ ተሳትፎ ቁጥጥር ላይ የተመሰረተ ሲሆን፣ የሚጠቀምበት ዘዴም ማሕበራዊ ክትትል (ቁጥጥር) ና የዜጎችን ሪፖርት በመጠቀም ነው። መመዝገቢያ ካርዱ እንደዜጎች ሪፖርት ሁሉ፣ ማህበራዊና ሕዝባዊ ተጠያቂነትንና ኃላፊነትን ለአገልግሎት ሰጪዎች የሚያስገነዝብ መሣሪያ ሲሆን፤ አካሄዱና መሠረቱ በህብረተሰቡ የታችኛው ደረጃ ላይ የቁጥጥሩን መረብ የዘረጋ ነው።" ይለናል። እንደዚህ ሰነድ ከሆነ "የለሁበትም" ማለት ድሮ ቀረ ማለት ነውና "ሙሽራዬ ቀረ"ን ለመጀመሪያ ጊዜ ደፍራ የዘፈነችው፣ የአበባ ደሳለኝ ". . . የለሁበትም" ዜማ ሥራውን ጨርሶ ከተሰቀለበት ወርዷል ማለት ነውና ደስ ይላል። ካልሆነ ግን አልወረደም ማለት ነውና በሌላ ድምፃዊያን ሊደገምና ሊደጋገም የሚገባው ግጥምና ዜማ ነው ማለት ነው።

ሰነዱ ይህንን ይበል እንጂ፣ ልክ በ2Pac "Brenda's Got a Baby" ዜማ እንደ ተብጠለጠለው ማህበራዊ ኢ-ፍትሀዊነት (social injustice) ማለት ነው፣ ዘመናችን ነገረ ሥራው ሁሉ ቁርጥ የድምፃዊት አበባ ደሳለኝን "የለሁበትም" አይነት ነው ". . . እኔ የለሁበትም" (ኧረ በፈጠረን፣ ይህንን የአበባ ደሳለኝን ጉደኛና ማህበራዊ ሂስ (Social criticism) ሰጪ ዜማ እናዳምጥና ከዚህ ጽሑፍ ጋር በማያያዝ መታዘብ ያለብንን (እንደ ማህበረሰብም እራሳችንን) እንታዘብ።)

ኪነጥበብ የእውኑ ዓለም ነፀብራቅ ነው እንዲሉ፣ በሴቭ ዩር ጀነሬሽን ኢትዮጵያ እና የባለሙያዎች ህብረት ልማት (ፓዴት) በጋራ ሲያከናውኑት በነበረው "ማህበራዊ ተጠያቂነት ፕሮግራም ሁለት" አማካኝነት ቀርቦ የነበረው፣ በዚሁ ጉዳይ ላይ የሚያጠነጥነውና በምህረት ማስረሻ የተዘጋጀው "ከመጠየው . . ." ቴያትርም በተለያዩ የአገሪቱ ወረዳዎች መድረኮች ለእይታ የበቃው ይህንኑ የሚያረጋግጥ ሆኖ ነው። (እዚህ ላይ የጋሽ መሀሙድን "ማን ይሆን?" እንዳለ ለአድማጭ ትተን መሆኑን ማስታወስ እንፈልጋለን። "ኧረ ማ'ነው . . .?")

የሰዎችን (ተጠያቂዎችን) ከተጠያቂነት ሽምጠጣ፣ ፍርጠጣና እግሬ አውጭኝ እንደ ጋዜጠኞች አሳምሮ የሚያውቅ ያለ አይመስለኝም። በሚዲያ ቀርቦ የተሠራ ያልተሠራውን፤ የለማ የወደመውን፤ ሀላፊነቱ የ(እነ)ማ እንደሆነ፣ ተጠያቂውስ ማን እንደሚሆን (ሊሆን እንደሚችል) መናገርን እንደ ጦር የሚፈራው ብዛቱ ከሰማይ ኮኮብ፣ ከምድር አሸዋ እንደሚበልጥ የሚያውቁት እነሱ ብቻ ናቸው። (ጋዜጠኛን ለነገ ቃለመጠይቅ ቀጥሮ ስልኩን እስከወዲያኛው የሚዘጋውን ባለሥልጣን ቤቱ ይቁጠረው እያልን ነው።)

እየቀጠረ የሚጠፋው፣ ስልኩን እስከ ወዲያኛው የሚጠረቅመው፣ የእጅ ስልኩ ሲያጓራ (እንደ ስልኩ ሁኔታ ሲንጫረር) ባልሰማ ጆሮውን በጥጥ የደፈነው፣ ጠያቂውን እያየ ላለመጠየቅ (በአላየሁም) አንገቱን አዞሮ የጎድን የሚሄደው . . . (ጥራት የለውም እንጂ) ብዛቱ ተቆጥሮ አያልቅም። መረጃ መስጠት ማለት አንገት ላይ ወደሮ ማጥለቅ የሚመስለው፣ ቃለመጠይቅ ማድረግን "በራስ እጅ ራስ ላይ ካቴና ማስገባት ነው" በማለት በእምነቱ የፀናውን ወዘተርፈ ቤቱ ይቁጠረው እንጂ ሌላ ምንም ማለት አይቻልም። የዚህ ሁሉ ድምር ውጤት ደግሞ ከተጠያቂነት ለማምለጥ መሆኑ ሲታሰብ ጉዳዩ እስከ ወዲያኛው ያሳዝናል (ልክ እየሄድንበት እንዳለው መንገድ ማለት ነው)።

ሌላው የሚያሳዝነው የተጠያቂነት አለመኖር በመኖር ይተካ ዘንድ የሚቀረጥፈው በጀት ነው። በሰኔ 2010 ዓ.ም ለአየር የበቃ የኢዜአ ዜና "የኢትዮጵያ ማህበራዊ ተጠያቂነት ፕሮግራም ሁለት ከአየርላንድ፣ ከአስትሪያና ከዓለም ባንክ በሚገኝ የገንዘብ ድጋፍ ከ2003 ዓ.ም ጀምሮ በአገሪቱ ሁሉም ክልሎች በሚገኙ 223 ወረዳዎች ላይ በአገልግሎት ሰጪዎችና ተገልጋዮች መካከል በመሆን ዜጎች ተገቢውን አገልግሎት እንዲያገኙ የግንዛቤና የሥልጠና ሥራ ሲሠራ ቆይቷል።" (ዜናው "የማህበራዊ ተጠያቂነት ሁለት ከ2003 ጀምሮ ለሰባት ዓመታት ሲተገበር የቆየ ሲሆን፤ ሶስተኛውን ምዕራፍ በ2011 ዓ.ም ለመጀመር በዝግጅት ላይ መሆኑም ተገልጿል።"ም ብሏል) ይህንን "የገንዘብ ድጋፍ" (ብድር ካልሆነ) በየዙሩ ስናሰላና የተጠያቂነት አለመኖርን ድምር ውጤት ስናስብ ነው እንግዲህ የችግሩ ሁለተኛ ጥፋት (ኤሊያስ ተባባል "ገንዘቡም ያልቅና . . ." እንዳለው) ድቅን የሚልብን። ግን ግን፣ ይህ ሁሉ ገንዘብ ወጥቶበት ለውጥ መጥቷልን? (እዚህች ጋ የሰዎቹን ሀሳብ መዋስ ያስፈልጋል - "ይህ ራሱን የቻለ ጥናት ይፈልጋል" የምትለዋን መሹለኪያ ቀዳዳ።)

የእኛ ጥያቄ "ውጤቱስ?" ቢሆንም፣ መልሱን ሳንጠብቅ (ለ"ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ" ትተን) ኢትዮጵያ (ከላይ "በሀገሪቱ ሁሉም ክልሎች በሚገኙ 223 ወረዳዎች"ን ልብ ይሏል) ምን ያህል በተጠያቂ አልባነት ተሰንጋ እንደተያዘች በመረዳት ብቻ ወደሚቀጥለው፤ መውጫ በራችን እንጠጋ።

አንተ፣ ወንድምም ሆንክ እርስዎ አዛውንቱ፣ ሌሎቻችሁም፣ "እንዴት ሶስቱ ጎምቱ ተቋማት፣ ሕግ አውጭው (The Legislative)፣ ሕግ አስፈፃሚው (The Executive) እና ሕግ ተርጓሚው (The Judiciary) ባሉበት አገር ተጠያቂነት አፈር ከድሜ ይበላል?" እያላችሁ የምትጠይቁ ሁሉ፣ ይህ ጽሑፍ መልስ የሚሰጥ ባለመሆኑ ከወዲሁ ይቅርታ እየጠየቅን፣ ለምትሰጡን ማብራሪያ ከወዲሁ እስከ ወዲያኛው እናመሰግናለን፤ በማጠቃለያችንም ጉዳዩን እንጠቀልለዋለን።

አሁን ባለው ተጨባጭ ሁኔታ፣ "ተጠያቂው ማን ነው?" በሚል ርእስ ወደ እዚህ ውይይት ስንገባ "እኔ" በማለት እጁን የሚያወጣ ሰው እናገኛለን ብለን አይደለም። እንደሌለ እናውቃለንና "እኔ"ን አንጠብቅም። የዚህ ጽሑፍ አላማ "እስከ መቼ?"፣ "ተጠያቂ አልባነት እስከ መቼ መደበኛ አሠራር ሆኖ ይቀጥላል?" የሚለውን ማስረፅና አፋጣኝ መፍትሄ ይፈለግ ዘንድ ማሳሰብ ነውና በዚሁ እንሰናበታለን።

ቸር እንሰንብት!!!

# የዘመን ጥበብ

# የሴት ደራሲያን ቁጥር ለምን አነሰ?

**ዋለልኝ አየለ**

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ መጽሐፍ የሚጽፉ ሰዎች እየበዙ ነው። ቀደም ባሉት ዓመታት መጽሐፍ መጻፍ የሚችሉት ታዋቂና ምሁር የሆኑ ሰዎች ብቻ ይመስል ነበር። መጻፍ ለእነርሱ ብቻ የተሰጠ መታደል ተደርጎም ይቆጠር ነበር።

ይህ የሆነው ለመጽሐፍ ባለን አመለካከት ነው። መጽሐፍ በውስጡ የያዘው በሆሄያት የተጻፈ ሀሳብ ነው። ያ ሀሳብ ማለት በየቦታው የምናወራው፣ የምናየውና የምንሰማው ማለት ነው። የሆነ የሚያስገርም ነገር ስናይ ለቤተሰቦቻችን ወይም ጓደኞቻችን እንናገራለን፤ ደራሲዎች ደግሞ በልዩ ተሰጥዖና ፈጠራ ጨማምረው መጽሐፍ ያደርጉታል ማለት ነው።

እነዚህን ነገሮች በመረዳት ይመስላል ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በተለያየ ሙያ ውስጥ ያሉ ሰዎች መጽሐፍ ሲጽፉ እያየን ነው። በየመንገዱ አዟሪ ላይ ከማያቸው መጽሐፎች በተጨማሪ የማውቃቸው ሰዎች መጽሐፍ ሲጽፉ እያየሁ ነው፤ በጓደኛ በኩልም ‹‹አንብብለት›› ተብዬ ይደርሰኛል።

ይህ ሁሉ ሲሆን ግን አሁንም የሴት ደራሲዎች ቁጥር አነስተኛ ነው። በዛሬው የዘመን ጥበብ ዓምዳችን የሴት ደራሲዎች ቁጥር ለምን አነስተኛ ሆነ የሚለውን በተለያየ ጊዜ ካስተዋልኳቸው ትዝብቶችና መረጃዎች በመነሳት ቅኝት እናድርግ።

የደራሲዎች ሕይወት ለብዙዎቻችን ግልጽ ነው። በእርግጥ የሁሉም ደራሲዎች አይደለም፤ የአብዛኞች ነው ማለት ግን እንችላለን። ይሄውም ሕይወታቸው የቅንጦት አለመሆኑ ነው። ለቁሳዊ ነገሮች ብዙም ቦታ የላቸውም። አለባበሳቸውም ሆነ አካላዊ ገፅታቸው ዘረክረክ ያለ ነው። ይሄ ውጫዊ መለያቸው የተፈጠረው በውስጣዊ ባህሪያቸው ነው። ለውጫዊ ነገሮች ብዙም ትኩረት ስለማይሰጡ ነው። እዚህ ላይ ግን ሁለት ነገር ልብ እንበል! አንደኛ፤ ይህ የሁሉም ደራሲዎች መለያ አይደለም፤ ሁለተኛ፤ ይህ ቀደም ሲል በነበሩት ዘመናት ይታይ የነበረ መለያ ነው።

ደራሲዎች ልዩ የማስተዋል ችሎታ አላቸው። አንድ ደራሲ ሥራው ተወዳጅ የሚሆነውም በዚህ ልዩ የማስተዋል ብቃቱ ነው። ሌላው ሰው ሲኖርበት የነበረውን ቦታ ደራሲ ግን አንድ ቀን አይቶ ብዙ ነገር ይጽፍበታል። ያ ደራሲ የጻፈውን ነገር ሌላው ሰው ግን ልክ አይቶት እንደማያውቅ ሁሉ ‹‹እንዲህም ነበር እንዴ!›› እያለ እንደ አዲስ ያየዋል።

ድምጻዊ ቴዎድሮስ ካሳሁን (ቴዲ አፍሮ) 70 ደረጃ የተሰኘውን ነጠላ ዜማ ያወጣ ሰሞን ደራሲ በዕውቀቱ ሥዩም አንድ ነገር ጽፎ ነበር። ‹‹ማንም ሲወጣበትና ሲወርድበት የኖረውን 70 ደረጃ ቴዲ በልዩ ጥበብ ገለጸው፤ ከዚህ በኋላ 70 ደረጃን በድሮው አይናችን አናየውም›› ነበር ያለው በዕውቀቱ።

የበዕውቀቱ አስተያየት ልክ ነበር። የቴዲ አፍሮ 70 ደረጃ ነጠላ ዜማ ከወጣ በኋላ የአዲስ አበባ ነዋሪ ሁሉ 70 ደረጃን እንደ አዲስ ማየት ጀመረ። ንግድ ቤቶች በስሙ መሰየም ጀመሩ። የቴሌቭዥን ፕሮግራሞች 70 ደረጃ ይቀረጹ ጀመር። ፊልሞች ቦታውን ማሳየት ጀመሩ። 70 ደረጃ ግን ብዙ ዓመታት የኖረ ቦታ ነበር።

ደራሲ እንዲህ አይነት አካላዊና መልከዓ ምድራዊ ነገሮችን ብቻ ሳይሆን ውስጣዊ ስሜቶችንም በልዩ አስተውሎት ይገልጻል። ራሳችን የምናደርገውን ነገር ይገልጽልናል። የሰዎችን ስነ ልቦና ይረዳል። ለዚህም ነው ሥራዎቻቸውን ስናነብ የምንመሰጠው።

እነዚህን ሁሉ ነገሮች ለማስተዋልና ሀሳብ ለማግኘት ደራሲ ማንበብ አለበት። ማንበብ ሲባል የግድ መጽሐፍ፣ ጋዜጣ ወይም መጽሔት... በአጠቃላይ የተጻፈ ነገር ብቻ ማለት አይደለም። ሰው ይነበባል፣ ተፈጥሮ ይነበባል፣ ቁስ አካል ሁሉ ይነበባል፣ የሰው ስነ ልቦና ይነበባል። ይሄ ነው የደራሲ ብቃት።

ርዕሰ ጉዳያችን ስለሴት ደራሲያን ለማውራት ነው። ስለሴት ደራሲነት ለማውራት ደግሞ እነዚህን ነገሮች ልብ እንበል። ለመሆኑ ማህበራዊ ሕይወታችንና ስነ ልቦናችን ሴቶች ደራሲ እንዲሆኑ የሚያስችል ነው? አንድ ደራሲ የሚደርስበት ቦታ የመድረስ ዕድል አላቸው? ነገሮችን ለማስተዋል የሚያስችል ሁኔታ አላቸው? ተፈጥሮንና አካባቢን ለመቃኘት የሚያስችል ማህበራዊ ነፃነት ተሰጥቷቸዋል?

አንድ ልብ ያልተባለ ችግር ይታየኛል። በብዙ ነገሮች የሴቶች ተሳትፎ አነስተኛ ነው። ያ የሆነው ግን በተፈጥሮ የችሎታ ልዩነት ሳይሆን በማህበራዊ አኗኗር ውስጥ በተፈጠረ ልዩነት ነው። ይሄ ችግር በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በሌላውም ዓለም የሚታይ ዓለም አቀፍ ችግር ነው። አሁን ግን የኢትዮጵያን ነባራዊ ሁኔታ ብቻ እንመልከት።

ሴቶች በብዙ ነገሮች ከወንዶች እኩል እንዳይሳተፉ ያደረገው ማህበራዊ አኗኗራችንና በዚያ የተቀረጸው ስነ ልቦናችን ነው። እንደ ማሳያ የምጠቀመው አሁን ባለንበት ዘመን ላይ ባለው ውስጥ ያስተዋልኳቸውንና እየሆኑ ያሉ ነገሮችን ነው። አንዱ ችግር መስሎ የሚታየኝ ቅድሚያ ለሴቶች በሚል ሰበብ ሴቶች ላይ የደካማነት ስነ ልቦና መፍጠር ነው። ‹‹አልችልም እንዴ!›› ብለው ራሳቸውን እንዲጠራጠሩ የሚያደርግ ነው። ግልጽ ለማድረግ ከዚህ በፊት በሌላ ጽሑፍ የገለጽኩትን አንድ ገጠመኝ ላንሳ።

ከአራት ዓመታት በፊት ነው። 123ኛውን የዓድዋ ድል በዓል ለማክበር ጋዜጠኞች ወደ ዓድዋ እየተጓዝን ነው። በጉዟችን ውስጥ ታሪካዊ ቦታዎች ይጎበኛሉ። ከእነዚህም አንዱ ወረኢሉ ነው። አካባቢው ምቹ የመኪና መንገድ የለውም። አንድ ቦታ ላይ ስንደርስ መንገዱ ለመኪና አስቸጋሪ ስለሆነ በእግር ለመውረድ ተገደድን። እዚህ ላይ ነው አሁን የምነግራችሁን ነገር የታዘብኩት።

ልክ ጉዞ ስንጀምር ‹‹ሴቶች እዚህ ይቆዩ›› ተባለ። ቦታውን የሚያውቁ ሰዎች ‹‹ኧረ ቅርብ እኮ ነው ይሂዱ›› አሉ። ይሄኔ ‹‹እናት የላችሁም? እህት የላችሁም? እንዴት በሴት ልጅ ላይ ትጨክናላችሁ?›› የሚሉ ቁጣዎች ተነሱ። ይሄ ሁሉ ሲባል ነፍሰ ጡርም ሆነ በዕድሜ የገፉች ሴት የለችም። ሁሉም ወጣቶችና ጤነኛ ናቸው። በነገራችን ላይ ወደ ቦታው ስንወርድ አንድም ሴት አልቀረችም፤ ሁሉም አብረው ወረዱ። ከአሁን አሁን አደገኛ የተባለውን ቦታ አየዋለሁ ስል የሚጎበኘው ቦታ ላይ ደረስን። እንኳን ለወጣት ለአዛውንት ሴቶችም የሚያስቸግር ቦታ አልነበረም።

የእኔ ጥያቄ የግድ ቦታው አደገኛ መሆን አለበት አይደለም፤ ትንሽም ቢሆን የሚያስቸግር ከሆነ መቸገር የለባቸውም። ዳሩ ግን ይሄ እንዲህ አይነት ድጋፍ ሴቶችን አይጎዳም ወይ ነው። እያወራን ያለነው ስለሴት ደራሲነት ነው። ታዲያ ያንን ቦታ እንዳታይ የተከለከለች ሴት እንዴት ነው የታሪክ ፀሐፊ የምትሆነው? ያንን ቦታ እንዳታይ የተከለከለች ሴት እንዴት ነው ስለአገሯ ነባራዊ ሁኔታ ከወንዶች እኩል የምታወራው? ልዩ ምልከታና ሀሳብ የሚገኘው ደግሞ ከእንዲህ አይነት ቦታዎች እንጂ ከትልልቅ መዝናኛ ቦታዎችና ከሆቴሎች አይደለም። ደራሲና ጋዜጠኛ የሚጽፈው ከእንዲህ አይነት ቦታዎች እንጂ ከትልልቅ የገበያ ማዕከላትና ከጌጣጌጥ ቤቶች ብቻ አይደለም።

ለሴቶች ቅድሚያ መስጠት አለበት። እንዲህ አይነቱ ግን ቅድሚያ መስጠት ሳይሆን ቅድሚያ መከልከል ነው። እስኪ የአምስት እና የአሥር ደቂቃ መንገድ በእግር ይሂዱ ማለት ምኑ ነው ‹‹እህት የላችሁም? እናት የላችሁም?›› የሚያሰኝ? እናቴ ወይም እህቴ በዚያ መንገድ ቢሄዱ ምን ይሆናሉ? ሴቶችን ማብቃት ማለትስ ይሄ ነው ወይ? የግድ ስቃይና መከራ ማየት አለባቸው እያልኩ አይደለም፤ ዳሩ ግን ከልክ ያለፈ ቁጥብነት ደግሞ ብዙ ነገር እንዳያዩ ያደርጋል።

ይሄ የሴቶች ጉልበት ብዝበዛ ወይም የሰብዓዊ መብት ጥሰት አይደለም። ይሄ ፆታዊ ጥቃት አይደለም። አንድ ኪሎ ሜትር እንኳን በእግሯ የማትሄድ ሴት ደራሲ ልትሆን አትችልም። በመጽሐፍ ውይይቶች ለምን የሴት ደራሲያን ቁጥር አነሰ የሚል ተደጋጋሚ ቅሬታ ይሰማል። ዳሩ ግን ሴቶች እንዲጽፉና እንዲያስተውሉ የሚያደርግ ማህበራዊ ስነ ልቦና የለንም።

የሆነው ሆኖ ግን በዚህ ሁሉ ውስጥ የጻፉ ብዙ ሴቶችም አሉን። እነዚያ ሴቶች እንዴት ደራሲ ሆኑ ካልን ወንዶች በዋሉበት መዋል ስለቻሉ ነው። እነዚህን ሴት ደራሲዎቻችንን ማየት አለብን።

### ሕይወት ተፈራ

ሕይወት ተፈራ ለብዙ ሴቶች ምሳሌ የምትሆን ናት። ለዚያውም ሴቶች ብዙም አይሳተፉበትም በሚባለው ፖለቲካ ውስጥ የተሳተፈች። መሳተፍ ብቻም ሳይሆን የኖረችበትን ዘመንና ያሳለፈችውን ሕይወት የጻፈች። የሕይወት ተፈራን ሕይወት ካየን ‹‹ሴት ስለሆነች›› ከሚለው አጥር ውስጥ እንወጣለን። ምክንያቱም የተጋፈጠቻቸው ፈተናዎች ሁሉ ከባድ ነበሩ።

ሕይወት ተፈራ በቀዳማዊ አጼ ኃይለሥላሴ ዘመነ መንግስት የተማሪዎች እንቅስቃሴ ውስጥ የነበረች ናት። ኢህአፓንና የኢህአፓን ዘመን ያስተዋለችና የተሳተፈችበት ናት። ከ1965 ዓ.ም የኢህአፓ የወጣቶች ሊግ ጀምሮ ብዙ እንቅስቃሴዎችን አድርጋለች። ‹‹ማማ በሰማይ›› በሚለው መጽሐፏ ያን ሁሉ ታሪክ ነግራናለች። ለስምንት ዓመታት ያህል እስር ቤት ውስጥ ቆይታለች።

መጽሐፏ ብዙ ተብሎለታል። ሌሎች መጽሐፎችም አሏት። በነገራችን ላይ የዚህ ጽሑፍ ዓላማ የሴት ደራሲዎችን የሕይወት ታሪክና ሥራዎቻቸውን መዘርዘር ሳይሆን ስማቸውን እየጠቀሱ ‹‹እንዲህም አሉን›› የሚለውን ማሳየት ነው። በሥራዎቻቸው ዝርዝር ላይ በሌላ ጽሑፍ መመለስ ይሻላል።

### ሸቶ መዝገቡ

‹‹ሰው በመሆኔ ደከምኩ›› በሚለው መጽሐፏ ትታወቃለች። ይህ መጽሐፍ ከ50 ዓመት በላይ ሆኖታል፤ ከዘጠኝ ዓመታት በፊት በ2006 ዓ.ም ከ48 ዓመታት በኋላ በድጋሜ ታትሞ ለገበያ ቀርቦ ነበር። ሸቶ መዝገቡ ገና በለጋነት ዕድሜዋ በኢትዮጵያ የባህል አብዮት ለማምጣት የታገለችና የጻፈች ናት። በነበረው ኋላቀር አስተሳሰብ ሴቶች ላይ ይደርስ የነበረው ነገር እንዲቀየር ትሰራ ነበር፤ የአሁኑን ዘመንም ከ50 ዓመታት በፊት ቀድማ ተንብያለች። ‹‹መማር እንጂ ለመማር ብሎ መማር አይገባም›› ሴቶች ላይ ይደርስ የነበረው ማህበራዊ አስተሳሰብ ለመቅረጽ ጥረት ያደረገች ናት።

### የዝና ወርቁ

‹‹መፍቻው እና ሌሎች አጫጭር ልቦለዶች›› የሚል መጽሐፍ አላት። ከ12 እስከ 18 ዓመት ባሉ ታዳጊ ሴቶች ስነ ምግባር ላይ ያተኩራል። በነገራችን ላይ ይሄ መጽሐፏ በነጻ ታድሏል። ለ30 ያህል ትምህርት ቤቶች ተሰጥቷል። የጥያቄና መልስ ፕሮግራም ላላቸው የሬዲዮ ጣቢያዎች ተሰጥቷል።

### ፀሐይ መላኩ

የሥነ ሥዕል፣ የሥነ ግጥም እና የእደ ጥበብ ሙያተኛ የሆነችው ደራሲ ፀሐይ መላኩ ከአሁን ቀደም አንጉዝ፣ ቋሳ እና ቢስራሔል የተሰኙ ረጅም ወጥ ልቦለድ መጽሐፎችን ለንባብ አብቅታለች። ‹‹እመ ምኔት›› የተሰኘው መጽሐፏ ደግሞ በቤተ ክርስቲያንና በገዳማት ታሪክና ትውፊት ላይ ያተኩራል። መጽሐፉን ከመጻፋቸው በፊት ሐይቅ እስጢፋኖስ አንድ ሱባኤ ከመቀመጣቸው በተጨማሪ ዝቋላ፣ አሰቦት፣ ራማ ኪዳነ ምሕረት፣ ዋሸራ እና ሌሎች ገዳማትን በመጎብኘት በመነኮሳት አኗኗር ላይ ጥናት በማድረግ አሥር ዓመታት ያህል ፈጅቶባታል።

### ከበደች ተክለአብ

ሠዓሊ ናት፣ ቀራጺ ናት፣ ገጣሚ ናት፣ የዩኒቨርሲቲ መምህር ናት። በርካታ የሕይወት ውጣ ውረዶችን አሳልፋለች። ከአዲስ አድማስ ጋዜጣ ጋር ባደረገው ቃለ መጠይቅ እንዲህ ብላ ነበር።

‹‹...በቀበሌና በወጣት ሊግ አማካይነት በተማሪዎች ንቅናቄ ንቁ ተሳትፎ ማድረጌን ቀጠልኩበት። ይሄም ሆኖ ግን ወታደራዊው መንግስት፤ የቀይ ሽብር ዘመቻን አውጆ ተማሪዎችን ከያሉበት እያደነ ማሰርና በጅምላ መጨፍጨፍ ሲጀምር፣ እኔም ለዚህ ክፉ ዕጣ ከታጩት ታዳኝ ተማሪዎች አንዷ መሆኔን አወቅሁት። ከተጋረጠብኝ አደጋ ማምለጥ ነበረብኝ። ለአንድ አመት ከመንፈቅ ያህል ከሌሎች አምስት የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ጋር አዲስ አበባ ውስጥ ተደብቀን ቆየን። በስተመጨረሻም ድንበር አቋርጠን ጅቡቲ ለመግባትና ጥገኝነት ለመጠየቅ በማሰብ፣ በ1971 ዓ.ም ከአዲስ አበባ ወጣን። በድብቅ ድንበሩን ሊያሻግሩን ፈቃደኛ የሆኑ ነጋዴዎች ብናገኝም፣ ሙከራችን ግን እጅግ አደገኛ ነበር። አቋርጠነው ልናልፍ ባሰብነው ድንበር ላይ ኢትዮጵያና ሶማሊያ ጦርነት ገጥመው ነበር። ይህ መሆኑን ሳናውቅ ነው፣ በእግራችን ጉዞ የጀመርነውና የሶማሌ መደበኛ ጦርና የሶማሊያ ነጻ አውጪ ግንባር ወታደሮች ሰፍረውበት ወደነበረው የጦር ካምፕ ሰተት ብለን የገባነው። በቁጥጥር ስር ውለን ወደ ሶማሊያ ተወስደን ታሰርን። በሁለቱ አገራት መካከል የተቀሰቀሰው ግጭት ከሶስት አመታት ጦርነት በኋላ ቢጠናቀቅም፣ እኛ ግን ቀጣዮቹን አስር አመታት ያሳለፍናቸው በሶማሊያ እስር ቤቶችና የጉልበት ስራ ካምፖች ውስጥ ነው። በስተመጨረሻም በኢጋድ ስብሰባ ላይ በተደረገ ስምምነትና በአለማቀፉ የቀይ መስቀል ድርጅት አግባቢነት ይመስለኛል፣ ሁለቱ አገራት የጦር እስረኞችን ለመልቀቅ ፈቃደኞች ሆኑ። እኛም በ1981 ዓ.ም ከእስር ተፈታን...››

የእነዚህን ሴት ደራሲያን ሕይወት መቀንጨብ ያስፈለገው ያለ ምክንያት አይደለም። ሴትም ትሁን ወንድ ደራሲነት አንድ ቦታ ቁጭ ብሎ እንደማይሆን ነው። አንድ ደራሲ ያላየውንና ያልሰማውን ሊጽፍ አይችልም። እርግጥ ነው ደራሲ ለመሆን ሲባል መንሳቆልና መንገላታት ያስፈልጋል ማለት አይደለም። ቢያንስ ቢያንስ ግን አካባቢን እንኳን ለማስተዋል የሚያስችል እንቅስቃሴ መኖር አለበት። ይሄ ደግሞ ለደራሲነት ብቻ ሳይሆን ለየትኛውም ሥራ ቢሆን አካባቢን ማስተዋል የግድ ነው። የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር ‹‹ሴቶችና ሳይንስ›› በሚል ባዘጋጀው አንድ መድረክ ላይ አንዲት ጥናት አቅራቢ ይህንኑ ጉዳይ ሲናገሩ ሰምቼ ነበር። ሴቶች በሳይንስ ተመራማሪ ይሆኑ ዘንድ አካባቢያቸውን ማስተዋል አለባቸው። ለዚህም ማንኛውም ሰው ሊያደርገው የሚችለውን የእንቅስቃሴ ዕድል ማግኘት አለባቸው፤ ተፈጥሮን ማስተዋል አለባቸው።

ሴት ደራሲያን በጣም ጥቂት ናቸው። በግጥምና በፊልም ላይ ነው አብዛኛው ተሳትፏቸው፤ ብዙ የግጥም መድብል ያላቸው ሴቶች አሉን። ግጥም ደራሲ አያሰኝም ማለቴ አይደለም፤ እንዲያውም ትልቁ የጥበብ ጥግ የሚባለው ነው። ዳሩ ግን በፖለቲካና በታሪክ ፀሐፊነት ደግሞ በጣም አነሱ። እንደነ ገነት አየለ አይነት የታሪክ ፀሐፊዎችም ሊኖሩን ይገባል።

ከላይ የጠቀስናቸው ሴት ፀሐፊዎች መጽሐፍ የጻፉት ለመጻፍ የሚያስችል እንቅስቃሴ ስለነበራቸው ነው። የታደለች ኃይለሚካኤል መጽሐፍ(ዳኛው ማነው) የተጻፈው በእንደዚያ አይነት እንቅስቃሴ ውስጥ ስላለፈች ነው። ስለዚህ ደራሲ ለመሆን ስቃይና መከራ ማሳለፍ የግድ ባይሆንም አካባቢን መቃኘት ግን የግድ ነው።

ማህበራዊ

# ልዩ ልዩ

## የህፃናት አካል ጉዳተኝነትና የወላጆች ጫናን የመቀነስ እርምጃ

ሰላማዊት ውቤ

የመጀመሪያ ልጇ ነው፣ ሲወለድ ጭንቅላቱ ከሌሎች ህፃናት ለየት ማለቱንም ቀድማ አላስተዋለችም ነበር። ‹‹ከዚህ በፊት ወልጄ ስለማላውቅና ህፃኑ የመጀመሪያ በመሆኑ ገና የተወለዱ ህፃናት ጭንቅላት መጠን ምን እንደሚመስል አላውቅም›› የምትለው መስተዋት ወሰኑ (የተለወጠ ስም) ሁለት እና ሦስት ወር ሲሞላው ጭንቅላቱ ከተለመደው መጠን የተለየ መሆኑን በደንብ እየተገነዘበች መምጣቷን ታስረዳለች።

በሴት አዳሪነት ሥራ ለተሰማራችው መስተዋት ይሄ የልጇ ሁኔታ ኑሮዋን የበለጠ አክብዶባትና አወሳስቦባታል። ልጇ በተለይ ከሁለት ወር እስከ አንድ ዓመት ባለው ጊዜ በጣም ይወራጭ ስለነበር ምን እንደፈለገ ለማወቅ ስትቸገር ቆይታለች፣ አሁን ድረስም አብዝቶ ያለቅስና ይወራጫል። ስታቅፈውና ስታባብለው ዝም ይላል። አንድ ዓመት ሁለት ዓመት እያለ የጭንቅላቱ መጠን ሲጨምር ታድያ የበለጠ ግራ መጋባቷንም ታነሳለች። የሕፃኑ ጭንቅላት ላይ የነበረው ለስላሳ ቦታ እብጠት ያለው መስሏት ነበር። በእርግጥም እብጠቱ እየጨመረ በመምጣቱ ትክክል ነበረች መስተዋት። ይዛው ሆስፒታል ስትሄድ የህክምና ባለሙያዎቹ የጎደጎደው በኋላም ያበጠው ለስላሳው የሕፃኑ ጭንቅላት ክፍል (እርግብግቢት የሰውነት ፈሳሽ ማነስ ምልክት መሆኑ ነገሯት።

ይሄኔ የሚወስድልኝ ሰው ባገኝ ልሰጠው ነበር። ነገር ግን እንኳን ለመውሰድ ገና ጭንቅላቱን ሲያዩት ሰዎች ይደነግጣሉ። አሁን ድጋፍ እያደረገልኝ ያለ ድርጅትም እንዲወስድልኝ ሞክሬ ነበር ። ግን አልቀበለም አለኝ›› ትላለች በምሬት። መስተዋት ይሄን የምትለው ልጇን ጠልታው ሳይሆን የኑሮ ሁኔታ አስገድዷት እንደሆነም ትናገራለች። ‹‹እኔ ቀንም ሆነ ማታ ወዲያ ወዲህ ተሯሩጬ የዕለት ጉርሴን የምፈልግ ሴት አዳሪ በመሆኔ



ወጣት ስምረት ዘነበ (የፕሮግራም አስተባባሪ)

በፍፁም እሱን አቅፌ መቀመጥ አልችልም›› ስትልም ምክንያቷን ትገልፃለች።

ማርዋ እያሉ ሲያቆላምጧት የሰማነውና ስሟ ይሄው መሆኑን ብቻ የነገረችን ሌላዋ በተለያዩ ቤቶች ልብስ በማጠብ የምትተዳደረው እናት እንደምትለው ልጇ ሁለት እግሩን የተጎዳው በወቅቱ የፖሊዮ ክትባት ስላላስከተበ መሆኑን የሰማችው ከህክምና ባለሙያዎች ነው። አሁን ዕድሜው ገና በመሆኑ ዝም ብሎ በእንፍቅቁና በዳዴ ቢሄድም እያደገ ሲመጣ መሄድ የሚችለው በክራንች ታግዞ እንደሆነም ባለሙያዎቹ ነግረዋታል። ግን ደግሞ ሊድን ይችላል በሚል ሕክምና መከታተሉ ተስፋ እንድታደርግ አድርጓታል። ይህችም እናት በጉዳቱ ምክንያት ህፃኑ ስለሚያስቸግራት ወስዶ የሚያሳድግላት ብታገኝ ደስተኛ እንደሆነችም ትናገራለች።

‹‹የአካል ጉዳት ያላቸው ህፃናት ወላጆች በአብዛኛው ልጆቻቸውን አይፈልጓቸውም›› የምትለው በኢትዮጵያ አካል ጉዳተኞች ማህበራት ፌዴሬሽን ውስጥ የአካል ጉዳተኞች የፕሮግራም አስተባባሪ ወጣት ስምረት ዝናቡ ወደስራው ከመግባቷ በፊት ለአምስት ዓመታት አካል ጉዳተኛ ህፃናት ላይ ስለሰራችም ግንዛቤ እንዳለት ትናገራለች። ፕሮግራም አስተባባሪዋ እሷ የምትሰራበት ተቋም እንዲወስድላቸው የሚፈልጉና የጠየቁም እናቶች አሉ። ምክንያቱን ስትገልጽም በአብዛኛው የህፃናቱ ወላጆች በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ ያሉ፣ አብዛኞቹ በሴተኛ አዳሪነትና በየሰው ቤት ልብስ በማጠብ የዕለት ጉርሳቸውን የሚሸፍኑ መሆናቸው ነው። ይሄን ታሳቢ አድርጎ ለልጆቻቻው በምግብ አቅርቦትና በሌሎች በሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች ይደግፋቸዋል።

የአካል ጉዳተኛ ህፃናቱ በአካላቸው ጉዳት ምክንያት በእናቶቻቸው ላይ ከሚያሳድሩት ከፍተኛ ጫና አንፃር ድጋፉ በቂ አይደለም። በመሆኑም ጫናቸውን ለመቀነስ የሚያስችላቸውን ሌሎች ተጨማሪ ድጋፎች ማለትም ልጆቻቸውን ማዋያ፤ ለራሳቸው መጠለያ የሚሰጥበትም ሁኔታ አለ። ‹‹እኔ ከዚህ በፊት በአካል ጉዳተኛ ህፃናት ላይ ስሰራ ቆይቻለሁ›› የምትለው ወጣቷ የአካል ጉዳተኛ ህፃናት ጉዳታቸውንና በጉዳታቸው ምክንያት በሚንቀሳቀሱበት ወቅት የሚገጥማቸውን ህመም ወይም ችግር እንደ አዋቂ በአንደበታቸው መግለጽ አለመቻላቸው መሆኑን ታወሳለች።

ህፃናት ስሜታቸውን ወይም ህመምና የተቸገሩባቸውን ጉዳዮች የሚገልጹት በተለያየ መንገድ መሆኑንም ገልጻ ፍላጎታቸው ምን እንደሆነ የሚያስደስታቸውን የሚያስከፋቸውን ላናውቅና ላንረዳላቸው እንችላለን። በዚህ ወቅት ደግሞ ወደ መጮህ፣ ማልቀስ ነው የሚሄዱት። የእጅ ጉዳት የሌለባቸው ከሆኑ ያገኙትን ነገር ይደበድባሉ። ራሳቸውን ከግድግዳ ጋር የሚያጋጩም አሉ፤ መሬት ላይ የሚፈጠፍጡበትና መሬት ላይ እየወደቁ በመነሳት የሚንፈራፈሩበትም ሁኔታ ይፈጠራል። በዚህ ሁኔታ ደግሞ ለተጨማሪ ጉዳት ሊዳረጉ ይችላሉ። እንደ ፕሮግራም አስተባባሪዋ ይሄ ሁኔታቸው እጅግ አደገኛ ነው። ነገር ግን ወላጆቻቸው ወደ ሕክምናም ሆነ ሕክምና የሚያገኙበትን ሁኔታ ወደሚያመቻቸው ማህበር የሚያመጧቸው በጣም ዘግይተው ነው። እናቶች መስማት የተሳነው ህፃን ልጅ ቢኖርሽ መቼ ነው መስማት ያለመቻሉን ያወቅሽው ቢባሉ ላይመልሱ ይችላሉ። ምክንያቱም ከፍ እስኪሉ ድረስም ጉዳታቸውን የማያውቁላቸው ብዙ ናቸው። የአእምሮም ሆነ ሌላ የአካል ጉዳት ያላቸው ህፃናት በተለይ ተናግረው ያለባቸውን ችግር ለማስረዳት ይቸገራሉ።

ስለዚህ አካል ጉዳተኛ ህፃናት የወላጅን ትኩረት ማግኘት አለባቸው። ሁሉም ወላጅ ምን ዓይነት ልጅ አለኝ የሚለውን ማስተዋል እንዳለበትም ታሳስባለች። በእኛ አገር ለአካል ጉዳተኝነት ያለው ግንዛቤ ዝቅተኛ ስለሆነ ጉዳቱ የመጣው በወላጆቻቸው ሀጢያት፣ በመርገምትና ሌሎች ብዙ ዓይነት አመለካከቶችም አሉ። ነገር ግን አንዳንዱ የአካል ጉዳት ፈጥነው ወደ ሆስፒታል ካለመሄድ ሌላውም ቢሆን በተመሳሳይ ቸልተኝነት የሚፈጠር ሊሆን ስለሚችል ሁሉም ወላጅ የወለዳቸውን ልጆች የቀን ተቀን ሁኔታ መከታተል የተለየ ነገር ሲያይ ደግሞ ፈጥኖ ወደሆስፒታል መውሰድ ያስፈልጋል፣ አንዳንድ ችግሮች በመዘግየት ብቻ ታክሞ መዳን ወደማይችልበት ደረጃ ላይ ሊደርስ ይችላል ፣ ይህ ከሆነ በኋላ ደግሞ ልጆቹን ማገዝ ያስቸግራል።

የአካል ጉዳተኞች ስምምነት መብት በዚህ በኩል መተግበር አለበት። መንግስትም ለህፃናት በተለይም ለአካል ጉዳተኛ ህፃናት በጀት መመደብ ይገባዋል ትላለች።

# ዓለም አቀፍ



## ሙሰኞች የመዘበሩትን ገንዘብ በአገር ውስጥ ኢንቨስት እንዲያደርጉ ኬንያ ጠየቀች

በጋዜጣዉ ሪፖርተር

የኬንያ ሙሰኞች ከመንግስት እና ህዝብ የመዘበሩትን ገንዘብ በአገር ውስጥ ኢንቨስት እንዲያደርጉ ተጠየቁ።

እንደ ዓለም ባንክ መረጃ ከሆነ የኬንያ በለስልጣናት በየዓመቱ 2 ነጥብ 6 ቢሊዮን ዶላር በመመዝበር ወደ ሌሎች አገራት ያሸሻሉ።

ጎረቤት አገር ኬንያ በስልጣን ላይ ያሉ የአገሪቱ ሙሰኞች ከህዝብ እና መንግስት የመዘበሩትን ገንዘብ ቢያንስ በአገር ውስጥ ኢንቨስት እንዲያደርጉ ተማጽናለች።

የአገሪቱ ኦዲተር ቢሮ እንዳለው ከሆነ ምንጫቸው ያልታወቀ ገንዘብ ወደ ልማት እንዲቀየሩ ቢፈቀድ ኬንያ በአጭር ጊዜ ውስጥ እድገት ልታስመዘግብ ትችላለች ሲል አስታወቋል።

የቢሮው ዋና ዳይሬክተር ናንሲ ጋቱንጉ እንዳሉት የኬንያ ባለስልጣናት ከህዝብ እና መንግስት የመዘበሩትን ገንዘብ ከማሸሽ ይልቅ እዚሁ አገራቸው ውስጥ ኢንቨስት ቢያደርጉት የተሻለ ነው ብለዋል።

ባለስልጣናቱ ከኬንያዊያን ከሰረቁ በኬንያ ኢንቨስት ሊያደርጉ ይገባል፤ ይህ ከሆነ ነገ የአገሪቱን ኢኮኖሚ ለማሳደግ ብሎም ገንዘቡን ለማወቅ ትልቅ መደላደልን በመፍጠር የተጠያቂነት ሥርዓት ለማስፈንም በእጅጉ ያግዛል ብለዋል፡፡

የዋና ኦዲተሯን አስተያየት ተከትሎም ጉዳዩ በኬንያ ዋነኛ መነጋገሪያ አጀንዳ የሆነ ሲሆን ሁለት አይነት አስተያየቶች ከህዝቡ በመንጸባረቅ ላይ ይገኛል።

የመጀመሪያው ሀሳብ በዋና ኦዲተሯ ሀሳብ ተስማምተው ሀሳባቸው ሲያጋሩ ቀሪዎቹ ደግሞ እርስዎንም የሾምነው ምዝበራን እንዲቆጣጠሩልን ነበር ሲሉ ትችቶችን ሰንዝረዋል።

## በእንግሊዝ ለተመሳሳይ ጾታ ጋብቻ ጸሎት መፍቀድ የተወገዙ የቤተ-ክርስቲያን መሪ

በጋዜጣው ሪፖርተር



የእንግሊዝ ቤተክርስቲያን ለተመሳሳይ ጾታ ጋብቻ ጸሎት እንዲደረግ ድጋፍ ከሰጠች በኋላ ከመላው ዓለም የተሰባሰቡ የአንግሊካን መሪዎች የቤተ ክርስቲያኗ መሪ ጀስቲን ዌልቢ መሪያችን አይደሉም አሉ።

በመላው ዓለም የሚገኙት እና 42 አባላት ካሉት የአንግሊካን ኅብረት አባላት መካከል አሥሩን የሚወክሉት ሊቀ ጳጳሳት፤ ጀስቲን ዌልቢ ከአሁን በኋላ "የዓለም አቀፉ ኅብረት መሪ" አድርገን አንመለከታቸውም ብለዋል። ሊቀ ጳጳሳቱ ጨምረውም የእንግሊዝ ቤተ-ክርስቲያን "እናት ቤተ-ክርስቲያን" ከመሆን "ውድቅ" ተደርጋለችም ብለዋል።

የካንተበሪ ሊቀ ጳጳስ ጀስቲን ዌልቢ ከፍተኛ ቁጥር ባላቸው አብያተ ክርስቲያናት ተቀባይነት ሲያጡ ይህ ለመጀመሪያ ጊዜ ነው።

42 አንግሊካን አብያተ ክርስቲያናትን ያቀፈው ዓለም አቀፉ የአንግሊካን ኅብረት እ ኤ አ 1867 በእንግሊዝ አገር ከተመሠረተ ጀምሮ የካንተበሪ ሊቀ ጳጳሳት የኅብረቱ መንፈሳዊ መሪ ኃላፊነትን ሲወስዱ ቆይተዋል።

የካንተበሪ ሊቀ ጳጳሳት በኅብረቱ ላይ ይፋዊ ሥልጣን ባይኖራቸውም 'የሞራል ኃላፊነት' ያላቸው ሲሆን፣ የሊቀ ጳጳሳት 'አውራ' ተደርገውም ይወሰዳሉ።

የሊቃነ ጳጳሳቱን ተቃውሞ ተከትሎ የካንተርበሪው ሊቀ ጳጳስ ይፋዊ መኖሪያ የሆነው ላምቤዝ ቤተ-መንግሥት ባወጣው መግለጫ፤ በዓለም አቀፉ የአንግሊካን ኅብረት አስተዳደር ላይ ለውጥ አይኖርም ብሏል።

10 ሊቃነ ጳጳሳት እና በአሜሪካ እና ብራዚል የሚገኙ ሁለት ተገንጣይ አብያተ ክርስቲያናት ናቸው የእንግሊዝ ቤተ-ክርስቲያን ተመሳሳይ ጾታ ያላቸው ሰዎችን ለማጋባት እና ለጋብቻ ጸሎት መፍቀዷን የተቃወሙት።

ውሳኔውን የተቃወሙት የደቡብ ሱዳን፣ የቺሊ፣ የኢንዲያን ኦሽን፣ የኮንጎ፣ የሚያንማር፣ የባንግላዴሽ፣ የኡጋንዳ፣ የሱዳን፣ የአሌክሳንደሪያ እና የሜላኔሲያ ሊቃነ ጳጳሳት ናቸው። እነዚህ አብያተ ክርስቲያናት በተለይ በእሲያ እና በአፍሪካ ብዙ ተከታዮች ያሏቸው ናቸው።

ተቃውሟቸውን ያሰሙት ሊቃነ ጳጳሳት ባወጡት መግለጫ ላይ የእንግሊዝ ቤተ-ክርስቲያን በጥንታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ ጸንተው ከሚገኙት የኅብረቱ አባላት ለመለየት ወስናለች ብለዋል።

ከጥቂት ሳምንታት በፊት በጀስቲን ዌልቢ የምትመራው የእንግሊዝ ቤተ-ክርስቲያን የተመሳሳይ ጾታ ጋብቻ ለሚፈጽሙ ጸሎት እንዲደረግ ለመጀመሪያ ጊዜ ፍቃድ ሰጥታ ነበር። ይሁን እንጂ አሁንም ቤተ-ክርስቲያኗ በተመሳሳይ ጾታ ጋብቻ ላይ ያላት አቋም አልተቀየረም እንዲሁም የተመሳሳይ ጾታ ጋብቻ በቤተ-ክርስቲያን ውስጥ ማድረግ አልተፈቀደም ተብሏል፡፡

# ስፖርት



# ኢትዮጵያ ለሁለተኛ ጊዜ የዓለም ምርጥ 10 ኪሎ ሜትር ውድድር አዘጋጅ ሆነች

**አስማየሁ ግዛው**

በዓለም ከሚታወቁት የስፖርት ጋዜጦች አንዱ፣ "RUNNERS WORLD" ባወጣው መረጃ መሰረት ኢትዮጵያ በዓለም ላይ ከሚካሄዱት ምርጥ የ10 ኪሎ ሜትር የሩጫ ውድድሮችን በማዘጋጀት ለሁለተኛ ተከታታይ ጊዜ ቀዳሚ ሆናለች።

ጋዜጣው ለኢትዮጵያ ይህን ደረጃ የሰጠው "ታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ ዓለም አቀፍ 10 ኪሎ ሜትርን" በየአመቱ በታላቅ ድምቀትና ስኬት ማስተናገድ በመቻሏ ነው።

ከኢትዮጵያ በመቀጠል በለንደን የሚካሄደው "ቪታሊቲ" 10 ኪሎ ሜትር የጎዳና ላይ ውድድርና የፓሪስ 10 ኪሎ ሜትር ውድድር ሁለተኛና ሶስተኛ ደረጃ ላይ ተቀምጠዋል።

ረነርስ ወርልድ ታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ በርካታ ሰዎች የሚሳተፉበት የአፍሪካ ትልቁ የጎዳና ላይ ውድድር መሆኑን በማስታወስ ጭምር አሞካሽቶታል።

ይህንንም ተከትሎ የታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ ማኔጂንግ ዳይሬክተር ወይዘሮ ዳግማዊት አማረ ደስታቸውን ሲገልፁ" ታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያን ለማዘጋጀት ከሃያ ሁለት አመታት በፊት ጉዞ ስንጀምር የኢትዮጵያን ብርቅዬ አትሌቶች ስኬት የሚያንፀባርቅ ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ የጎዳና ላይ ውድድር እውን ለማድረግ እንደምንፈልግ ገልጸን ነበር፣ ከዓለም ምርጥ የ10 ኪሎ ሜትር የጎዳና ላይ ውድድሮች ቀዳሚ መሆን ማለትም ይህ ነው፣ ኢትዮጵያውያን አትሌቶች በአስር ኪሎ ሜትር የዓለም ምርጦች ናቸው፣ እኛም አሁን የዓለም ምርጡን 10 ኪሎ ሜትር ውድድር አዘጋጆች ነን ብለን በኩራት መናገር እንችላለን" ብለዋል።

ይህ ስኬት የኢትዮጵያ ስኬት መሆኑን የተናገሩት ወይዘሮ ዳግማዊት፣ በተለይም ከመጀመሪያ አንስቶ ለውድድሩ ድጋፍ ያደረጉ አትሌቶች የዚህ ስኬት ሚስጥሮች መሆናቸውን ገልጸዋል። በተጨማሪም ለተገኘው ስኬት ብዙ ባለድርሻ አካላት አስተዋጽኦ ማበርከታቸውን አክለው መንግስትም ላደረገው ድጋፍ ምስጋናቸውን አቅርበዋል።



**ኢትዮጵያ በዓለም ላይ ከሚካሄዱት ምርጥ የ10 ኪሎ ሜትር የሩጫ ውድድሮችን በማዘጋጀት ለሁለተኛ ተከታታይ ጊዜ ቀዳሚ ሆናለች**

ታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ ከዚህ ቀደም "The Challenge Awards " በተሰኘ መድረክ ላይ በጎዳና ላይ ሩጫ ዝግጅት ዘርፍ በዓለም ቀዳሚ ሆኖ በመመረጥ ልዩ ሽልማት መቀበሉ ይታወሳል፡፡

ዘ ቻሌንጅ አዋርድን የሚያዘጋጀው ሌትስ ዱ ዚስ (Let's Do This) በዓለም አቀፍ ደረጃ ከፍተኛ ተቀባይነት ያለው የድረ ገፅ ምዝገባ አገልግሎት ሲሆን የሽልማቱ አቅራቢ ደግሞ በከፍተኛና ልዩ የአትሌቲክስ ባለሙያዎች የተደራጀው ታዋቂው ራነርስ ዎርልድ መፅሄት መሆኑ ይታወቃል፡፡ በዓለም የሩጫ ስፖርት ኢንዱስትሪ የኦስካርን ያህል ክብርና ግምት የሚሰጠው ሽልማቱ በመላው ዓለም የሚካሄዱ ፈታኝ የስፖርት ውድድሮችን የሚያዘጋጁ፤ ጎን ለጎን የበጎ አድራጎት እንቅስቃሴዎችን የሚያከናውኑ ማህበረሰቦችና ግለሰቦችን በልዩ መስፈርቶች አወዳድሮ እውቅና ይሰጥበታል፡፡

ታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ ደረጃ ልዩ የክብር ሽልማቶችን ከዚህ ቀደምም ማሸነፍ ችሏል። በ2013 የመጀመሪያውን "የAIMS Social Award" የማህበረሰብ አዋርድ ማሸነፉ ይታወሳል፡፡

ታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ የዓለም አቀፉ የማራቶንና የጎዳና ላይ ሩጫዎች ማህበር AIMS አባል መሆኑ ይታወቃል፡፡ ኤይምስ AIMS በየዓመቱ የውድድር አዘጋጆች በሚያቀርቡት ማመልከቻ መሰረት ለአባል የማራቶንና የጎዳና ላይ ሩጫ አዘጋጆች በሁለት ዘርፎች አወዳድሮ የሶሻል እና የግሪን አዋርዶችን በማዘጋጀት ይሸልማል፡፡ ታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያም ከዓመታት በፊት ዓለም አቀፉ የጎዳና ላይ ሩጫ ማህበር በግሪክ አቴንስ ባዘጋጀው የሽልማት ስነስርዓት ላይ የAIMS Social Awardን አሸንፎ ነበር፡፡

ከ22 ዓመት በፊት በ10 ኪሎ ሜትር፤ 10 ሺህ ሰዎችን በማሳተፍ የጎዳና ላይ ሩጫ ውድድር የጀመረው ታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ በአሁኑ ወቅት የተወዳዳሪው ቁጥር ከ45 ሺህ ልቋል።

በአሁኑ ወቅት ዓለም አቀፍ እውቅናና ተሳትፎ ያላቸውን የጎዳና ውድድሮች አዲስ አበባን ጨምሮ በተለያዩ የኢትዮጵያ ከተሞች የሚያሰናዳውን ታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ የመሰረተው ጀግናው አትሌት ኃይሌ ገብረስላሴ ነው።

የተለያዩ የዓለማችን ዜጎች ምንም ዓይነት ዕድሜ፣ ጾታና ዘር እንዲሁም ሃይማኖትና የቆዳ ቀለም ሳይገድባቸው በአንድ መድረክ ሮጠው ስሜታቸውን የሚገልጹበት የሚደሰቱበትና ሁሉም አሸናፊ የሚሆኑበት ታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ በየዓመቱ በወርሐ ኅዳር ይካሄዳል፡፡ ሩጫው የአንድ ቀን ድግስ ሆኖ ነገር ግን ዓመቱን ሙሉ የሚጓጓለትና ዝግጅትም የሚደረግበት ነው፡፡ በዚህ ስኬቱ የተነሳም ዛሬ በአፍሪካ ትልቁ የጎዳና ላይ ሩጫ ሆኗል፡፡ የአዲስ አበባ ጎዳናዎች ልዩ ጌጥ እንደሆነ የተነገረለትና ኢትዮጵያን የሩጫ ምድር እንደሆነች ያስመሰከረም ሆኗል። ከዚህ ጎን ለጎን በሚያከናውናቸው የተለያዩ የበጎ አድራጎት ስራዎችም ተመስጋኝ ለመሆን በቅቷል።


## የጨረታ ማስታወቂያ

የአዲስ አበባ ጠርሙስና ብርጭቆ አክሲዮን ማህበር የሠራተኛ መዝናኛ ክበብ የመዝናኛ ክበቡን በኮንትራት ለድርጅት/በዘርፉ ለተሰማሩ ግለሰቦች በግልጽ ጨረታ አወዳድሮ መስጠት ይፈልጋል፡፡ በመሆኑም የመዝናኛ ክበቡ የመመገቢያ አዳራሽ እና የተሟላ የመገልገያ ዕቃዎች ያሉት ሲሆን በተጨማሪም የውሃ እና መብራት አቅርቦት ይሰጣል፡፡ ስለሆነም የተሟላ የክበብ አገልግሎት በተመጣጣኝ ዋጋ ለማቅረብ የምትፈልጉ ተጫራቾች የጨረታ ሰነዱን ይህ ማስታወቂያ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ለ20/ሃያ/ ተከታታይ ቀናት ዘወትር በሥራ ሰዓት የማይመለስ ብር 200.00 /ሁለት መቶ ብር/ በመክፈል ከድርጅቱ ሰነዱን መውሰድ የምትችሉ ሲሆን የጨረታው ዝርዝር መመሪያ እና ይዘት በጨረታ ሰነዱ ላይ የተካተተ መሆንኑን እየገለጽን ድርጅቱ የተሻለ አማራጭ ከአገኘ ጨረታውን የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

**ለተጨማሪ መረጃ በስልክ ቁጥር 0911 41 50 47/0921 22 33 35 ደውሉ መጠየቅ ይቻላል፡፡**

**የአዲስ አበባ ጠርሙስና ብርጭቆ አክሲዮን ማህበር**



| የንግድ ምልክት ምዝገባ ተቃውሞ ጥሪ ማስታወቂያ | | | |
|---|---|---|---|
| 1 | የአመልካች ስም :- ከበደ ምራጭ ኪዳኔ<br>የአመልካች አድራሻ፡- ወረዳ 08 የቤት ቁጥር 792, አራዳ አዲስ አበባ/ኢትዮጵያ | | |
| 2 | የማመልከቻ ቁጥር :- LTM/13453/2015<br>ማመልከቻው ገቢ የሆነበት ቀን፡- 11/04/2015 E.C. | | |
| 3 | ምልክት፡- | 4 | የምልክቱ መግለጫ፡-የምስል |
| | | 5 | የቀለም ዓይነት፡- ጥቁር እና ነጭ |
| | | 6 | የብቸኛነት መብት አለመጠየቅ መግለጫ፡- |
| | | 7 | ዓለም አቀፍ ምድብ፡- 35 |
| 8 | ማልከቻው የሚሸፍናቸው ምርቶች ወይም አገልግሎቶች | | |
| | የቡናና ሻይ ጅምላ ንግድ (ምድብ 35) | | |

አመልካች ከላይ የተመለከተውን የንግድ ምልክት ለማስመዝገብ ጥያቄ አቅርበዋል። ስለሆነም ተቃዋሚ ካለ የጋዜጣ ማስታወቂያው በወጣ በ 60 ቀናት ውስጥ የተጠቀሰው የንግድ ምልክት በመዝገብ እንዳይገባ የሚያስችል ማስረጃ ለኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረትባለስልጣን መ/ቤት ካልቀረበ ምልክቱን የምንመዘግብ መሆኑን እናስታውቃለን። ስለሆነም ማንኛውም ሰው ካለባለቤቱ ፍቃድ በዚህ ምልክት ከተጠቀመ በኢትዮጵያ ህግ ይጠየቃል።

**የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ባለስልጣን**

ADDIS ZEMEN VOl-LXXXII No-166 16/6/2015 (23/2/2023)


## አማራ ክልል

ከሳሽ ገበያው ተሻለ

ተከሳሽ ኢሳ ወርቄ

መካከል ስለለው የገንዘብ ክስ ክርክር ጉዳይ አቶ ኢሳ ወርቄ

መከሰስዎን አውቀው ክሱን በመዝገብ ቤት በኩል ወስደው መልስዎን በ27/06/2015 ዓ.ም. ለሆነው ቀጠሮ በ3፡00 ሰዓት ባ/ዳርና አካ/ከፍ/ፍ/ቤት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**በአብክመ ጠቅላይ ፍ/ቤት የባሕር ዳርና አካባቢዋ ከፍተኛ ፍ/ቤት**

ከሳሽ አቶ ናርዶስ ሽፈራው

በተከሳሽ ለወ/ሮ ፅጌ አስገዶም አብርሃ

መካከል ስላለው የገንዘብ ክርክር ጉዳይ ተከሳሽ መከሰስዎን አውቀው ክሱን በመዝገብ ቤት በኩል ወስደው መልስዎን በ22/06/2015 ዓ.ም. ለሆነው ቀጠሮ በ4፡00 ሰዓት ባ/ዳርና አካ/ከፍ/ፍ/ቤት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዝዟል፡፡

**በአብክመ ጠቅላይ ፍ/ቤት የባሕር ዳርና አካባቢዋ ከፍተኛ ፍ/ቤት**

ከሳሽ እነ አዝመራው ፀጋ

ተከሳሽ ለአቶ ሀብታሙ አክሎግ

መካከል ስላለው የገንዘብ ክስ ክርክር ጉዳይ መከሰስዎን አውቀው ክሱን በመዝገብ ቤት በኩል ወስደው መልስዎን ለ22/06/2015 ዓም. ለሆነው ቀጠሮ በ4፡00 ሰዓት ባ/ዳርና አካ/ከፍ/ፍ/ቤት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዝዟል፡፡

**በአብክመ ጠቅላይ ፍ/ቤት የባሕር ዳርና አካባቢዋ ከፍተኛ ፍ/ቤት**

## አዲስ አበባ አስተዳደር

በከሳሽ ኦሮሚያ ኢንሹራንስ ኩባንያ አ/ማ እና

በተከሳሽ ነገሰ ዲርባ

መካከል ስላለው የፍ/ብሔር ክርክር ጉዳይ ፍ/ቤቱ በሰጠው ትዕዛዝ ተከሳሽ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የንግድና ኢንቨስትመንት ምድብ 2ባ/ኢንሹራንስ ችሎት እየታየ መሆኑን በዚህ ማስታወቂያ ጥሪ አውቀው መልሱን በጽሁፍ በ28/06/2015 ዓ.ም. በ5፡00 ሰዓት በሬጅስትራር በኩል እንዲያቀርቡ እና ክስ ለመስማት በ04/07/2015 ዓ.ም. በ3፡30 ሰዓት ችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ንግድና ኢንቨስትመንት ምድብ ችሎት**